# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በ አዳም ረታ ሕማማትና በገና ውስጥ

በ

ሰላማዊት በየነ

ግንቦት፣ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በአዳም ረታ ሕማማትና በገና ውስጥ


## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

### የአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


### የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ሰላማዊት በየነ

አማካሪ

አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር)



2010 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎችጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በአዳም ረታ ሕማማትና በገና ውስጥ

በ

ሰላማዊት  በየነ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ፊርማ

____________________ ____________________

ፈታኝ ስም ፊርማ

____________________ ____________________

____________________ ____________________

# ምስጋና

በፍቅራቸው እያገዙ ለዚህ ላደረሱኝ ቤተሰቦቼ (እቴትዬ) በተለይም ድንገት መጥቶ በፍቅርና በእንክብካቤው ተስፋ ለሆነኝ ከገባሁበትም አዘቅት አውጥቶ ወደ ሕይወት ጎዳና ለመለሰኝ አባቴ ለማርክ ስታንቦቭስኪ ፍቅሬ ወደር የለውም፡፡ ጨኸቴንና ብስጭቴን ችላችሁ ከጎኔ የቆማችሁት ለኩኪዬና ለእማ ሁሌም ለናንተ ደስታ ልደክም ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ አርቆ ባለማሰብና ባለማስተዋል ያልሆነ መንገድ ስመርጥ በምክራቸውና በእገዛቸው ላቃኑኝ መምህሬ ለቴዎድሮስ ገብሬ አክብሮቴንና ምስጋናዬን አቀርባለሁ፣ የሥጽሑፍን ፍቅር በልቤ ላሳደረው መምህሬ ለመሐሪ ዘ መልዓክ ወርቁ ምስጋና ይገባዋል፡፡ በደንብ ያልታሸ ስራ ሳቀርብ ቃል ከማረም አንስቶ ድክመትና ጥንካሬዬን እየለየሁ ባሰብኩት መንገድ እንድሰራ ላገዙኝ አማካሪዬ ለአየለ ፍቅሬ (ዶ/ር) ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ጥናቱ ሳይጀመር በፊት፣ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያልቅም ድረስ ከጎኔ ሆና ስደክም ድጋፌ፣ ሳዝን እንባ አባሼ ለሆነችው ከጓደኛ በላይ እህት ለሆነችልኝ ለወይንሸት ሙሉጌታ ምስጋና ብቻ በቂ ባይሆንም ምስጋና አቀርባለሁ፤ “እወድሻለሁ”፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ለውይይት ስራ ላስፈታሁዋቸው፣ በትርጉም፣ በጽህፈት፣ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በመስጠትና በመፈለግ ላገዙኝ ልዑል፣ ከሊፋ፣ ብኒያም፣ ሞሐመድ፣ አዜብ፣ ጌች፣ ሳለዬ፣ አለምነህ ለክፍል አጋሮቼ እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ርእስ ገጽ

ምስጋና.......... I

ማውጫ.......... II

አኅጽሮተ ጥናት .......... V

ምዕራፍ አንድ.......... 1

መግቢያ.......... 1

1.1 የጥናቱ አደረጃጀት .......... 2

1.2 የጥናቱ ዳራ.......... 2

1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.......... 3

1.4 ዓላማ.......... 4

1.4.1 ዓቢይ አላማ.......... 4

1.4.2 ንዑሳን አላማዎች .......... 4

1.5 የጥናቱ ጥያቄዎች.......... 4

1.5.1 ዓቢይ ጥያቄዎች.......... 4

1.5.2 ንዑሳን ጥያቄዎች .......... 5

1.6 የጥናቱ ፋይዳ.......... 5

1.7 የጥናቱ አድማስ.......... 5

1.8 የጥናቱ ዘዴና የማንበቢያ ስልት .......... 6

1.8.1 የናሙና አመራረጥ .......... 7

1.8.2 ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ዘዴ .......... 7

ምዕራፍ ሁለት ..................................................... 9
2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ..................................................... 9
2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ..................................................... 9
2.1.1. ግብረገብ ..................................................... 9
2.1.1.1. ግብረገባዊ ፍልስፍና (Moral Philosophy) ..................................................... 10
2.1.1.2. የሥነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ..................................................... 12
2.1.2 ግብረገብ እና ደመነፍስ ..................................................... 18
2.1.3. ግብረገብ እና ሥነ ጽሑፍ ..................................................... 21
2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ..................................................... 23
ምዕራፍ ሦስት ..................................................... 33
3. የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በሕማማትና በገና ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ንባብ ..................................................... 33
3.1 “የሳር ልጆች” ..................................................... 33
3.1.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ..................................................... 33
3.1.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ..................................................... 38
3.2 “እራት” ..................................................... 40
3.2.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ..................................................... 40
3.2.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ..................................................... 48
3.3 “ስንዝሮ” ..................................................... 50
3.3.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ..................................................... 50
3.3.2 የተፈጥሮና ባህል ዕርቅ ..................................................... 56
3.4 “የሐር ነዶ” ..................................................... 59

3.4.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ...... 59
3.4.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ...... 62
3.5 "ሕማማትና በገና" ...... 64
3.5.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ...... 64
3.5.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ...... 73
3.6 "የምስራች! ልጅ እንደ እናቷ ኾነች" ...... 77
3.6.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ...... 77
3.6.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ...... 80
3.7 "መንገዶች ሁሉ ወደ ዘሴ ይወስዳሉ" ...... 81
3.7.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት ...... 81
3.7.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ ...... 85
ምዕራፍ አራት ...... 86
ማጠቃለያ ...... 86
ዋቢ ጽሑፎች ...... 91

## አኅጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት የተፈጥሮና የባህል ግጭት እና ዕርቅ በአዳም ረታ *ሕማማትና በገና* ውስጥ በሚል ርእስ ቀርቧል። በቴክስቶቹ (ገጸንባቦቹ) ላይ ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ንባብን በማድረግ የግብረገብንና ደመነፍስን ጉዳይ ተንትኖ የመመልከቻን መንገዶች ማቅረብ ዋንኛ ዓላማው ነው። በተመረጡት ሰባት ቴክስቶች (ገጸንባቦች) ውስጥ ግብረገብ ባህላዊ እሴቶችን ማስጠበቅ ሲያቅተው፣ ተፈጥሯዊ ስሜት ለመታመቅ በመጣሩና ገጸ ባህሪያቱ ግብረገባዊ ጽናትን ያላደበሩ በመሆናቸው ለደመነፍሳዊ ስሜታቸው በመማረክ ግጭት ውስጥ ሲገቡ ተስተውሏል። በማፈንገጣቸው ምክንያት አንድም ኅሊናዊ ጸጸት፣ አንድም አካባቢያዊ ጫና (ቅጣት) ሲደርስባቸው የአእምሮ መታወክ እንደሚገጥማቸውና፣ ከዚህ ለመሸሽም የተለያዩ መፍትሄዎችን በማበጀት ሲታረቁ ተቃኝቷል። መታረቂያዎቹም ወይ በማስመሰል ለባህላቸው ተገዢ ሆነው በድብቅ ተፈጥሯዊ ፍላጎታቸውን በፈለጉት መንገድ ማርካት፣ ወይ እሴታቸውን ተቀብለው በጸጸት መኖር፣ ወይ በማኅበረሰቡ ውስጥ እየኖሩ ልቡናዊ መነጠል ነው፤ አለበለዚያም እራስን በማጥፋት ሰላምን ለማግኘት መሻት ነው። ከዕርቅ በኋላም ቢሆን ስጉ፣ ሃላፊነትን መቀበል የሚከብዳቸው፣ በማስመሰል የተሞሉ ይሆናሉ። ውስጣዊ ጉዳዩም ከስልጣኔ ጋራ ተያይዘው የሚመጡ የሌላ ሃገር እሴቶችን በመቀበልና ሃገራዊ እሴቶችን ባለመልቀቅ መካከል የሚፈጠረውን ግብግብ የሚያስቃኝ ሲሆን በአባቶችና በልጆች መካከልም ይህ አለመጣጣም ባህላዊ ማንነትን እስከማሳጣት የሚደርሱ መነጠሎች፣ እንዲሁም በሁለቱ እሴቶች መካከል የሚፈጠረውን ፍትጊያ መቋቋምና ማስታረቅ ባለመቻል እራስን ማጥፋት ሁሉ ያለበት ነው። እነዚህ ጉዳዮች ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ዘዴን በመጠቀም መፈልፈል በሚቻል መልኩ ተሰናስለው ቀርበዋል። የተለያዩ አንጻሮችን በመጠቀምም ሊነሱ ይገባቸዋል የተባሉ ፍቺዎች ቀርበዋል። የግብረገብን ጽንሰ ሃሳብ በጭብጥነት በመጠቀም ለገጸ ባህሪያት መንደፊያ፣ ለትልምና ለታሪክ መመስረቻ በመጠቀም በዘመናችን ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ግብረገብ ነው የሚለውን ሃሳብ አዳምም ጥበብን ተጠቅሞ አቀንቅኖታል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ደመነፍስ ሰውን ከእንስሳ የሚያመሳስለው ተፈጥሯዊ ባሕሪው ነው፡፡ እንስሳት ሲርባቸው የሚበሉትን በደመነፍስ ይፈልጋሉ፤ ጠላት ሲመጣባቸው ይከላከላሉ፤ የመራቢያ ጊዜያቸው ሲደርስ ግንኙነት ስለሚያደርጉ ይራባሉ፤ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ ከማን ጋራ፣ ምን፣ ለምን፣ በምን ወዘተ. የምናደርገውን ማድረግና የምንፈጽመውን መፈጸም አለብን? የሚሉትን ጥያቄያዊ መስፈርቶች አርቅቀውና ደንግገው አይመሩም፡፡ ይህን ድንጋጌ የሚከተለው ሰብኣዊ ፍጡር ስሜቱን ተከትሎ ሕይወቱን በደመነፍስ የሚመራ አይደለም፡፡

የሰው ልጅ በሕብረት ኑሮው ውስጥ በተፈጥሯዊ ስሜቱ እየተነዳ እርስ በርስ እንዳይጠፋፋ ደመነፍሳዊ ፍላጎቱን በባህል ይገታበታል፡፡ ባህል ተፈጥሯዊ ስሜቱን እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ከማን ወዘተ. ጋራ ማድረግ እንዳለበት የሚነግረው መመሪያውና ልጁን ወይም ዘግይቶ የመጣን የባህሉን አባል ባህሪ መቅረጫ ስርዓቱ ነው፡፡ በሃይማኖትና በሥርዓተ ድንጋጌዎች እያለዘበ ግብረገባዊነትን ያስተምራል፤ ሕይወቱንም ይመራበታል፡፡ መልካምና፣ መጥፎ፤ የሚደረግና የማይደረግ፤ ትክክልና ስህተት እያለ በማስቀመጥ ግብረገባዊ ባህሪን ለማላበስ ይጥራል፡፡ የአንድ ግለሰብ ባህሪ በባህሉ ግብረገባዊ እሴቶች መቃኘቱም የግድ ነው፡፡

ግብረገባዊ እሴቶች እንደየማኅበረሰቡ ቢለያይም ዓለም አቀፋዊ የሆኑና ሁሉም ሰው ሊፈጽማቸው የሚገቡ ተብለው የተቀመጡ ግብረገቦች አሉ፡፡ ጠና ደዎ Pojmanንን ጠቅሰው ያስቀወመጧቸው አስር መርሖች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

> *አትዋሽ፣ ቃል ኪዳንን ጠብቅ፣ አትግደል፣ የሌሎችን ነጻነት አክብር፣ አትስረቅ ወይም አታጭበርብር፣ ሌሎች ሰዎችን እርዳ፣ ለሰዎች ፍትኃዊ አያያዝ አድርግ (ማለትም ከግብረገብ አንጻር አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር በዘር፣ በቆዳ ልዩነት፣ በብሔር ብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ አያያዝ ከማድረግ ተቆጠብ) ሥቃይ የሚያስከትል ነገር በማንም ላይ አትፈጽም፣ መልካም ነገርን በመልካም እንጂ በእኩይ አትመልስ፣ ፍትኃዊና ምክንያታዊ የሆኑ ሕግጋትን አክብር* (ጠና፣ 2008፡ 46-50)

እነዚህ ግብረገቦች መከወን ያለባቸው ከባህል ልዩነት ጋራ ተያይዘው ከሚነሱት ሥነ-ምግባራዊ እሴቶች አንጻር ሳይሆን ሰው ሁሉ ተስማምቶ፣ የርሱንም የሌላውንም እኩልነትና ነጻነት ጠብቆ/ አስጠብቆ ለመኖር ሲባል ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የህልውናው ጉዳይም ይሆናል፡፡ ለምን?

ቢባል *ሥነ* ስርዓት የበላይ ሆኖ በማይገዛበት ማኅበረሰብ ውስጥ ጉልበተኞች ለመንገስ ይጥራሉ፤ እርስ በርስ መጠፋፋትና ማለቅም ይመጣል። በዚህ ከቀጠለ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት በዓለም ላይ የተፈጠሩትን አይነት እልቂቶች ይከሰታሉ።

ይህ ለህልውና አስፈላጊ የሆነ ጭብጥ በተለያዩ መስኮች ውስጥ ይነሳል። ከነሱ ውስጥ ደግሞ አንዱ ፍልስፍና ነው። በፍልስፍና ውስጥ ግብረገብ አንዱ አውታር ነው። ለፍልስፍናዊው ግብረገብ ደግሞ *ሥነ* ጽሑፍ "ምቹ ማደሪያው" ሆኖ ያገለግላል። *ሥነ* ጽሑፍም ግብረገብም የሰው ልጅ ብቻ ጉዳዮች ስለሆኑ እርስ በእርስ መሰናሰል ይችላሉ። ይህ ጥናትም በተመረጡት ቴክስቶች (ገጸንባቦች) ውስጥ *ሥነ* ጽሑፉ ግብረገብን እንዴት ለጉዳዩ ማደሪያነት እንደተጠቀመውና እና ግብረገብ እንዴት እንደተቀነቀነ ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ዘዴን በመጠቀም ይተነትናል።

## 1.1 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ ፋይዳ፣ አድማስ እና የጥናቱ ዘዴን ያቀፈ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ፣ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ቀርቧል። በምዕራፍ ሦስት የተመረጡት ቴክስቶች (ገጸንባቦች) በተቀነበበው ንድፈ ሃሳብ እየታገዙ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል። በመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያና የጥቁምታ ሃሳቦች ቀርበዋል።

## 1.2 የጥናቱ ዳራ

አዳም ረታ የአማርኛ ረዥምና አጭር ልብ ወለዶች ደራሲ ነው። የመጀመሪያ ስራዎቹ የሆኑትን *አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች* 1977 በታተመው መድበል ውስጥ "ድብድብ፣ ዕብዱ ሺበሺ፣ ሲሮክ እና ሲፊንክስ" የተሰኙ አጫጭር ልብወለዶችን አሳትሟል። በ*ጭጋግና ጠል* 1990 የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ ውስጥ ደግሞ "ዘላን" የተሰኘ አጭር ልብወለዱ ታትሟል። ከዚህ በኋላ በግሉ ያሳተማቸው ስራዎች እንደየዘመን ቅደም ተከተላቸው፡- *ማህሌት*፣ 1981 ዓ.ም፣ አጭር ልብ ወለድ፤ *ግራጫ ቃጭሎች*፣ 1997 ዓ.ም፣ ረዥም ልብወለድ፤ *አለንጋና ምስር*፣ 2001 ዓ.ም፣ የአጭር ልብወለዶች ስብስብ፤ *እቴሜቴ ሎሚ ሽታ፣* 2001 ዓ.ም፣ አጫጭር ልድወለዶችና ኖቬላዎች ስብስብ፤ *ከሰማይ የወረደ ፍርፍር፣* 2002 ዓ.ም፣ የአጫጭር ልብወለዶች ስብስብ፤ *ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ*፣

2003 ዓ.ም፣ አጫጭር ልድወለዶችና ኖቬላዎች፤ *ሕማማት እና በገና፣* 2004ዓ.ም፣ አጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ፤ *መረቅ፣* 2007 ዓ.ም፣ ረጅም ልብወለድ፤ *የስንብት ቀለማት* 2008 ዓ.ም ረዥም ልብወለድ፤ *አማሌሌ እና ሌሎች አጫጭር ልብወለዶች* በተሰኘው መድበል ውስጥ "አማሌሌ" የተሰኘው *ታሪክ*፣ በ2009 ዓ.ም እና *አፍ*፣ 2010 ዓ.ም. ናቸው።

የዚህን ደራሲ ስራዎች የተለያዩ ሃያስያን፣ የሥነ ጽሑፍ ተማሪዎች፣ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና መሰል አካላት ምርምር አድርገውባቸዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በዚህ ደራሲ ስራዎች ላይ የተለያዩ ጥናቶች በመጀመሪያና በሁለተኛ ድግሪ የተሰሩ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥናቶችና መጣጥፎች ይገኙበታል። መጣጥፎች፡- ቴዎድሮስ ገብሬ፣ 1992 ዓ.ም፣ "ውስጣዊ ግለወግ÷ እንደ ወረደ እና ሕልም በትረካ ብልሃትነትበ ‹ኤልዛቤል›"፤ ማንያዘዋል እንደሻው፣ 1985 ዓ.ም፣ "የአዳም ልጆች ንፅፅር"፤ ቴዎድሮስ ገብሬ፣ 2013 እ.ኤ.አ፣ "Mahilet: A Laboratory of Stylistic Experimentation"

ለድግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች፡- ህይወት ዋለልኝ፣ በ2012 እ.ኤ.አ፣ "Narrative techniques of Adam Reta's Gracha Qachiloch: Stream-of-Consciousness in focus"፤ እንደሻው ለተራ፣ በ2005 እ.ኤ.አ.፣ "Stream of Consciousness as Reflected in Adefris and 'ke' Lijitwa'"፤ አክሊሉ ደሳለኝ 2010 እ.ኤ.አ. ፣ "Existentialism in the Selected Creative Works of Adam Reta"፤ ታደሰ ሺበሺ፣ 2005 ዓ.ም፣ "ሚቶሎጂያዊ ጥናት እቴሜቴ ሎሚ ሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ በተሰኙ የአዳም ረታ መድበሎች"፤ ቴዎድሮስ አለበል፣ 2006 ዓ.ም፣ "‹ልጅነት› በ*ማሕሌትና አለንጋና ምስር*፤ ሥነልቡናዊ ንባብ"፤ እንዳለጌታ ከበደ፣ 2004 ዓ.ም፣ "አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች" የተሰኙት ጥናቶችና ሌሎችም ስላልተገኙ ያልተዳሰሱ ጥናቶች ተደርገዋል። በዛ ያሉ ጥናቶች በደራሲው ስራ ላይ ቢደረጉም ግብረገብን የዳሰሰ ጥናት አልተገኘም፤ ትንሽ የዕውቀት ክፍተት ለመሸፈን ሲባል ይህ ጥናት ሊደረግ ችሏል።

## 1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በተለያዩ የግል ውይይቶች ወቅት ለአዳም ረታ ስራዎች የሚቀርቡ አስተያየቶች ተገቢ መስለው አልታዩኝም። ይህም የመጣው ስራው በይነ ዲሲፕሊናዊ አቀራረብ ስላለውና የማንበቢያ መንገድን ካለማግኘት ይመስለኛል። ልቦለዶቹ ታሪክ ብቻ ሳይሆኑ አንባቢው ወይም ሃያሲው

እንደየአጠለቀው መነጽር የሚለያዩ ሃሳቦችን መፈልፈያ መሆናቸውን አንዱን ጽንፍ በመመርመር ለማረጋገጥና ለማሳየት መሻቴ፣ እንደ ሥነ ጽሑፍ ተማሪነቴም ስራውን ለመመልከት ከሚረዱ መንገዶች ውስጥ አንዱን ለማሳየት ይህን ጥናት አድርጌያለሁ።

የሰብእና መንጠፍ በዘመናችን እየተስፋፋ እንደሆነ ይገለጻል። ይህ ጉዳይ ደግሞ በተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ እንደተቀነቀነ ጥናቶች ያመላክታሉ (ለምሳሌ፡- መአዛ ገብሩ፣ 2005)። ይህ ጉዳይም ከግብረገባዊነት መጥፋት ጋራ ተያይዞ የሚከሰት ነው። የተለያዩ መጻሕፍት ሥነ ምግባር (ግብረገብ) የዘመኑ አሳሳቢ ጉዳይ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ሊደረግ ሲወሰን የአዳም ስራ ለጥናት ከተመረጠ በኋላ በግብረገባዊ ጉዳይ በልጽጎ የተገኘው *ሕማማትና በገና* የተሰኘው የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ በመሆኑ ሊመረጥ ችሏል። በተጨማሪም የግብረገብና የቴክስቶቹ (ገጸንባቦቹ) ውህደትም ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) በሆነ መንገድ የቀረበ በመሆኑ በዚሁ ዘዴ ማቅኛነት ልጠቀመው ወድጃለሁ።

## 1.4 ዓላማ

### 1.4.1 ዓቢይ አላማ

የሰው ተፈጥሮና ባህል አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠርና የበላይ ለመሆን የሚያደርጉትን ትግልና ትግሉ የሚያስከትለውን ቀውስ በመፈተሽ የመመልከቻ መንገዶችን ማውጣት።

### 1.4.2 ንዑሳን አላማዎች

በተመረጡት ቴክስቶች ውስጥ የሰው ተፈጥሮ ከባህል ጋራ በሚያደርገው ግጭትና እርቅ ላይ ዲኮንስትራክሽናዊ ንባብ ማድረግ፣

ታሪኮቹ የቀረቡበትን ቅርጽ በማፍረስ በአስተማስሎ የቀረቡትን ጭብጦች መፈልፈልና አዲሱን ቅርጽ መግለጽ፣

ተፈጥሮና ባህል ከግጭት በኋላ የሚኖራቸው የዕርቅ ገጽታ ምን እንደሚመስል ማሳየት።

## 1.5 የጥናቱ ጥያቄዎች

### 1.5.1 ዓቢይ ጥያቄዎች

አዳም ረታ በተመረጡት ልብ ወለዶች ውስጥ የሰው ተፈጥሮንና የባህልን ግጭትና እርቅ እንደምን አርቅቆታል?

### 1.5.2 ንዑሳን ጥያቄዎች

ለምንድን ነው ተፈጥሮና ባህል ግጭት የሚፈጥሩት?

ተፈጥሮና ባህል እንደተጋጩ ቢቀሩና ባይታረቁ የሚከሰቱ ችግሮች ምንድን ናቸው?

ከዕርቅ በኋላ የሚኖራቸው ሕይወት ምን ይመስላል?

## 1.6 የጥናቱ ፋይደ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ዘመን ትኩረት ሊደረግበት ይገባል ተብሎ በተለያዩ ምሁራን እየተሰበከ ያለው የሥነ ምግባርና ግብረገብ ጉዳይ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህ ስራም ልብወለዶቹ ውስጥ የግብረገብ ጉዳይ እንዴት እንደቀረበ በመመረመር፣ ሥነ ጽሑፍ ለጉዳዩ የተመረጠ ማቀንቀኛ ሆኖ ስለቀረበ በበይነ ዲሲፕሊናዊ መንገድ ጥናቶችን ለሚያደርጉ ባለሙያዎች በተወሰነ መልኩ ሊያግዝ ይችላል፡፡

ከተለያየ መስክ ለሚመጡ አንባቢያንና የሂስ ባለሙያዎች የተመረጡት ስራዎች በተመረጠው ንድፈ ሃሳብ  እንዴት እንደሚመረመሩና የተለያዩ ፍቺዎችን እንዴት እንደሚፈለፍሉ ሊያሳይ ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ በትምህርት ክፍሉ በአዳም ረታ ስራዎች ላይ ወይም በሌሎች ሥራዎች ላይና በጉዳዩ ዙሪያ ወደ ፊት ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎችና አካላት የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ሆኖ ያገለግላል፡፡

ለተለያዩ ጉዳዮች ጥናት ማድረግ ፈልገው ርዕስ ለሚፈልጉ እገዛ ሊያደርግላቸው ይችላል፡፡ የአዳም ረታ ስራ በተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦች መምሪያነት ጥናት የተደረገባቸው ቢሆንም በዚህ ትምህርት ክፍል የግብረገብ ጉዳይ ጥናት ስላልተደረገበት ይህንኑ ክፍተት ለመሙላት ያግዛል፡፡

## 1.7 የጥናቱ አድማስ

ደራሲው የተለያዩ አጫጭርና ረዥም ልብ ወለዶች ቢኖሩትም ለዚህ ጥናት የተመረጠው መጽሐፍ *ሕማማትና በገና* ብቻ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አስራ ሦስት አጫጭር ልብ ወለዶች ቢኖሩም አገልግሎት ላይ የዋሉት “ሕማማትና በገና፣ እራት፣ ስንዝሮ፣ የምስራች ልጅ እንደናቷ ኾነች!፣ የሐር ነዶ፣ የሳር ልጆች እና መንገዶች ሁሉ ወደ ዘሴ ይወስዳሉ” የተሰኙት ሰባት ታሪኮች ብቻ ናቸው፡፡

ተፈጥሮና ባህል ሰፊ ትርጓሜ አላቸው፡፡ ይህ ጥናት ግን ዋና ዋና ግንዶቻቸው የሆኑትን በመምረጥ ትኩረቱን አድርጎባቸዋል፡፡ ተፈጥሮ፡- የሰውን ተፈጥሮ የሚቃኝ ጉዳይ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከባህል ውጪ የሚኖረውን የሚመለከት ጉዳይ ስለሆነም ከደመነፍስ ጋር ትይዩ የሆነ ፍቺን ይዞ በተለዋዋጭነት ይጠቀማቸዋል፡፡ ባህል፡- ሰፊ ቅርንጫፎች ስላሉትና አብላጫውን ክፍል የሚወስደው ግብረገብ ስለሆነ ከባህል ውስጥ ግብረገብ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ግብረገብ የሚጠቀልለው ሰፊ ጉዳይን በመሆኑና የአካባቢ ተጽዕኖዎችም ታላሚ ስለሆኑ ርዕሱ በባህል ሊቀነበብ ችሏል፡፡

ግብረገብ በብዙ መስኮች ውስጥ ስር ሰዶ እሳቤዎችን ቢያበጅም፣ ጥናቱ በፍልስፍናዊው ግብረገብ ላይ ብቻ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን እንዲሁም ዲኮንስትራክሽናዊ የመሄሻ ዘዴን በመጠቀም በቴክስቶቹ ውስጥ ስለ ጽንሰ ሃሳቡ የተቀነቀኑትን ጉዳዮች ሁሉ በአስተማስሎ ከተሰገሰጉበት ፈልፍሎ አቅርቧል፡፡

በተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ከሃገር ውስጥም ከውጪም ስራዎች የተቃኙ ቢሆንም የተመረጡት ስራዎች ከጉዳዩ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ ለምን? ቢሉ በጉዳዩ ዙሪያ በርካታ የተሰሩ ስራዎች ስላሉና መምረጡ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

## 1.8 የጥናቱ ዘዴና የማንበቢያ ስልት

ጥናቱ ቴክስትን (ገጸንባብን) በንድፈ ሃሳብ መመርመር እንደመሆኑ መረጃ ማቅረቢያ የሚሆነው ተንታኝ ዘዴ ነው፡፡ ተንታኝ ዘዴ አንድን ጉዳይ ለመፈከር፣ ለማብራራትና ለመተንትን ተመራጭ ዘዴ ነው፡፡ ስለዚህም ቴክስቶቹን (ገጸንባቦቹን) የግብረገብ ንድፈ ሃሳብና ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) የማንበቢያን ዘዴ በጋራ በመጠቀም ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ጥናቱ ሁለት አይነት መጻሕፍትን አገልግሎት ላይ አውሏል፡፡ እነርሱም፡- የመጀመሪያው ጥናቱ የሚሰራበት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የሆነው የአዳም ረታ ሕማማትና በገና ሲሆን፣ ሁለተኛዎቹ ዳህራይ የመረጃ ምንጭ የሆኑት ደግሞ ለንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት እና ለክለሳ ድርሳንነት ያገለገሉ ናቸው፡፡

### 1.8.1 የናሙና አመራረጥ

አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያግዛሉ የተባሉ ስራዎች፣ ንድፈ ሃሳቦችና የማንበቢያ ዘዴ ተመርጠዋል። በአዳም ረታ ስራዎች ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተደርጎባቸዋል። እስካሁን ጥናት ያልተደረገበት (በተለይም ከአጫጭ ልብ ወለድ ስብስብዑቹ ውስጥ) ሕማማትና በገና በመገኘቱ እና የሰው ተፈጥሮን እና የባህል ግጭትና ዕርቅን የሚያስቃኘው ይኸው ስራው በመሆኑ የተመረጠ ቢሆንም፣ አንድም ይህ ጥናት ለተፈቀደለት የገጽ ብዛት ሲባል፣ አንድም የሚጠናውን ጉዳይ በሚገባ ማሳየት ይችላሉ በሚል እምነት በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አስራ ሦስት ታሪኮች ውስጥ ሰባቱ ታሪኮች ብቻ ተመርጠዋል።

በታሪኮቹ ውስጥ የቀረቡትን ግጭቶች በመያዝ የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ የተተነተነ ሲሆን ለጉዳዩ ለማጠናከሪያነት ምልልሶች፣ ተረካዎች፣ ሀቲቶች፣ አውድና ጠቅላላ ታሪኩ ተዳሰዋል። የተለያዩ ተምሳሌቶች ከቅዱስ መጻሕፍት፣ ከሥነ ጽሑፍ መዝገበ ተምሳሌቶች የተወሰዱ ሲሆን አለም ዓቀፋዊ፣ ሃገራዊና ግለሰባዊ ዘይቤዎች እንደየ አስፈላጊነታቸው ታትተዋል። አብዛኛው ትርጓሜ በአውድ ላይ የተመሰረተና ለመፍቻነትም ዲኮንስትራክሽንን (ነገረ አፍርሶትን) የታከከ ነው። የናሙናው አደረጃጀት ታሪኮቹ በተናጠል በግጭትና በዕርቅ ንዑስ ርእስ ተከፋፍለው የቀረቡ ሲሆን የመጽሐፉን የታሪክ ቅደም ተከተል ጠብቀው ይጓዛሉ።

በተመረጡት ቴክስቶች (ገጸንባቦች) ውስጥ ግብረገባዊ ጉዳይን ለመመርመር ሲታሰብ ታሪኮቹ ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) የማንበቢያ ስልትን እንደሚፈልጉ ምልክቶች ስለታዩ (ለምሳሌ፡- በተለያየ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ ሀቲቶች እና ድርጊቶች በአንድነት ተዛንቀው ቀርበዋል። ተቃራኒ እየመሰሉ ግን የሚመሳሰሉ፣ ተመሳሳይ እየመሰሉ ደግሞ ተቃራኒ የሚሆኑ ገጸባሕሪያት እና ሀቲቶች ቀርበዋል።) ለጥናቱ ማቅኛነት ይኸው ስልት ከጽንሰ ሃሳቡ ጋር በትይዩ እንዲጓዝ ተመርጧል።

### 1.8.2 ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴ

> *Deconstruction is a constant reminder of the etymological link between 'crisis' and 'criticism'. It makes manifest the fact that any radical shift of interpretative thought must always come up against the limits of seeming absurdity. Philosophers have long had to recognize that thinking may lead them inescapably into regions of*

*scepticism such that life could scarcely carry on if people were to act on their conclusions* (Norris, 2004: xii).

ዲኮንስትራክሽን በJaques Derrida የተፈጠረ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በቴክስቱ ላይ ብቻ አተኩሮ በምክንያታዊ ተቃውሞ ታሪኩ ከቀረበበት ገጽታ በስተጀርባ ጭብጥን ወይም ፍሬ ነገርን የሚመረምር የማንበቢያ ስልት ነው። ቃላት በራሳቸው ፊት ለፊት ከሚሰጡት ትርጉም ባሻገር ሌላ መልዕክት አላቸው፤ ስለዚህ ውስጣቸው መመርመር አለበት በሚል ዕምነት ላይ የተመረኮዘም ነው።

አንድ ቃል ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ብሔራዊ፣ እና ግለሰባዊ ፍቺዎችን አዝሏል። በሚገባበት አውድም ከነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ቢመረመር በቀጥታ ሊያስረዳ ከሚችለው በተጨማሪ ሌላ ፍቺን ይዞ ይገኛል። ተምሳሌቶችም እንዲሁ በቀጥታ ከሚገልጹት ነገር በተቃራኒው ያለውን ጉዳይ በጥንድ አቅፈው ይገኛሉ። ስለዚህ ብቸኛ የሚባል ትርጉም የለም። ቴክስቶች (ገጸንባቦች) ከተለያየ አንጻር ቢመረመሩ የተለያዩ ፍቺዎችን አዝለው ይገኛሉ።

Norris እንደሚያስረዳውም ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) ስልት በነቀፌታና ሂስ መካከል ያለውን ስርወ ቃላዊ ጭብጥ አስታዋሽ ነው። በፈላስፋዎች ዘንድ ፍቺን ለመፈልፈል እንደሚያመች ሁሉ ግን ጭብጡን ከስረ መሰረቱ ሊለውጠውና ቴክስቱን (ገጸንባቡን) በተሳሳተ መንገድ መረዳት ላይ ሊያድርስ ይችላል የሚል ስጋት አለ። አንድ ቴክስት በተለያየ መንገድ ለመተርጎም ምቹ ሆኖ እስከቀረበ ድረስ የተለያዩ ፍቺዎችን ማፍራቱ ግን ስህተት አይደለም፤ ምክንያቱም ሁሉም አንባቢ የየራሱ አረዳድ አለውና ነው።

አንድ ነገር የሚገነባው ከተለያዩ አላባውያን ነው። የተገነባው ነገር ሲፈርስ አላባውያኑ የተለየ ቅርጽን ይዘው ይቀጥላሉ እንጂ ከፈረሰው ቅርጽ ጋር አብረው አይጠፉም። በዚህ ጥናት ታሪኮቹ የያዙት ሃሳብ ላይ ዲኮንስትራክሽናዊ ትንታኔ በማድረግ፣ የሰው ተፈጥሮና ባህል የሚያደርጉት ግጭትና እርቅ ላይ በተመረጠው ንድፈ ሃሳብ ማሕቀፍነት ምርመራ ተደርጓል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል የግብረገብ ጽንሰ ሃሳብና እሱን ለመመርመር የሚረዱ የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ለጥናቱ ማቅኛነትም የግብረገባዊ ፍልስፍና ንድፈ ሃሳቦች በማሕቀፍነት መጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ከግብረገብ ጋራ ተቆራኝተው የሚጠኑ ጽንሰ ሃሳቦች ተዳሰዋል፡፡

#### 2.1.1.ግብረገብ

ግብረገብ ምንድን ነው? የሚለው ጉዳይ ከመመለሱ በፊት ሊጠራ የሚገባው ነገር አለ፡፡ ከጊዜው የቋንቋ አጠቃቀምና ቃሉ ከሚገልጸው ሃሳብ ጋራ ተያይዞ የቃላቱ መገኛ ስፍራ የተለያየ ቢሆንም ሥነ ምግባርና ግብረገብ ተመሳሳይ ብያኔ ነበራቸው፡፡ ይህን ተያያዥነታቸውን ምክንያት በማድረግም አንዳንዴ ግብረገብና ሥነ ምግባር ልዩነታቸውን አጥርቶ ባለማወቅ ለተመሳሳይ ሃሳብ መግለጫ በተለዋዋጭነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ የትርጉም መመሳሰልና መዛባቱ የመጣውም የሥነ ምግባርና የግብረገብ ሥርወ ቃል ተቀራራቢ ትርጉም ያዘሉ በመሆናቸው ነው፡፡ እንደ ጽንሰ ሃሳብ ከሚኖራቸው ፍቺ አንጻር ግን ይህ ተገቢ አለመሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ (ለምሳሌ፡- ጠና (2008)፣ ttena (2008))፡፡

በዚህ ዘመን ግን ግብረገብና ሥነ ምግባር ተወራራሽ ሆነው አያገለግሉም፡፡ “Ethics is the science which deals with the right or wrong of human conduct.” (LaBossiere, 2012: 27) ሥነ ምግባር ግብረገብንና ግብረገባዊ ጉዳዮችን የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን ግብረገብ ደግሞ በሥነ ምግባራዊ ንድፈ ሃሳቦች እየተመራ፣ ስለ ተፈጥሮው፣ ዓይነቱ፣ መሰረቱ፣ እሴቱና አሰራሩ የሚጠና ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡

ግብረገብ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ከሥነ ምግባር ተጠኝነት ባሻገር በራሱ ያለው ፍቺስ ምንድን ነው? ግብረገብ አንድም የድርጊትንና የባህሪን ትክክልነትና ስህተትነት፣ ተገቢነትና ኢ ተገቢነት የሚለይና በጉዳዮቹ ላይ ለመፍረድ/ለመወሰን የሚያስችሉ እሴቶችን የሚያዘጋጅ፤ አንድም እነዚህ ውሳኔዎች እንዲለመዱ፣ እንዲበለጽጉና እንዲተላለፉ የሚረዳ፣ አንድም እሴቶቹ እንዳይጣሱ የሚጠብቅና ከተጣሱም ለጸጸት የሚዳርግ ኅሊናዊ ባህሪ ነው፡፡ ግብረገባዊ መርሖች

የእለት ተእለት ሕይወትን ማስሄጃ ድንጋጌዎች ናቸው ጠና (2008)፣ Pojman (2005)፣ Aguas, (2013)፣ Lind (1995)፣ Miller (1984)። ከላይ ለቀረበው የግብረገብ ብያኔ የቀረበ ወይም ከሃሳቡ ጋር የተመሳሰለ አቋም አላቸው።

“Morality is also closely related to law; and some people equate the two practices. Many laws are instituted in order to promote well-being, resolve conflicts of interest, and promote social harmony, just as morality does,…” (Pojman, 2005: 3). በሌላ በኩል ግብረገብ የሕግ ተስተካካይ እንደሆነ የሚገልጸው Pojman እንደሚያስረዳው የሕግ አድርግ አታድርግ ድንጋጌዎች ከግብረገብ መርሆዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። ሕግ የማኅበረሰብን ፍላጎት በተገቢው መንገድ እንደሚያስተናግድ፣ ያጠፋን ቀጥቶ ወደ እርቅ እንደሚመልሰው ሁሉ ግብረገብም ተመሳሳይ ሂደትን ያደርጋል። ልዩነቱ ሕግ ደንቦችን ደንግጎ የግድ ተፈጻሚ ሲያደርግ፣ ግብረገብ ድንጋጌዎችን ተመርኩዞ ኅሊናዊ ጫናን በማድረስ የሚሰራ መሆኑ ነው።

ግብረገብን ለመመርመር የተለያዩ ጠገጎችን ማንሳት ይቻላል። ከነዚህም ውስጥ በተለያዩ የታሪክ ክስተቶች ከተፈጠሩ ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ላይ የሚመረኮዘው፡- ሃይማኖታዊ ግብረገብ፣ የሲግመን ፍሮይድን ንድፈ ሃሳብ መሰረቱ ያደረገው፡- ሥነ ልቡናዊ ግብረገብ እና የተለያዩ ፈላስፋዎች ጽንሰ ሃሳብ መነሻው የሆነው የፍልስፍና ግብረገብ ተጠቃሾች ናቸው። ይህ ጥናት መሰረቱና ትኩረቱን ያደረገው ፍልስፍናዊ ግብረገብን ነው።

#### 2.1.1.1. ግብረገባዊ ፍልስፍና (Moral Philosophy)

ፍልስፍና የተለያዩ አእማዳት እንዳሉት ይታወቃል። ስለ ብዛታቸው ግን የተለያየ አቋም አላቸው። “Not all lists of philosophy would agree, but most of them would almost certainly include six: *metaphysics, epistemology, value-theory, ethics, aesthetics, and logic*” (Miller, 1984: 5). የMillerን ሃሳብ ይዘው፣ የግድ ማካተት አለባቸው ያሉዋቸውን ጽንሰ ሃሳቦች ወደ አራት የሚያሳንሱት (ጠና፣ 2008) ናቸው። እነዚህም ዲበ አካል፣ ሥነ ዕውቀት፣ ሥነ ፋይዳ እና ሥነ አመክንዮ የተሰኙ ቅርንጫፎች ናቸው። የዚህ ጥናት ጉዳይ የሆነው ሥነ ምግባር፣ በMiller ገለጻ እራሱን ችሎ የሚቆም (ለብቻው የሚጠና) ቢሆንም በጠና ምደባ ደግሞ በሥነ ፋይዳ ቅርንጫፍ ከሥነ ውበት “aesthetics” ጋር በአንድ ክፍል ይጠናሉ።

> *Moral philosophy refers to the systematic endeavor to understand moral concepts and theories. It undertakes to analyze concepts and terms such as "right", "wrong", "permissible", "ought", "good", and "evil" in their moral contexts. Moral philosophy seeks to establish principles of right behavior that may serve as action guides for individuals and groups. It investigates which are paramount to a worth-while life or society. It build and scrutinizes arguments in ethical theories* (pojman, 2005: 2).

pojman እንደሚሉት የግብረገባዊ ፍልስፍና አንዱ ጉዳይ ግብረገብን ለማጥናት የሚረዱንን ጽንሰ ሃሳባዊና ንድፈ ሃሳባዊ ዘዴዎችን ማሰናዳት ነው፡፡ ግብረገብ ውስብስብ የሆነ የሰው ልጅ የንቃተ ኅሊና አካል እንደመሆኑ በራሱ ውስብስብና ከባህል፣ ቋንቋና የሰው ተፈጥሮ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በቀላሉ እንኳን ብናየው ከሶቅራጥስ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ውስብስብነቱ ሳይጠራ ቆይቷል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመመርመርና ስምምነታዊ መስመር ለማበጀት የሚረዱትን ቀመሮች የሚያበጅልን ይህ የግብረገብ ፍልስፍና ነው፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ ተገቢና ኢ ተገቢ፣ ትክክልና ስህተት፣ ጥሩና መጥፎ የሚባሉ ነገሮች የሚወሰንባቸውን ግብረገባዊ አውድ መፍጠር ፋይዳው ነው፡፡

እንዲሁም የሰው ልጅ ለድርጊቱ የሚሰጠውን የሰናይና እኩይ እሴት እንዴት እንደሚሰራው፣ እንዴት እንደሚገልጸው ለመተንተን ያገለግለናል፡፡ እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ለምንድን ነው? ማዕከላዊ ጉዳዩ የሆነው የሰው ልጅ ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖር በመልካም ሰብዕና የተቀረጸ ባህሪ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህንን ማድረጊያ መንገዱ ቀዳሚው ግብረገብ ነው፡፡ የግብረገብን ጉዳይ የሚመረምረውና የሚያጠናውም ሰላማዊ ኑሮ ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲስፋፋ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ የእለት ተእለት ሕይወትን ለመምራት  የሚጠቅሙ ግብረገባዊ ብልሃቶችን ያቀርባል፡፡

የግብረገብ ፍልስፍና ጥናት የግብረገብን ህላዌ፣ ምንጭና መሰረት ያካትታል፡፡ ይህ ደግሞ የግብረገብ እና የግብረገብ ዕውቀት መሰረት ነው፡፡ በሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ላይ የተመረኮዙ የግብረገብ ንድፈ ሃሳቦች አሉ፡፡ "Fortunately, there are moral theories that are based on the concept of human nature or a natural way and they can be used by those employing this method." (LaBossiere, 2012: 39) እንደ ሥነ ዘዴ የሰፈሩት ንድፈ ሃሳቦች በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ ግብረገብ ከተለያዩ ዘርፎችና ጉዳዮች ጋር

ተጣምሮ ሊጠና የሚችል ሃሳብ ሲሆን ይህንኑ ቁርኝት ለማጥናት የሚረዱ ሥነ ዘዴዎች አሉ፡፡ ምሁራንም በተመቻቸው መልኩ የግብረገብ ማጥኛ ዘዴዎችን ቀምረዋል፡፡

### 2.1.1.2. የሥነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች

ግብረገብን ለማጥናት የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎች ቢኖሩም ሦስት ዋና ዋና የሥነ ምግባር ንድፈ ሃሳብ ክፍሎች አሉ፡፡ እነርሱም ቨርቹ ኢቲክስ፣ ቴሊኦሎጂካል እና ዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሃሳቦች ናቸው ጠና (2008)፣ pojman (2005) እና Gammel (2006) እንደሚገልጹት፡፡

**ቨርቹ ኢቲክስ**

ይህ የሥነ ምግባር ፍልስፍና የሥነ ምግባርንና ግብረገብን ዳራ ከማንሳቱም በተጨማሪ የግብረገብ መሰረቱ ባሕሪ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ጥሩ ባህሪ ያለው ሰው ሁል ጊዜ መልካም ይሆናል፤ ወይም መልካም ነገሮችን ብቻ ለመስራት ይሻል፡፡ በተቃራኒው ያለው ደግሞ የእኩይ ተግባር ባለቤት ነው ባይ ናቸው፡፡ በዚህ ስር የሚነሱት ሦስቱ የግሪክ ፈላስፎች ናቸው፡፡ ግብረገባዊ ፍልስፍና ትኩረት ተሰጥቶት መቀንቀን የጀመረው በጥንታዊያን የግሪክ ፈላስፎች ነው፡፡ ከነሱ ውስጥ ዋናዎቹ ሶቅራጥስ፣ ፕሌቶ (አፍላጦን) እና አርስቶትል (አርስጣጣሊስ) ናቸው፡፡ ሶቅራጥስ የግብረገብ ጉዳዮችንና ጥያቄዎችን በማንሳት የመጀመሪያው ነው፡፡

**ቴሊኦሎጂካል ሥነ-ምግባር**

ማንኛውም ድርጊት የሚፈጸመው ለአንዳች ግብ ነው፤ ስለዚህ ምግባርንም ሰናይ እና እኩይ የሚያስብለው ከታለመለት ግብ አንጻር ነው ብሎ የሚሞግት ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ፍጹም መጥፎ፣ ፍጹም መልካም፣ ፍጹም እውነትም የሚባል ነገር የለም፡፡ ከቆሙለትና ካነገቡት ዓላማ መሳካትና አለመሳካት አንጻር ነው የተገቢነትንና የኢተገቢነትን ብያኔ የሚያገኙት ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ መልካም ውጤትን የሚያስገኙ ድርጊቶች ሰናይ ሲሆኑ፣ መጨረሻቸው በተቃራኒው የሆኑት ደግሞ እኩይ ናቸው፤ በማለት ይሞግታል፡፡

**ዲኦንቶሎጂካል**

የዚህ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች ትክክልና ስህተት የሚባሉት ድርጊቶች ከውጤት ጋራ ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም ብለው ያምናሉ፤ ድርጊት የሚያስገኘውን ውጤት የግብረገብ መለኪያ አድርጎ መጠቀምም ተገቢ አይደለም ሲሉም ይገልጻሉ፡፡ የመጨረሻን ግብና የሚገኝን ጥቅም ታሳቢ ሳያደርጉ ከልብ በመነጨ ግብረገባዊነት መልካም ነገሮችን ማድረግ ያስፈልጋል፤

መልካም ነገሮች ደግሞ ጥሩነታቸው ከውስጥ በሚወጣ ስሜት ይታወቃሉ ይላሉ፡፡ መልካም ድርጊቶች መፈጸም ያለባቸውና ሰውም ግብረገባዊ የሚሆነው ግዴታን በመወጣት ነው፡፡ የግብረገብ ግዴታዎች የተሞሉባቸውን እሴቶች በማክበርና በመፈጸም ሃላፊነትን መወጣት ደግሞ የሰናይ ምግባር ባለቤት ያደርጋል ባይ ናቸው፡፡

ለካንት ግብረገባዊ ሕይወት ማለት መልካምን ነገር የማግኘት ወይም ደስተኛ የመሆን ችሎታ አይደለም፡፡ ማድረግ የሚገባን ነገር (ሰናይ ምግባሮችን) ከውስጥ በፈለቀ፣ የራስ ተነሽነት በተገቢው መንገድ የማድረግና ከድርጊቱም ጥቅምን አለመፈለግ ነው፡፡ ይህም ግዴታን ከመወጣት አንጻር ሊደረግ ይገባዋል፡፡

ይህ ጥናት የዲኦንቶሎጂካልን ንድፈ ሃሳብ ይቀበላል፡፡ ነገር ግን ቨርቹ ኢቲክስንም ሆነ ቴሊኦሎጂካል ንድፈ ሃሳብን አይገፋም፡፡ ይህ የሚሆንበትም ምክንያት በሚመረመሩት ታሪኮች ውስጥ የተለያዩ የግብረገብ ጽንሰ ሃሳቦች ስላሉና እነርሱን ለመመርመር ስለሚረዱ ነው፡፡ ጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ መሰረትን በመጣል ማሕቀፍን ለመስራት ግን አውታር መያዝ ስላለበትና ትኩረቱ በስፋት በድርጊታቸው ላይ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን ንድፈ ሃሳብ በመሰረትነት መርጧል፡፡ ዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሃሳብ ከካንት የግብረገብ ፍልስፍና ጋር ይጣመራል፡፡

### 2.1.1.3 ግብረገብን ለመመርመር የሚረዱ ጽንሰ ሃሳቦች

የግብረገብ ባሕሪ የማይነጣጠሉ ግን በተቃራኒ ጽንፍ ያሉ ሃሳቦችን በጋራ ይዞ መቅረቡና እኩል የመልካምነትና የእኩይነት መለያ መስጠቱ ነው፡፡ ቀጥሎ በሚቀርቡት ጽንሰ ሃሳቦች ውስጥም የሚስተዋለው ይህ ነው፡፡ ጠና (2008፣ 69-100) ግብረገብን ለማጥናት የሚረዱ ጽንሰ ሃሳቦች ትንታኔዎች፣ ለዚህ ጥናት በጽንሰ ሃሳብነት ስለሚያገለግሉ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**እሴት እና ፋክት**

መልካም (የተሻለ) ሕይወት መኖርን መሰረቱ ያደረገው ይህ ጽንሰ ሃሳብ የሰው ልጅ ለሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እሴትና ዋጋ መስጠቱ የተለየ ያደርገዋል፡፡ እናም ግብረገባዊ ድርጊቶች መፈጸም ያለባቸው የተሰጣቸውን እሴት ከግብ ለማድረስ ነው፡፡ ግብረገብም ሲመዘን ለሰው ልጅ ከሚኖረው እሴት አኳያ ነው፡፡ የግብረገብ ሕግጋት በራሳቸው ግብ ናቸውና ልንፈጽማቸው እንገደዳለን፡፡ Aguasም ለዚህ ሃሳብ የቀረብ የግብረገብ እሴት ትንታኔን ሰጥተዋል፡፡

**ሰናይና እኩይ ድርጊት**

ሰዎች በግብረገብ የጋራ ስምምነት ውስጥ መደረግ የሚገባውና የማይገባ ብለው ባስቀመጧቸው መርሖች መሰረት ለድርጊታቸው ተገቢነትና የማይገባነት ዋጋ የሚሰጥበትና የሚመዘንበት ጽንሰ ሃሳብ ነው። የቆመለትን አላማ ከግብ ለማድረስ መልካም ወይም እኩይ መንገድን ሊጠቀም ይችላል። ሰናይና እኩይ ነው ብሎ ከለየ በኋላ መልካሙን መንገድ የሚጠቁመው ይህ ዘዴ ነው። ሰናይ ድርጊቶች ሲባሉ ሁሉም ተመሳሳይ ዋጋ የላቸውም። ስለዚህ ለሰናይ ድርጊቶችም የተሻለ ደረጃን ያበጃል፤ ይህም "ከፍተኛ ሰናይ" ይባላል የመጨረሻው መልካም ድርጊት። የሰውን ሰብኣዊነት የሚያጎድፍ፣ ክብርን የማያስጠብቅና ጥቅም አልባ ድርጊት ሁሉ እኩይ ነው። እኩይ ሲባልም፡- የተፈጥሮ እኩይ፣ ግብረገባዊ እኩይ ይባላሉ። ግብረገባዊ እኩይ የሚባለው አንድ ሰው ሁን ብሎና አቅዶ ማኅበረሰቡ የማይፈቅደውን ኢ-ግብረገባዊ ድርጊት ሲፈጽምና ሰውን ሲጎዳ ነው።

**ሰናይና እኩይ ምግባር**

ሰናይ ምግባርና ግብረገባዊ ግዴታ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። የአንድን ሰው ግብረገባዊ ምግባር የምንገመግምበት ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን ከሰናይና እኩይ ድርጊት የሚለየው ይህን ባህሪ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው። በአርስቶትል ገለጻ "ወርቃማ አማካይ" ይባላል። ይህም ከጥልቅ ተቃራኒ ስሜቶች በመውጣት ጽንፍ ስሜቶችን መቆጣጠር መቻልን የሚመለከት ነው። ሰናይ ምግባር አብሮን የሚወለድ ሳይሆን ስሜቶቻችንና ደመ-ነፍሶቻችንን በመቆጣጠር ዘወትር በምናከናውነው በጎ ድርጊት ውስጥ የሚፈጠር ነው።

**የሚገባና የማይገባ**

በግብረገብ ሕግጋት ሊደረጉ የሚገባቸውና የማይገባቸው ተብለው የተደነገጉትን የመፈጸምንና ያለመፈጸምን ጉዳይ የሚመለከት ነው። መሆን የሚገባና የማይገባም ድርጊት በዚህ ስር ነው የሚመዘነውና ተገቢነቱ የሚረጋገጠው። ከሁለቱ ጥጎች የተለየ ሦስተኛ ምርጫ የለም። በግብረገብ መልካም ናቸው የተሰኙ ድርጊቶችን መፈጸም፣ ባሕሪያትንም መተግበር፣ እንዲሁም እኩይ የተባሉትን አለመሆንንና አለመፈጸምን የሚመለከት ነው። በዚህም ርምጃ ግብረገባዊና ኢ-ግብረገባዊ ተብለን ልንፈረጅ እንችላለን። ይህም መጥፎ ሰውና ጥሩ ሰው የሚለውን ስያሜ ከማኅበረሰቡ እንድንቀዳጅ ያደርጋል፤ ስለዚህ በሚገባ ተገቢ የሆኑትንና ያልሆኑትን ማወቅና መፈጸም ይኖርብናል።

### የመምረጥ ነጻነትና ግዴታ

ግብረገባዊ ወይም ኢ-ግብረገባዊ ለመሆን የምርጫ ነጻነት አለ፡፡ ነገር ግን ምርጫው እንዴት ነው? የሚመጣውንም ሃላፊነት መቀበል የግድ ነው፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ ማመዛዘንን የሚጠይቅና ሃላፊነትን የሚሰጥ ነው፡፡ ይኸውም አንድ ሰው አንድን ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ውጤቱን ማሰላሰልና ከግብረገብ አንጻር ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ውሳኔው ግብረገባዊነትን መከተል ከሆነ በኋላ ሊደርስበት የሚችለውን የደመነፍሳዊ ፍላጎት ነጻነት ማጣት አስቀድሞ ማወቅና ለዚያ መዘጋጀት አለበት፤ ውሳኔው ኢ-ግብረገባዊ ድርጊትን ወይም ባህሪን መፈጸምም ከሆነ በማኅበረሰቡ ሊደርስበት የሚችለውን ጫና አስቀድሞ ማሰብና መወሰን አለበት፡፡

### የሰዎች ግብረገባዊ ጽናት

ይህ ጽንሰ ሃሳብ የሚያተኩረው አንድ ሰው ግብረገባዊ መርሖችን እስከምን ድረስ ታግሶ እንደሚፈጽም ነው፡፡ ይህ ማለት በመልካምም ይሁን በመጥፎ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ቢወድቅ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለግብረገባዊነቱ እንጂ ላስገዳጁ ስሜት ወይም ሁኔታ አይደለም፡፡ ለዚህም ኅሊናው የስራውን ግብረገባዊነትና ኢ-ግብረገባዊነት ያረጋግጥለታል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች አንዳች ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝ እድል ቢያገኙ ያ የዕርስዎ ጥቅም ግን ሌላውን የሚጎዳ ቢሆን የትኛውን ይመርጣሉ? በአስገዳጅ ሁኔታዎች ውስጥ ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶችን ላለመፈጸምዎስ ምን ያህል ዕርግጠኛ ነዎት? የሚሉትን ጉዳዮች የሚያሳስብና ለኅሊናችን እንድንገዛ የሚገፋ ሃሳብ ነው፡፡

### የሰው ባሕርይና ጠባይ

ልክ መልካምና እኩይ ድርጊትና ምግባር ተብለው እንደተገለጹት ሃሳቦች ሁሉ የሰው ልጅ ባሕሪውና ጠባዩ ለግብረገባዊነቱ ማሳያ ናቸው፡፡ ከውስጣዊ ማንነቱ ዋንኞቹ የሆኑት ባሕሪይና ጠባይ በጊዜና በሁኔታዎች ለውጥ ሊለዋወጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ባሕሪውን የሚያገኘው ከአካባቢው እንደመሆኑ መጠን እርሱም ለአከባቢውና ምንነቱ አስተዋጽኦን ያደርጋል፡፡ የሰው ባሕሪይና ጠባይ ያለውን ግብረገብ ተቀብሎ የሚኖር ብቻ ሳይሆን ወደ ተሻለና የላቀ ወደሚባለው የግብረግብ ደረጃ የሚያደርስ መሆን አለበት  በሚለው ጉዳይ ዙሪያም ያጠነጥናል፡፡ ግብረገባዊ ጉዳዮችን ስንመረምርም ያለውን ግብረገብ ከመመርመርና ከመኖር ይልቅ የላቀ ግብረገብ የምናዳብርበትን ጽንሰ ሃሳብ ማዳበር ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

## ኅሊና

ኅሊና የሚለውን ሃሳብ ከነ3ዙ ወክሎ የቀረበ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው ግብረገባዊ መርሖችን እንዲፈጽም የዚህን ተቃራኒ ካደረገ ደግሞ እንዲጸጸትና አካሄዱን እንዲያስተካክል የሚመራው የግብረገብ ማዕከል ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ድርጊት ትክክልና ስህተት፣ ተገቢና የማይገባ ብሎ መመሪያና የምናደርግበትን ቅጥ የሚያበጀው ኅሊና ነው፡፡ ይህም በተቻለው አቅም ውጫዊው ድርጊቱና ውስጣዊው ማንነቱ ተመጣጣኝ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለውም ከአካባቢያዊ ግንዛቤና ከውስጣዊ ስሜት በሚጠራቀም ዕውቀት አማካኝነት ነው፡፡ ንጹህ ኅሊና ያለው ሰው ማለትም መጥፎ ነገር ከማሰብ፣ ከማድረግና በአጠቃላይ ሰዎችን ከሚጎዱና ከሚያሳዝኑ ነገሮች የራቀ ሲሆን ነው፡፡

## የአካባቢ ጫና

በሰው ልጅና በሚኖርበት አካባቢ መካከል ውስብስብና ጥብቅ ግንኙነት እንዳለ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ አካባቢ ስንል በዚህ ውስጥ የሚነሱት፡- በተፈጥሮ የሚገኙ ማንኛውም ነገሮችና ክስተቶች ናቸው፡፡ አካባቢ ተፈጥሯዊና ማኅበራዊ ነገሮችን ሁሉ ጠቅልሎ የያዘ፣ በሰው ላይም የተወሰነ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል ነው፡፡ በዚህ  ውስጥ የሰው ማንነትና ባህሪ በከፊል በራሱ እንቅስቃሴ፣ በከፊል ደግሞ በአካባቢ ተፅዕኖ ይወሰናል፡፡ አካባቢ ለሰው ልጅ ውጫዊ ሁነት ቢሆንም በውስጣዊው ማንነቱ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖም አለ፡፡ ባህሪውን ከመግራት አንጻርም አካባቢ አቅም አለው፡፡

## የግብረገብ ልዩነቶች

እንደየማኅበረሰቡ እምነትና ስርዓት የተለያዩ ግብረገቦች አሉ፡፡ በአንዱ ማኅበረሰብ ተቀባይነት ያለው ግብረገብ በሌላው ማኅበረሰብ ተቀባይነት የሌለውና ኢ-ግብረገባዊ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰው ልጅ የአካባቢው የማኅበረሰቡ ውጤት ነው ተብሏል፡፡ ስለዚህ ሊያስብም፣ ሊፈርድም የሚችለው እንደየራሱ ግብረገባዊ እሴት ነው፡፡ የዚህ ግብረገባዊ እሴት መለያየት ደግሞ አቋሙ የተለያየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ አንድን ድርጊት ትክክል፣ ወይም ስህተት የሚያደርጉት የጋራ ባህሪያት (በሁሉም ቦታ) የሉትም፤ ታዲያ ይህን ልዩነት ልናስታርቅ የምንችለው እንዴት ነው? የጋራ የሚባል ግብረገብ የለም፤ ስለዚህ ግብረገብ የግድ ሊሆን አይችልም የሚሉትን ጉዳዮች ይዞ የሚመረምር ነው፡፡

**ወርቃማ የግብረገብ ሕጎች**

በላይኛው ንድፈ ሃሳብ የተነሳውን ግብረገብዊ እሴቶች እንደየአካባቢው የመለያየትን ጉዳይ ለማስማማትና የጋራ ግብረገብን የመፍጠር (የመለየትን) ጥናት ለማካሄድ የሚረዳ የንድፈ ሃሳብ አይነት ነው። ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ ሰዋዊ ባህሪ ስላለን ብቻ ሊፈጠሙ የሚገቡ፣ "ወርቃማ የግብረገብ መርሖች" የሚባሉትን ያስቀምጣሉ።

> *1 ለራስዎ እንዲደረግልዎት የሚሹትን አያያዝ ለሌሎችም አድርጉላቸው። (ሲግዝም)፣ 2 ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉልዎ የሚፈቅዱትን ነገር ሁሉ ለሌሎችም አድርጉላቸው። (የናዝሪቱ ኢየሱስ)፣ 3 ለስርስዎ የሚያስጠላዎትን ነገር ወገንዎ በሆነው ሌላው ሰው ላይ አይፈጽሙ። (ሂለል)፣ 4 ቢፈጸምብዎ ሊጎዳዎ የሚችልን ማንኛውም ዓይነት ድርጊት በሌሎች ላይ ፈጽሞ አይፈጽሙ። (ሂንዱይዝም)፣ 5 ሌሎች እንዲያደርጉብኝ የምፈልገውን ነገር እኔም ለሌሎች ማድረግን እፈቅዳለሁ። (ፕሌቶ)፣ 6 ለራስዎ በጎ ያልሆነውን ነገር በሌሎች ላይ አያድርጉ። (ዞርይስትራንዝም)፣ 7 በደስታና በሐዘን ጊዜ ለራሳችን የምናደርገውን ለሌሎች ፍጡራን ሁሉ ማድረግ አለብን። በራሳችን ላይ እንደ ጥቃት ያሉ ነገሮች ቢፈጸሙብን እንደሚጎዱነወ ሁሉ እነዚህ ድርጊቶች ሌሎችን ም የሚጎዱ ስለሆነ ከመፈጸም መታቀብ አለብን። (ጂይኒዚም)፣ 8 በእርስዎ ላይ ቢፈጸም ሊያሳምምዎ (ሊጎዳዎ) በሚችል ነገር ሌሎችን አይጉዱ። (ቡድሃ)፣ 9 እንዲደረግብዎ የማይፈልጉትን (የማይፈቅዱትን) ነገር በሌሎች ላይ አያድርጉ። (ኮንፊዩሽስ)* (ጠና፣ 2008፡ 194-197)

እነዚህ መርሖች ምንም እንኳን ከዘጠኝ ሰዎች አንደበት ቢወጡና እራሳቸውን ችለው ቢቀመጡም ዋና ነጥባቸው በራስህ ላይ ሊደረግ የማትሻውን ነገር በሌሎች ላይ አታድርግና አንተ ሊደረግልህ የምትወደውን ነገር ለሌሎች አድርግ በሚሉ መርሖች ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው። ጠና (2008፣ 161) እነዚህ ወርቃማ መርሖች አለማቀፋዊ ግብረገቦች ተብለው ለተቀመጡት መርሖችም መፍለቂያ ናቸው። የነዚህ ግበረገባዊ እሴቶች መፈጸምም መልካም ሕይወትን የመፍጠሪያና የማግኛ ቁልፎች ናቸው። እነዚህን ጽንሰ ሃሳቦች እንደየ አስፈላጊነታቸው እየቀያየርኩ በመጠቀም የአዳም ረታን የተመረጡ ታሪኮች ዲኮንስትራክሽናዊ በሆነ ንባብ የምተነትን ይሆናል።

### 2.1.2. ግብረገብ እና ደመነፍስ

የተፈጥሮና ባህል ግጭት ተብሎ በሚቃኘው በዚህ ጥናት ውስጥ የሚዳሰሱት ደመነፍስና ግብረገብ ናቸው፤ ምክንያቱም ተፈጥሮ የሰው ልጅ በተፈጥሮው የሚኖረውን ደመነፍሳዊ ባህሪ ይወክላል። ነገር ግን በአከባቢው ከሚኖሩ ተፈጥሮዎች ጋር የሚኖረው ቁርኝት መቃኘቱ ስላልቀረ ተፈጥሮ ከደመነፍስ ሰፍቶ አገልግሎት ላይ ውሏል። "‹ባህል› እና ‹ፍትሀዊነት› ሁለቱም የግብረገብ መሰረታዊ መደቦች ናቸው። የግብረገብ እና ሌሎች እሴቶች የባህልን ፍሬ ትርጓሜ ይሰጣሉ።... ባህል በተለያየ መንገድ ፍካሬ ሊሰጠው ይችላል። በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በመልክአ ምድራዊ አሰፋፈር፣ በማኅበረ ኢኮኖሚ አወቃቀር፣ በልማዳዊ ባህሪ፣ በሚት እና በመሳሰሉት።" Lind (1995, 3)

የLind ገለጻ እንደሚያመለክተው ባህል ሰፊ በመሆኑ ምክንያት በተለያዩ ጉዳዮች ሊገለጽ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ግብረገብና ባህል ያላቸውን ውስብስብ ቁርኝት እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *The relationship between morality and culture has been conceptualized in many different ways by psychologists, social scientists, and philosophers. These conceptualizations reflect different definitions of morality and of culture as well as different perspectives on the extent to which morality is defined by or is independent of cultural norms. (Killen and others, 2015፡ 161-162)*

የአጥኚዎቹ ብያኔ እንደሚጠቁመው ግብረገብና ባህል በተለያዩ መስክ ባለሙያዎች ሊጠና ይችላል። በፈላስፋዎች፣ በማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችና በሥነ ልቡና ጠበብት ተመርምሯል። እኔም አንዱ አካሉ የሆነውን የፍልስፍናውን ጠገግ በመያዝ ባህልን በሰፊነቱ ወደ ግብረገብ አውርጄ፤ በግብረገብ ጠባብነት ደግሞ የባህልን ስፋት ተጠቅሜ፣ በርእሰ ጉዳዬ ላይ ጥናቴን አደርጋለሁ።

ደመነፍስና ግብረገብ ያላቸውን ተራክቦ ለመዳሰስ ሁለት ጽንፎችን አነሳለሁ። አንደኛው የሰው ልጅ በተፈጥሮው ደመነፍሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት ስለሚጥር የአውሬነት ባህሪ አለው፤ ይህንን ሊያስቆመው የሚችለውም ግብረገብ ነው ብሎ ሲያምን፣ ሌላኛው የሰው ልጅ በነጻ ፈቃዱ ግብረገባዊ ድርጊቶችን የመፈጸም ደመነፍሳዊ ባህሪ አለው። ግብረገብም ደመነፍሳዊ ፍላጎትን

የማሰር ሳይሆን ግዴታን የመወጣት ሂደት ነው የሚል ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ጽንፎች እንዲያሳዩ የመረጥኳቸው ፈላስፋዎችም ቶማስ ሆብስና ኢማኑኤል ካንት ናቸው፡፡

ኢማኑኤል ካንት ግብረገብን ትኩረት ሰጥቶ የመረመረ ፈላስፋ ሲሆን ዓላማውም አለም አቀፋዊና ጽኑ ግብረገብን መፍጠር ነበር፡፡ (የግብረገብን መሰረትም ለመረዳት ምርመራ አድርጓል፡፡) ግብረገብ መልካም ባህሪ ስላለን ሳይሆን በጎ ወይም ነጻ ፈቃድ ስላለን የምንከውነው ምግባር ነው፡፡ አንድ ሰው ግብረገባዊ የሚሆነውም በነጻ ፈቃዱ የመረጠውን ግብረገብዊ እሴት የመተግበር ግዴታውን ሲወጣ ነው፡፡ ስለዚህ የግብረገብ መሰረቱ ነጻ ፈቃድ ነው፡፡ የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ሁል ጊዜም እና በየትኛውም ስፍራ መገኘት ይችላል፡፡ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ክስተት ይህን ባህሪውን ሊቀይረው አይችልም፡፡ ሌሎች ነገሮች ግን በተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ፡፡ ስለዚህም ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶች ይፈጸማሉ በማለት ያትታል፡፡ (Archie, and Archie, 2003፡ 153-157)

እንደ ካንት ገለጻ የሰው ልጅ በደመነፍሱ ራሱን ለሕግ የማስገዛት ዝንባሌ አለው፡፡ በነጻ ፈቃዱ ላለመመራት እንዳይወስንም ያስገድደዋል፡፡ የእኩይ ባህሪ ባለቤት የሚሆን ሰው ደመነፍሳዊ ክፋት ስላለው ወይም ደመነፍሳዊ መልካምነት ስላለው ሳይሆን ግዴታውን ሲወጣ አስቀድሞ የሚመጣውን ውጤት ባለማስተዋል ነው ተግባሩን የሚያከናውነው፡፡

ቶማስ ሆብስ (1651፡ 9-11) የሰው ልጅ የሚሻውን ነገር ለማግኘትና የሚጠላውን ነገር ደግሞ ለማስወገድ ግብረገብን ባልተማረበት ዘመን በአእምሮ ብልጠቱ ወይም በአካላዊ ጥንካሬው ይጠቀም ነበር፤ ይህም የሰውን ልጅ ሕይወት አስቀያሚና አጭር የጦርነት አውድማ ያደርገዋል፡፡ ሁሉም ሰው፣ ወይ በብልጠት፣ ወይ በጉልበት አቻ የሆነ ሃይል ስላለው አንዱ ለሌላው አይተኛም፡፡ ይህንን የኑሮ ሂደት ነው ተፈጥሯዊ ኑባሬ ብሎ የሚጠራው፡፡ ራሱን ከአደጋ ለመጠበቅ እና መጠን አልባ ለሆነው ፍላጎቱ ዕርካታን ለማግኘት በሚደረግ ፍትጊያም ግብረገባዊነትን እየለመደ ወይም ሕግን እየተማረ ሄደ፡፡ ለሆብስ ግብረገብ ለሰው ልጅ በየትኛው መንገድ ቢሄድ ችግር ሳያጋጥመው ፍላጎቱን ማርካትና የሚጠላውን መሸሽ እንደሚችል የሚመራው መንገድ ሲሆን፣ የሚማረውም በዙሪያው ከተጋረጡበት ችግሮችና ከእርሱ ከራሱ ፍላጎትና አልጠግብ ባይነት ነው፡፡ የግብረገብ መሰረቱም ይህ ነው፤ እንጂ ነጻ ፈቃድ የሚባል ነገር አይደለም፡፡ (Hobbes, 1651፣ ጠና፣ 2008)

በሆብስ እምነት መሰረት የሰው ልጅ ለኢ-ግብረገባዊነት የተጋለጠ ተፈጥሯዊ ባህሪ አለው፡፡ ይህ ባህሪው አይሎ ከወጣ ወደ ቀድሞው የጦርነት ሕይወቱ ስለሚመለስ ባህል መጠናከርና ሊቆጣጠረው መቻል አለበት፡፡

ይህ ጥናት ከሁለቱ ፈላስፋዎች የተቀዳ ማሕቀፍን አበጅቶ ይጓዛል፡፡ ሆብስ የሚሰጠውን የደመነፍስ ብያኔ ይቀበላል፡፡ እንዲሁም የካንትን በነጻ ፈቃድ ግብረገባዊ እሴቶችን የመተግበር ወይም ግዴታን የመወጣት ጽንሰ ሃሳብ ያምናል፡፡ በሁለቱ መካከል ማለትም በደመነፍስ ፍላጎትን ለማርካት ማስገደድ እና በግብረግብ ግዴታን መወጣትና ሃላፊነትን መውሰድ መካከል በሚያደርጉት ፍትጊያም ገጸባህሪያቱ የሚኖራቸውን ሰብዕና፣ ባህሪና ድርጊት ይቃኛል፡፡

## የተፈጥሮና የባህል ግጭት ዘላቂ የማይሆነው ለምንድን ነው?

የተፈጥሮና የባህል ግጭት ዘላቂ አይደለም፡፡ ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የተለያዩ የስሜት ህመሞችን ስለሚያመጣ ነው፡፡ ከዚያ ውስጥ አንዱ "ኦሲዲ" የተሰኘው የአእምሮ መዛባት ህመም ማጋጠም ነው፡፡ ይህ ህመም አንድ አደጋ በሰዎች ላይ ከማድረስ ወይም በራስ ላይ እንዳይደርስ መስጋትና ለዚህ ስጋት አስቀድሞ መልስ መስጠት ነው፡፡ ከተማ አድማሱ "ስሜትና አእምሮ" (2009፡ 148-198) እንደሚያስረዱት የህመሙ ተጠቂዎች ከጭንቀታቸው ውስጥ አንዱ "ባሕል፣ ልማድ፣ ሞራላዊ፣ ወይም የሃይማኖትን መርሆዎች ከመጣስ ስለመጠበቅ ማሰብና መጨነቅ" ነው፡፡ (ዝኒከማሁ፣ 326) ይህ እንደሚያመለክተው ግጭት ውስጥ በሚገቡ ጊዜ ይህ ስለሚያሳስባቸው ወደ አእምሮ መዛባት ወደ ከፋ ደረጃ ስለሚያደርሳቸው ከዛበፊት መከላከያውን ማበጀት ይሻሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ድብርት ነው፡፡ በአካባቢያዊ ጫና የሚፈጠረው ድብርት በሁሉ ነገር ፍላጎት ማጣትና ተስፋ መቁረጥን የሚያመጣ ስለሆነ የከፋ ደረጃ ላይ ከደረሰ ደግሞ ራስን ማጥፋትንም ይጨምራል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ህመሞች በፍጥነት ምላሽ ከተሰጣቸው ሊድኑ የሚችሉም ናቸው፡፡

በአእምሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ስሜቶች ሲበዙ አእምሮ ተረጋግቶና አመዛዝኖ ውሳኔን እንዳያስተላልፍ ያደርጉታል፡፡ የተለያየ ትዕዛዝን እንዲያስተላልፍና ሆርሞኖች እንዲመነጩ ያደርጋል፡፡ ይህም የማምለጥን ወይም የመከላከልን ርምጃ እንድንወስድ ያደርጋል፡፡ በዚህ እርምጃ ጊዜ በሚፈጠሩ ኬሚካሌችና ሆርሞኖች ከዘወትራዊው ጉልበት የበለጠ ሃይለኛና ፈጣን እንድንሆን ያደርገናል፡፡ ስለዚህ ያልተረጋጋ ወይም ብዙ ስሜቶችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ ሰው  የከፋ አደጋ ሊያደርስ ይችላል፤ ወይም አላስፈላጊ ድርጊት ሊደረግ ይችላል፡፡

### 2.1.3. ግብረገብ እና ሥነ ጽሑፍ

በቀድሞው ዘመን ሁሉም መስኮች የየራሳቸውን ጉዳይ ብቻ በመመርመር ለሌሎች መስኮች ትኩረት ሳይሰጡ ቆይተዋል፡፡ (ስለ ሌላው መስክ አያገባኝም የሚል አስተሳሰብና አሰራርን ሲከተሉ ነበር፡፡) አሁን ባለንበት ዘመን ግን የተለያዩ መስኮች በጋራ በመጠናት ልዩ ልዩ ግኝቶችን አምጥተዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከተለያዩ መስኮች ጋር ተጣምሮ በመጠናት ውጤታማ በመሆን በዋነኛነት የሚጠቀሰው ሥነ ጽሑፍ ነው፡፡ ቴዎድሮስ (2001) እንደሚያስረዱት ሥነ ጽሑፍን ብቻውን ከማጥናት ይልቅ ከተለያዩ መስኮች ጽንሰ ሃሳቦች ጋር አቆራኝቶ መመርመሩ የተሻለ ውጤትና እድገት እያስገኘለት እንደሆነ የግብረገብ ጉዳይ መነሳት ከጀመረ በኋላ ከሥነ ጽሑፍ ጋር እንዴት እንደሚሄድና በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ግብረገብ የሚኖረውን ሚና በተመለከተም የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ ግብረገብና ሥነ ጽሑፍ ያላቸውን ጥንታዊ ግንኙነትም ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

“Literature - morality relation has remained a point of vital critical debate since the ancient civilization. In the twentieth Century this question has continued ton inspire critical debate despite phenomenal decline in religious and moral aspect of life.” (Karim, 2012፡ 186) እንደ Karim ገለጻ የሥነ ጽሑፍና ግብረገብ ቁርኝት ጥንታዊ የስልጣኔ ዘመን ከሚባለው ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካለንበት እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንኑ ሃሳብ ጠቅላይ ከሆነው ሥነ ጥበብ ጋር በማቆራኘት ያላቸውን ግንኙነት “The issue of morality in art has always been very strong in the field of aesthetics. Nevertheless, it remains a nebulous and undecided issue.” (Migliavacca 2011፡ 295) በማለት ይገልጹታል፡፡ የጊዜው ርዝመት የሰፋ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ግን ይህ ቁርኝታቸው ተጠንቶ እንዳላለቀና ውስብስብ እንደሆነም አያይዘው ገልጸዋል፡፡ አንድም ግብረገብ በሥነ ጽሑፍ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ምንድን ነው? አንድም ሥነ ጽሑፍ በግብረገብ ውስጥ ያለው ሚና ምንድን ነው? አንድም አንባቢ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ምንድን ነው? እንዴትስ ግብረገብና ሥነ ጽሑፍ መቅረብ አለባቸው? በሚሉ ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

*Studies in culture and communication* በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው በ1972 አካባቢ ውስጥ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ግብረገባዊ “ሰቆቃ” (panics) የያዙ ስራዎች እንዲተላለፉና ማኅበረሰቡ ለሚያደርገው ድርጊት (ግብረገባዊም ሆነ ኢ ግብረገባዊ) ሃላፊነትን

መውሰድ እንዲችል፣ ይህም ማኅበረሰቡ ግብረገባዊ እንዲሆን ይረዳ ዘንድ ይጥሩ የነበሩ ሰዎችን በመጥቀስ ተገልጿል Fiske, E.d. (2006፡ 186-87)፡፡ ማኅበረሰቡ ሰቆቃውን እያሰበ ባህሉን በግብረገብ እሴቶች የተሞሉ እንዲያደርግ ይረዳዋል የሚል እምነት ስለነበር የሕይወት መንገዳቸውን ከዛ ይቀዳሉ፡፡ ይህንኑም ለባህል ማጥኛነት ተጠቅመውታል፡፡ ከስቃይ የመማር አይነት ዘዴ አለው፡፡

በ15ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ16ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በእንግሊዝ "ሞራሊቲ ፕሌይ" የተሰኘ የድራማ ዘውግ ነበር፡፡ ይህ የድራማ አይነትም በገጸ ባሕርያቱ አማካይነት ግብረገባዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ወክሎ ሰውን ሥነ ምግባር ለማስተማር፣ በሃይማኖት ለማረቅና ከጥፋት ለመታደግ የሚጥር (የቤዛነት ስራ የሚሰራ)ና እጅግ ሃይማኖታዊ የሆነ እንደነበር Abrams (1999, 166) ይገልጻሉ፡፡

ስለዚሁ የድራማ ዘውግ *A Dictionary of Literary and Thematic Terms* በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥም "A form of English drama of the 15th and early 16th centuries in which characters exemplify moral or religious abstractions." (Quinn, 2006፡ 268) በማለት "ሞራሊቲ ፕሌይ" ገጸባህርያቱን ግብረገባዊነት በማላበስ ማኅበረሰቡን ለማስተማር የሚሰራ የድራማ አይነት እንደሆነ ከላይኛው ሃሳብ ጋራ የሚመሳሰል ገለጻ ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ ግብረገብ በትምህርት ቤት ደረጃ ከመሰጠቱ ሌላ፣ በሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ግብረገብና ልብወለድ ከፍተኛ ቁርኝት ነበራቸው፡፡ በተለይም የመጀመሪያዎቹ ልብወለድ ስራዎች በግብረገባዊ ጉዳዮች የተቃኙና የአንባቢን ሥነ ምግባር ለመቅረጽ የሚጥሩ እንደነበሩ Ttena (2008) ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያነት በሰራው ጥናት ውስጥ ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ከዘርዓይ ያዕቆብና ከወልደሕይወት ፍልስፍና ጀምሮ፣ በግእዝ ቋንቋ ከውጭ ቋንቋ የተተረጎሙትም በግዕዝ የተጻፉትም ስራዎች፣ እንዲሁም በመጀመሪያው አካባቢ የሚመደቡት የረጅም ልብወለድ ደራሲያን ስራዎች አስተማሪና ግብረገብን መቅረጽ ላይ ትኩረት ያደረጉ እንደነበሩ ገልጿል፡፡

"ግብረገብንና ሥነ ጽሑፍን በማጣመር ማጥናት የጀመረው ማቲው አርኖልድ ነው፡፡ ማቲው አርኖልድ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ጸሐፊና ሃያሲ ነው፡፡ ግብረገብን በግል ከመልመድና ከመተግበር ይልቅ በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲሰጥ ያደረገ ሲሆን ይህም የግብረገብ ዕውቀት ከግለሰባዊነት ወደ ሕዝባዊነት እንዲያድግ ረድቶታል፡፡" (Karim, 2012, 187) ምንም እንኳን

አርኖልድ ግብረገብን ለማስተማር ይረዳው ዘንድ ሥነ ጽሑፍን ቢጠቀምበትም ይህ ተግባሩ ግብረገብንና የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዘውጎችን አቆራኝቶ ለማጥናት በር ከፍቷል፡፡ በPantić, (2006፡ 402) ውስጥ ይኸው ሃሳብ በተመሳሳይ መልኩ ተገልጿል፡፡

የአርኖልድ ንድፈ ሃሳብ መሰረቱን ያደረገው ሥነ ጽሑፍ አንባቢ ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላል፤ ስለዚህ በሥነ ጽሑፍ አማካይነት መልካም ሥነ ምግባርን ወይም ግብረገብን መቅረጽ እንችላለን በሚለው ሃሳብ ላይ ነው፡፡ እንዲሁም ሥነ ምግባር በዘመኑ (በአሁን ዘመንም አሉ፡፡) የሃይማኖተኞች ብቻ ጉዳይ ተደርጎ ይቆጠር ስለነበር፣ በሁሉም ሰው ዘንድ የሚሰራና የሚያስፈልግ እንጂ ከሃይማኖት ጋር የታከከ ብቻ እንዳይደለ ለማሳወቅ ጥሯል፡፡ ለዚያም ነው ግብረገብን ከሃይማኖታዊነት ወደ ሕዝባዊነት ቀይሯል የሚባለው፡፡ የማቲው ትምህርት ስርዓትን የተከተሉትም የሱን ንድፈ ሃሳብ ተመርኩዘው ለሥነ ጽሑፍ ትምህርት መሳሪያነት እንደተገለገሉበትም ይገለጻል፡፡

በርግጥ ቀደም ሲል የተለያዩ ፈላስፋዎች ግብረገብና ሥነ ጽሑፍ ስላላቸው ተራክቦ ሃሳቦችን የጠነሰሱ ቢሆንም በንድፈ ሃሳብነት ተጠቅሞ ማሕቀፍን ለመስራት ግን አርኖልድንና እርሱን ተከትለው የመጡትን ምሁራን መንገድ መከተሉ አዋጭነት አለው፡፡ Eileen John, (2010) ግብረገብ በሥነ ጽሑፉ ላይና በአንባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ከመመርመር ይልቅ ግብረገብን እንደ ንድፈ ሃሳብ ወይም ጽንሰ ሃሳብ አድርጎ ቴክስቴን መተንተንና ፍካሬን ማበጀት አዋጭነት እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

በሃገራችን በግብረገብ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች (ጥናቶችና መጻሕፍት) ተበራክተዋል፡፡ በመጽሐፍ ደረጃ ያለውን ስናይ አንድም በሃገራችን ሥነ ምግብርና ግብረገብ ጉዳይ ላይ ዋና ትኩረታቸውን አድርገው የተሰሩ፣ አንድም በትርጉምና በንኡስ ጉዳይነት የተሰሩ ናቸው፡፡ ግብረገብን እንደ ጽንሰ ሃሳብና ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ በመጠቀም ልብወለድን መመርመርም ተጀምሯል፡፡ ይህም ሥነ ጽሑፍን በተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች መሄስ ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ ይህ ጥናትም ይህንኑ መንገድ በመከተል “በይነ ዲስፕሊናዊ” ንባብን ያደርጋል፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ከዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይና የማንበቢያ ዘዴ ጋር ቅርበት ያላቸው መጻሕፍት፣ ጥናታዊ ጽሑፎችና ጥናታዊ መጣጥፎች ተዳስሰዋል፡፡ ግብረገብን ከሥነ ጽሑፍ ጋር በማዋሀድ የተደረጉ ጥናቶች ሊገኙ የቻሉት በ“የውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት

ክፍል” ውስጥ በመሆኑ በዚህ ትምህርት ክፍል በግብረገብ ጽንሰ ሃሳብና ዲኮንስትራክሽናዊ የማንበቢያ ዘዴ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

በመጀመሪያ የሚታዩት መጻሕፍት ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም ስለ ሰው ሥነ ምግባር ከፍልስፍና አንጻር፣ በቀጥታና በስፋት ያነሱ በመሆናቸውና ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው የመጀመሪያነትነን ደረጃ አግኝተዋል፡፡ በመቀጠል ለሦስተኛ ድግሪ፣ ለሁለተኛ ድግሪ እና ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች የተዳሰሱ ሲሆን በመጨረሻ በውጭ ጸሀፍት የቀረቡ መጣጥፎች ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያው መጽሐፍ የጠና ደዎ *ሰው፣ ግብረገብና ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች* የተሰኘው ሲሆን መጽሐፉ የሥነ ምግባርንና የግብረገብን ምንነት፣ ግንኙነት፣ አስፈላጊነትና የኢትዮጵያውያን ግብረገብ ምን እንደሆነ ይዳስሳል፡፡ በመጀመሪያ የፍልስፍናን ምንነት ብያኔዎችን በማስቀመጥ ተነስተው በደረጃ የሥነ ምግባርን፣ የግብረገብን ምንነት፣ መመርመሪያ ዘዴዎች፣ ለማጥናት የሚስማሙ ንድፈ ሃሳቦችን ከዘረዘሩ በኋላ በተለያዩ ጽንሰ ሃሳባዊ መሰረቶች ላይ በመመርኮዝ ይበጃል ያሉትን ራሳቸው የሚስማሙበትን የግብረገብ ንድፈ ሃሳቦች አስፍረዋል፡፡ መጽሐፉ የተዘጋጀው የተለያዩ ጥናቶችን ተመርኩዞ እንደሆነ ጸሓፊው ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ በኋላ እንደ ኢትዮጵያዊ (አሁን ባለንበት) ዘመን ግብረገብ የተዘነጋ ጉዳይ እንደሆነና ይህንንም ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ምን ቢደረግ ይሻላል? የሚለውን ጉዳይ በማንሳት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ እንደ ኢትዮጵያዊ የጋራ ግብረገብ እንዳለና የታሪክ ክስተቶች እንደሚመሰክሩት በብዛት ብልሹ የሆኑ ግብረገቦች ባለቤት እንደሆንን ነው፡፡ ወንድማማችነት፣ ቅድሚያ መሰጣጣት፣ መተዛዘን የመሳሰሉ ግብረገቦች ቢኖሩም እንኳ በየዘርፉ የሚገኙ ሥነ ምግባሮችን አለማክበር፣ ተንኮል፣ እርስ በርስ መቀናናትና ለማጥፋት ማሴር፣ ሰዓትን በአግባቡ አለመጠቀም፣ ፊላጭ ቆራጭነት፣ ስንፍና፣ ለነገው ባለማሰብ ዛሬ ተግቶ አለመስራትና ልመናን የመሳሰሉ እኩይ ባህሪያት እንዳሉና እነዚህም የልማት ጠር ስለሆኑ ሊወገዱ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ በርዕሱ ለማየት እንደሚቻለው ግብረገብ በተለየም ለዘመናችን (ለሀገራችን) እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ ሊተኮርበት ይገባል፡፡

መጽሐፉ በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰ ሲሆን ይህ ጥናትም መሰረቱን በዚህ መጽሐፍ ላይ አድርጎ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥናት ይህ መጽሐፍ እንደ ቋሚ የንድፈ ሃሳብ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የተመረጠበትም ምክንያት አንድም፡- ሰፊ ስራዎችን ዳስሶ ለሃገራችን ግብረገባዊነት

የተመቸ ንድፈ ሃሳቦችንና ጽንሰ ሃሳቦችን የያዘ፣ ሙያዊ ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ስራ በመሆኑ ነው። አንድም፡- በእናት ቋንቋ የተገኘ መረጃ ሃሳቡን ለመረዳትና ለመጨበጥ ከተለመዱ ቋንቋዎች (በልምድ የሚገኙ/ አፍ መፍቻ ቋንቋ ካልሆኑቱ) በተሻለ ተመራጭ ስለሆነ ነው።

በሁለተኛነት የሚነሳው መጽሐፍ፡- የተክለ ጻድቅ መኩሪያ *የሰው፡ ጠባይና፡ አብሮ፡ የመኖር፡ ዘዴ።* 1943 ዓ.ም ሲሆን፣ መጽሐፉ በ ደ ላብሩዬርን፣ *ካራክተርስ* በተሰኘው ጽሐፍ ላይ በመመርኮዝ ሁለት ጉዳዮችን በዋናነት አንስቷል። የመጀመሪያው፡- ምድራዊና መንፈሳዊ ሰው ብለው ያነሷቸው ሁለት አይነት ፍልስፍናዎች ማቴሪያሊስት እና ስፐሪቹዋል እሳቦቶችን በማንሳት የሰው ልጅ ባህሪያት ምን እንደሚመስሉ በመዘርዘር በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚቀመጡትን የሰው ልጅ ባህሪያት አይነቶች በንጽጽር አቅርበዋል።

በመቀጠልም የተለያዩ ባህሪያትን በማንሳት በግል የሚያውቋቸውን ሰዎች፣ በታሪክ የሚታወቁ ነገስታትንና በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የሚገኙ ግለሰቦችን ታሪኮች፤ ከሃገራችንም ከውጪም እንደ ምሳሌነት በመጥቀስ ጉዳዩን በተጨባጭነት ለማስረዳት፣ ወይም ረቂቁን የሰው ልጅ ባህሪይ በሚያውቋቸውና ይህ ባህሪ ይመጥናቸዋል ብለው ባሰቧቸው ሰዎች ውስጥ ግዘፍ እንዲነሳ ለማድረግና ሃሳባቸውን ለአንባቢ ግልጽ ለማድረግ ጥረዋል።

በሁለተኛነት፡- ያነሱት ሃሳብ አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ ምን አይነት ባህሪ ሊኖረን እንደሚገባና እንደየአውዱ ምን አይነት ምግባርና ባህሪ ማሳየት እንዳለብን የሚጠቁሙ ዝርዝር ጉዳዮችን ነው። በዚህም ውስጥ "የበላይና የበታች፣ ባልና ሚስት" አንዱ ላንዱ ምን አይነት እንክብካቤና አጠባበቅ ሊያደርግለት እንደሚገባ የተለያዩ የስነ ልቡና እና የፍልስፍና መጻሕፍትን በማጣቀስ ገልጸዋል። በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ሁሉም ሰው ሊኖረው ይገባል ብለው ያመኗቸውን ባህሪያትና አመለካከቶችም ዘርዝረዋል።

ከአጠቃላይ የጹሑፉ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ከላይ ከተነሱት እሳቦቶች ውስጥ መንፈሳዊ የሚለውን አቋም የሚደግፉ ናቸው። የሰው ልጅ ሁሉንም አይነት ባህሪያት ሊኖሩት ቢችሉም በምድራዊያን ባህሪያት ውስጥ የተጠቀሱት እንደ "እራስ ወዳድነት፣ ስንፍና፣ አሳበ ውሱን፣ አድር ባይ፣ ክፉ አሳቢ፣ ልበ ደንዳና" የመሳሰሉ ባህሪት ጎልተው ከወጡ ማኅበራዊ ሕይወትን ሊያደፈርሱ ስለሚችሉ የመንፈሳዊያን ባህሪያት ከሆኑት "ትጉህ፣ ለሰው አሳቢ፣ ልበ ፍንቅል፣

ቅን አሳቢ፣ አሳበ ሰፊ” ከመሳሰሉት ባህሪያት ጋር በማመጣጠን መልካም ባህሪን ማካበት ይገባል የሚል አቋም አላቸው። በመቀጠል የጥናታዊ ጽሑፍ ማሚያዎች ይቃኛሉ።

Ttena Shale. “Moral Vision on the Continuumia Tody of selected Amharic Novels.” *ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያነት* እ.ኤ.አ. በ2008 በውጪ ቋንቋዎችና *ሥነ* ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያቀረበው ይህ ጥናት የመረጣቸው የስድስት ደራሲያንን አስራ አንድ ስራዎች ነው። እነርሱም፡- 1 የሀዲስ አለማየሁ *ፍቅር እስከ መቃብር፣ ወንጀለኛው ዳኛና የልምዣት*፤ 2 የዳኛቸው ወርቁ *አደፍርስ*፤ የበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪና ደራሲው፤* 3 የተስፋዬ ገብረአብ *የቡርቃ ዝምታ፤* 4 የሲሳይ ንጉሱ *ረቂቅ አሻራ፤* 5 የፍቅረ ማርቆስ ደስታ *ኢቫንጋዲና አቻሜ* ናቸው።

ግብረገብን በንድፈ ሃሳብነት በመጠቀም በልብወለዶቹ ላይ ትንታኔን አቅርቧል። በየመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ዋና ገጸባህሪያት ሀቲቶችና የእርስ በእርስ ምልልሶች ላይ ዋና ትኩረቱን አድርጎ ፍቺን የፈለገባቸው ቢሆንም አጠቃላይ ታሪኩንና የታሪኩን መቋጫም እንደ አከርካሪ ነጥብነት ተጠቅሞበታል። በዚህም ገጸ ባህሪያቱ ግብረገባዊ ጥያቄዎችን የሚፈትኑ፣ (ከሌላ እንኳን በደሉ ባይመጣ ራሳቸውን የሚበድሉና የሚጨቁኑ)፣ ፍትህን የተጠሙ፣ አንዳንዶቹ ግብረገብ የጎደላቸው ያም ለመጨረሻቸው ውድቀት መንስኤ የሚሆናቸው፣ አንዳንዶቹ ፍትህን በመነፈጋቸውና በሌሎች ኢ-ግብረገብዊ መሆን ውድቀታቸው የሚመጣ፣ እንዲሁም ግብረገባዊ ራዕያቸው በጉጉት ያለ መሆኑን ገልጿል።

በግኝቱም ለጥናት የተመረጡት ስራዎች የሚያመሳስላቸው ጉዳይ በግብረገብ ራዕይ የተቃኙ በመሆናቸው እንደሆነና ዋና ገጸ ባህርያቱ አንድም የግብረገብን ጥያቄ በራሳቸው የሚያነሱ፣ በግብረገብ ጉድለት የብዙዎቹ መጨረሻ የማያምር በመሆኑ የግብረገብ መርሖችን ተፈጻሚነት ጥያቄ ውስጥ እንድንከተው፤ የግብረገብን የወደፊት እጣም መጠየቅ እንደሚገባ እንድንገነዘብ የሚያደርጉና በአስተማስሎ የቀረቡ መሆናቸውን ገልጿል። ልብወለድም ይህንን የግብረግብ ጥያቄ ለማንሳት፣ ለማሳሰብና፣ ራዕያቸውን ለማሳየት ምቹ “ማደሪያ” ሆኖ እንዳገለገለ ገልጿል። ለጉዳያቸው ማጠንጠኛነትና ለስራቸው ድድርና መፍጠሪያነትም ግብረገብን ይጠቀሙ እንደነበር ገልጿል።

ይህን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ግብረገብን በማሕቀፍነት፣ ልብወለድን ደግሞ በማተኮሪያነት የተጠቀመ በመሆኑ ነው፡፡ የሚለያየውም በሥነ ዘዴ፣ በማንበቢያ ስልት፣ ለማሳያነት በሚመረጡ ቴክስቶችና በሚቀርብበት ቋንቋ ነው፡፡

ሁለተኛው ጥናት በMola feleke. “Decanstructive Discourse of content as Reflected in Haddis Alemayehu’s Fikir Eske Mekabir.” በተሰኘ ርዕስ ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለሁለተኛ ድግሪ መርሃ ግብር እ.ኤ.አ. 2008 የቀረበ ሲሆን በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ ዲስኮርሶች ዲኮንስትራክሽናዊ በሆነ መንገድ እንዴት እንደቀረቡ ዳስሷል፡፡ ዲኮንስትራክሽናዊ የማንበቢያን ዘዴ ልብወለዱን ለመመርመር እንደ ንድፈ ሃሳብም እንደ መሄሻ ዘዴም ተጠቅሟል፡፡ በቴክስቱ ላይ ዲኮንስትራክሽናዊ ንባብን ማድረግ የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡

በተለይም “ጉዱ ካሳ” የተሰኘው ገጸባህሪ የሚያቀርባቸውን ሀቲቶች በማንሳት ስለ ማኅበራዊ ስርዓቱ አወቃቀር ለሚያቀርበው ትችት እንዴት ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን እንደተጠቀመ አሳይቷል፡፡ ማኅበረሰቡም ልማዱንና ስርዓቱን የሚቃወመውን ግለሰብ ቅጽል ስም ከመስጠት ጀምሮ የተለያዩ ሃላፊነቶችን እስከ መንጠቅ ድረስ በሚደርሱ ደረጃዎች በተራው ሲያገሉትና ሲገፉት አሳይቷል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን እንደተጠቀሙና አጠቃቀማቸውም የተሳካ እንደነበር ገልጿል፣ ምክንያቱም በቴክስቶች ውስጥ የሚገኝ ፍቺ በተለያየ መንገድ ሊፈለፈል ይችላል፣ ይህም ብዙ ፍቺዎችን ለማምረት ደግሞ በቋንቋ ላይ ተመስርቶ የሚሰራው ዲኮንስትራክሽን ወደር የለሽ ዘዴ መሆኑን አጥኚው ገልጿል፡፡

በግኝቱም ደራሲው ፍቅር እስከ መቃብርን ዲኮንስትራክሽናዊ ሐቲቶችን በመጠቀም እንደገነቡትና ተገቢውን ፍቺም ማግኘት የሚቻለው ይህንኑ የንባብ ስልት በማድረግ እንደሆነ፣ ሃዲስ አለማየሁ ዲኮንስትራክሽናዊ ጸሓፊ እንደሆኑ ገልጿል፡፡ ከቀመለት ዓላማ አንጻር ተገቢውን ሥነ ዘዴ በመጠቀሙ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ችሏል፡፡

ዲኮንስትራክሽናዊ ስልትን ለልብ ወለድ ማንበቢያነት በመጠቀሙ ከኔ ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ የእኔ ጥናት ግብረገብን እንደ ንድፈ ሃሳብ ይዞ የሰውን ተፈጥሮና የባሕልን ግጭትና እርቅ ለማሳየት ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን መጠቀሙ፣ ለጥናት የተመረጡት ልብወለዶች የተለያዩ መሆናቸው፣ የሚቀርብበት ቋንቋና የሚቀርብለት ትምህርት ክፍል የተለያዩ መሆናቸው የስራዎቻችን መለያያ ነጥቦች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ጥናት የWendmu Geda. "Deconstruction and Pluralist Discourse: An Analysis of Nawal, El Saadawi's novels: Woman at Point Zero and God Dies by the Nile"፣ እ.ኤ.አ 2007፣ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ፣ ለቋንቋዎች ጥናት ትምህርት ክፍል የሰራው ጥናት ትኩረቱን ያደረገው የግብጻዊቷ ደራሲ የNawal, El Saadawi. ስራዎች በሆኑት "Woman at point zero" እና "God Dies" የተሰኙ ልብወለዶች ላይ ሲሆን ከመረጣቸው ስራዎች ውስጥ ሀቲቶችን እየመዘዘ፣ ከእንስታዊ ዲኮንስትራክሽን ንድፈ ሃሳብ አንጻር ጽንሰ ሃሳቡን በመጠቀም ጥናቱን አካሂዶበታል።

የጥናቱ ማዕከል ያደረገው የዲኮንስትራክሽን ሒስ መርሖች እና በእንስታዊያን እሳቤዎች መካከል ያለውን ግንኙነት፣ በተመረጡት ቴክስቶች አማካኝነት መመርመር ነው። ይህንንም በዋናነት በቴክስቶቹ ውስጥ ባሉ በሚቃረኑና ብዙኀነት ባላቸው ተረካዎች ትርጉም ላይ በማተኮር ሰርቷል። አጥኚው የመረጣቸው ቴክስቶች ላይ ዲኮንስትራክሽናዊ ንባብ ከማድረግ ይልቅ ስራዎች እንዴት በራሳቸው ዲኮንስትራክት እንደሚሆኑ ለማሳየት ሞክሯል።

ጥናቱ የደራሲዋን ማኅበራዊ ሕይወትና ያላትን ማኅበራዊ አተያይ (ሂስ) በመመርመር ይጀምርና ወደ ስራዎቿ ይህንኑ ነጥብ ይዞ ያመራል። ስራዎቿም የመቼቱን ማኅበራዊ ስርዓት መሄስ ላይ ያተኮሩ እንደሆኑና በተለይም እንስታዊ ዲኮንስትራክሽናዊ የገጸባህሪያት (በተለይም የሴት ገጸባህሪያት) ሀቲቶችን ተጠቅማ የተመረጡትን ስራዎች "እንደሸመነቻቸው"፣ ይህንኑ ዘዴ በመጠቀም ሲነበቡም በራሳቸው እየፈራረሱና እየተገነቡ ፍሬ ነገሩን እንደሚበትኑ ገልጿል።

በግኝቱም ያስታወቀው ደራሲዋ አስባበትም ይሁን ሳታስበው ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን የታሪኮቿ (የተመረጡት) ማተኮሪያ ነጥብ አድርጋ መጠቀሟን ነው። በተጨማሪም በቴክስቶቹ ውስጥ የተስተዋለው ነገር ልክ እንደ ግል ሕይወቷ ሁሉ (ማኅበራዊ ሃያሲ እንደመሆኗ) እንስታዊ ሂሳዊ ቅኝትን የተላበሱና በብዙኀነት መርህ የተቃኙ ናቸው የሚል ነው። በዓላማው እንዳሰፈረውም ንባቡን ሲያደርግ በራሳቸው የመጀመሪያ ቅርጻቸውን እያፈረሱ አዳዲስ ቅርጽ ሲያበጁም ማሳየት ችሏል።

ይህ ጥናት ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን ለቴክስት ማንበቢያነት መጠቀሙ፣ ከተመረጡት ቴክስቶች ውስጥ የገጸባህሪያትን ሀቲቶች በዓላማ ተኮር ዘዴ እያነሳ ለትንታኔ ማመቻቸቱ፣ ዘዴውን ከልብወለድ ጋራ አጣምሮ መመርመሩ ከእኔ ስራ ጋራ ቢያመሳስለውም፤ የተመረጡት ስራዎች መለያየታቸው፣ ንድፈ ሃሳቦቻችን መለያየታቸው ያለያየናል።

በመጨረሻ የሚቀርበው ጥናት በእሸቱ አጋ "ሥነ ምግባር ከ1940-1953 የወጡ የአማርኛ ግጥሞች" በሚል ርእስ በ1982 ዓ.ም ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት፣ በአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት ነው፡፡ እሸቱ በጽንሰ ሃሳብነት የተጠቀመው ሥነ ምግባር በቀደምት ጊዜያት ግብረገብና ሥነ ምግባር በተመሳይ ፍቺ በመታወቃቸው ምክንያት ግብረገብን ነው፡፡

የላቀው ትዕዛዝን፣ የመዝገቡ አባተን፣ የምናሴ የስጋትን፣ የጊይለጊዮርጊስ ወልደ መድህንን፣ የአሸናፊ ጌታሁንን፣ የአቤ ጉበኛን፣ የአክሊለብርሃን ወ/ቂርቆስን፣ የያሬድ ገ/መስቀልን ግጥሞች እንደፍላጎቱ በመምረጥ ጥናት አድርጎባቸዋል፡፡ እኩይና ሰናይ የተባሉ ባህሪያትን በመያዝ ከግጥሙ ጋር በማገናኘት ከፋፍሎ አቅርቧቸዋል፡፡

በግኝቱ እንዳስፈረውም ግጥሞቹ በስፋት በሃይማኖታዊ ሥነ ስርዓት መርሖች የታቃኙና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን መነሻ ያደረጉ ሆነው አግኝቷቸዋል፡፡ ስራዎቹም አስተማሪና ሥነ ስርዓትን በዋና ጉዳይነት የሚያቀነቅኑ (የሚያንጸባርቁ) ናቸው፤ የዚህም ምክንያት በዘመኑ የነበሩት ሰዎች በሃይማኖታዊ ሕይወት የተቃኙ ስለነበሩ ነው ሲልም አክሏል፡፡

የሥነ ምግባር ጉዳይ በግጥም ውስጥ በመቃኘት፤ የቀረቡበትን መንገድ አጥንቷል፡፡ በሌላ አንጻር ግን በመጀመሪያ እንደየ አከባቢውና ዘመኑ የተለያዩ የሥነ ምግባር አይነቶች እንዳሉ ቢገልጽም በየትኛው መስፈርት (የጋራ) ባህሪ ላይ ተመርኩዞ ጥናቱን እንዳደረገ አያመለክትም፡፡ የትኛውን የንድፈ ሃሳብ መሰረት እንደሚከተል አላጠራም፡፡ ከተመረጡት ግጥሞች ውስጥ የፍቅርን ጉዳይ አንስተው የሚያወሱትንና ሃይማኖታዊ አስተምህሮቶችን አንስተው የሚዘረዝሩትን እንደ ሰናይ ምግባር ወይም ሥነ ምግባራዊነትን አቀንቃኝ አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ እኩይ ምግባር ብሎ ያቀረባቸው ደግሞ ኩራት፣ ስካር፣ ዝሙትና፣ ቅናትን ነው፡፡ ግጥሞቹን ዘረዘራቸው እንጂ ትንታኔ ስላላደረገባቸውና በዓላማው እንደገለጸው ሥነ ምግባር የቀረበበትን መንገድ መርምሮ አለማሳየቱ እንደ ድክመት የሚነሱ ናቸው፡፡

ይህ ጥናት የግብረገብን ጉዳይ ከሥነ ጽሑፍ ጋር አጣምሮ በማሳየቱ ከኔ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሆኖ ለቅኝት ቢቀርብም፣ በመረጥናቸው የሥነ ጽሑፍ ዘውጎች፣ በንድፈ ሃሳብና የማጥኛ ዘዴ በኩል ልዩነት አለው፡፡

በመቀጠል በውጪ ሃገር ሰዎች የተሰሩና በትምህርታዊ መጽሔቶች ላይ የቀረቡ መጣጥፎችን የማቀርብ ሲሆን የመጣጥፎቹ ትኩረት በዋንኛነት በግብረገብና ሥነ ጽሑፍ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለቅኝት ተመርጠዋል፡፡

የመጀመሪያው በEileen John አማካኝነት "Literature and the Idea of Morality." በተሰኘ ርዕስ እ.ኤ.አ በ2010፣ A Companion to the Philosophy of Literature. 285-299 ላይ የቀረበ መጣጥፍ ነው፡፡ የተለያዩ ፈላስፋዎች በግብረገብና ሥነ ጽሑፍ ጽንሰ ሃሳብ ላይ ያቀረቡትን ገለጻ አንስተው ከጠቀሱ በኋላ በጥያቄዎች የተቃኘ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

በዋናነት ያነሱት ሃሳብ ሥነ ጽሑፍ በበርካታ ውስብስብ ግብረገባዊ ጉዳዩች የተሞላ በመሆኑ ጥቂት የግብረገባዊ ጉዳዮችን መርጠን በቴክስቶች ውስጥ ስላለው ተግባር፣ ፋይዳና የቀረበበትን "ቅጥ" ከመመርመር ይልቅ ሥነ ጽሑፉ ግብረገብን ለምንና እንዴት እንደተጠቀመበት መርምሮ ማወቅ ይሻላል የሚለውን ነው፡፡

በሌላ በኩል በአጠቃላይ ሲታይ የዚህ ጥናታዊ መጣጥፍ ትኩረቱ በሁለት አውታር ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ ግብረገብ በአንድ የጥበብ ስራ ውስጥ (ሥነ ጽሑፍ ውስጥ) መገኘቱ የሥነ ጽሑፉ ዋጋ ዝቅና ከፍ ማድረግ አለማድረጉ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ የአንድ የጥበብ ስራ በግብረገብ መቃኘት ለስራው የሚኖረው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ሥነ ጽሑፍን ታላቅ ስራ የሚያደርገው የግብረገብ ይዘቱ ነው ወይ? ገጸባህሪያት የሚኖራቸው ግብረገባዊ ባህሪ በአንባቢ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ምንድን ነው? የሚሉና ሌሎችም ጉዳዮች በጥያቄነት ተነስተዋል፡፡ አንድ ድርሰት ያለ ግብረገብ (ግብረገባዊ ጉዳይን ሳያነሳ) ቢቀርብ ስራው እርባና ቢስ ነው ብለን መደምደም አንችልም፡፡ ነገር ግን የልብወለዱ አከርካሪ ግጭት ነው፡፡ ይህን ግጭት ከመፍጠሪያ ዘዴዎች ውስጥ ዋንኛውና አንደኛው ግብረገብ ነው፤ ስለዚህ ብዙ ጊዜ ሊከሰት ይችላል፡፡

ሌላኛው አውታር እንደየአንባቢው ሥነ ልቡናና የባህል አስተሳሰብ ውጤት ግብረገብ ይለያያል፤ ታዲያ የገጸባህሪያትና የአንባቢ ግብረገብ እንዴት ይግባባሉ የሚለውን ጉዳይ ይዞ ሥነ ጽሑፉ ግብረገብን እንዴት ለሁለቱ ውህደት መፍጠሪያነት እንደተጠቀመው ለማሳየት የሚጥር ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ሥነ ጽሑፍን ግብረገባዊ ነው፤ ወይም ኢ-ግብረገባዊ ነው፣ ብለን የምንፈርደው በማን ቦታ ላይ? በምን ሁኔታ ውስጥስ ሆነን ነው የድርጊቱን ወይም የባህሪውን ትክክለኛነትና ስህተትነት የምንገልጸው? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ስለዚህ በማን ቦታና በምን ሁኔታ

ውስጥ ሆነን ነው ግብረገባቸው ላይ መፍረድ ያለብን? የሚለው ጉዳይ አሳሳቢ አይሆንም፡፡ ለምን? ቢሉ አንባቢው የድርጊቱ ተሳታፊ ስለሚሆን በራሳቸው (በገጸባህሪያቱ) ግብረገብና ባሉበት ሁኔታ ላይ ቆሞ መፍረድ ይችላል፡፡

ሁለተኛነት Asim, Karim. “Literature and Morality” በሚል ርዕስ፣ በInternational J. Soc. Sci. & Education, 2012, Vol. 2,186Vol. 2, 186-193 የቀረበው መጣጥፍ ነው፡፡ በዚህ መጣጥፍ የሥነ ጽሑፍና የግብረገብ ግንኙነት ከጥንታዊ ስልጣኔ ጀምሮ ምን እንደሚመስልና እንዴት አይነት አከራክሪ ነጥቦች ይቀርቡ እንደነበር ተዳስሷል፡፡ እንዲሁም በሃያኛው ክፍለ ዘመን ስለ ግብረገብና ሥነ ጽሑፍ ያሉ አመለካከቶች ቀርበዋል፡፡ በቀረበውም የግብረገብ ብያኔ የሰው ልጅ መልካምና እኩይ ብሎ የሚደነግጋቸው እሴቶች ሲሆኑ እነዚህም እሴቶች ደስተኛ (መልካም) ሕይወትን ለመኖር ሲባል የተፈጠሩ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ የተለያዩ ፈላስፋዎችን (አርስቶትልን፣ አርኖልድን፣ ፕሌቶንና የመሳሰሉትን) ሃሳቦች ትኩረት ገልጸዋል፡፡ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚቀርቡ የግብረገብ ይዘቶች በሰዎች ሥነ ምግባር ላይ አሉታዊም፣ አዎንታዊም ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚሉት ሃሳቦች ተንሸራሽረዋል፡፡

የጥናቱ ዋና ትኩረት የግብረገብና የሥነ ጽሑፍ ቁርኝቶች፣ በአንባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖና የትኛው የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ይበልጥ በግብረገብ ከተቃኘ አንባቢው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ፈላስፋዎችና ምሁራን ያነሱዋቸውን መከራከሪያ ሃሳቦችን መግለጽ ነው፡፡ የትራጀዲ ዘውግ ይበልጥ ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚችልና እስካሁን የተሰጡት ብያኔዎች ስምምነት ላይ መድረስ ያልተቻለባቸው እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ የመከራከሪያ ነጥቦችም ማቆሚያ የሌላቸው ናቸው ብለዋል፡፡ ማቲው አርኖልድ ግብረገብን በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲሰጥና ከግለሰብ ወደ ማኅበረሰብ ግብረገብ ትኩረቱ እንዲዞር ማድረጉንና ግብረገብን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከእርሱ ስራ ጋር ተያይዞ እንደተጀመረ ይህም የግብረገባዊ ንድፈ ሃሳብ መመስረቻው እንደሆነ አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻነት የተቃኘው መጣጥፍ የAdriano Moraes Migliavacca “Morality in Poetry the new critical approach.” በተሰኘ ርዕስ እ.ኤ.አ በ2011፣ ገጽ 295-304 ላይ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት ግብረገብ በግጥም ውስጥ በምን አይነት መልኩ እንደቀረበ መመርመር ነው፡፡ የግብረገብ ጉዳይ በጥበብ ውስጥ ከጥንታዊ ስልጣኔ የጀመረ ቢሆንም ይህን ጉዳይ መመርመሩ እልቆ ቢስ እንደሆነም ጠቁሟል፡፡

ግብረገብ በጥበብ ውስጥ እንደምን ይቀርባል? በራሱ አውድስ እንዴት ይቃኛል? ግብረገቡስ ከምን ይመነጫል? ደራሲያንስ በስራቸው ውስጥ ግላዊ ግብረገብን ያቀነቅናሉ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን በዋንኛነት ለመመለስ የተደረገ ጥናት ነው። በግብረገብና በሥነ ጽሑፍ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ለማጥናት ከተፈጠሩ ሥነ ዘዴዎች ውስጥ “New Criticism” በመሆኑ ይህንን ዘዴ ለጥናቱ ማስኬጃነት ተጠቅሞበታል። በኢልቶ እና በዊንተርስ “Eliot’s and Winters’s” ሃይማኖታዊው ግብረገብ ሃሳቦችን ማብላላት ላይ ተመርኩዞ ጥናቱን አካሂዷል። የተለያዩ ምሁራን እንደ መሰረተ ሃሳብ የተጠቀማቸውንም ጨምሮ የሌሎቹንም (Eliot, Winters, Pound) የግብረገብ እይታ፣ ክፍተቶች ጭብጥና አመለካከት ምን እንደሚመስል፣ ድክመትና ጥንካሬያቸውን እያወዳደረ በንጽጽር ሃሳቦቻቸውን የዳሰሰ ጥናት ነው። እነዚህ ምሁራን ትኩረታቸውን ያደረጉት በደራሲያን ካጠበብነውም በገጣሚያን ላይ ነው።

ይኸውም አንድ ገጣሚ የሚኖረው የቋንቋ አጠቃቀም በማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መሰረት አድርገው ምን መሆን አለበት በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሽከረከር ነው። ይህ ስራ የምሁራኑ እሳቤዎች የቀረቡበትን አጠቃላይ መንፈስ መቃኘትም ግቡ አድርጓል። ግጥም በራሱ ውስብስብና የጠራ ፍቺ ሊቀመጥለት የማይችል ሆኖ ሳለ እንደሱው ያለ ውስብስብ የሆነውን ግብረገብን መመርመሩ አዳጋች ቢሆንም ውስብስብነታቸውን ትቶ የጋራ የሚያደርጋቸው የሰው ባህል አንድ ክፍል (የሰው ጉዳይ) ስለሆኑ ርዕሰ ጉዳዩ ላይ ማተኮሩን ገልጿል።

በአጠቃላይ ያነሳው ሃሳብ ግን ግብረገብ የአንድ ማኅበረሰብ ተሞክሮዎች ውጤት ነው። የባህል ምርት ውጤት እንደሆነና ይህንኑ ምርትም ከሚያከፋፍሉበት መንገድ ውስጥ ጥበብ መሰረታዊው እንደሆነ ነው፤ ከጥበቦች ውስጥ አንዱ የሆነው ግጥም ደግሞ የበለጠ ምቹ ነው ሲል ገልጿል።

ከቅኝቱ መረዳት እንደሚቻለው በግብረገብና በሥነ ጽሑፍ ግንኙነትና መጣጣም ዙሪያ የተሰሩ በርካታ ስራዎች አሉ። በሃገራችን ግን በተለይም በጥናትነት ደረጃ የቀረቡት ጥቂት ናቸው። ከነዚህ ጥቂቶች ውስጥም አብዛኛው በሃይማኖታዊ ግብረገብ ላይ ያተኮሩና በልብወለድ ውስጥ ስላለውም የግብረገብ ይዘት የሚመረምሩ ስላልሆኑ ይህ ጥናት ሊደረግ ችሏል።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በሕማማትና በገና ዲኮንስትራክሽናዊ ንባብ

## 3.1 “የሳር ልጆች”

### 3.1.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚከሰቱት አበበና ዳዊት ሲሆኑ የግብረገብ ጉዳይ በይበልጥ የተቀነቃነው በዳዊት አማካይነት ነው፡፡ አበበ እና ዳዊት የአንድ ማኅበረሰብ ውጤቶች በመሆናቸው የተመሳሳይ እሴት ባለቤቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን አመለካከታቸው የተቃረነ ነው፡፡ አበበ ልክ እንደ ማኅበረሰቡ ለሞት ክብር ያለው ሲሆን ዳዊት ደግሞ በተቃራኒው ለሕይወት ክብር አለው፡፡ እነዚህ ጉዳዮችም በዎፍና በሳር ተመስለው ቀርበዋል፡፡

አበበ ዎፍ ይይዝና ለዳዊት ሊያሳየው ይመጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ዳዊት አበበን ጨካኝ አድርጎ ይቆጥረዋል፤ ዎፏን እንዳሰቃያት እያሰበ ይጠላዋል፤ ዳዊት ዎፏ ስላሳዘነችው “እስኪ መብረር ትችል እንደሆን ሞክራት” (10) ብሎ (አውቆ መብረር መቻሏን ገምቶ) እንድትበር ያደርጋታል፡፡

አበበ ዎፏን ሲይዝ ዓላማው ሁለት ነገር ነበር፡፡ የመጀመሪያው ዎፏን መሸጥና ገንዘብ ማግኘት፣ አሊያም ጓደኞቹ ላይ “መጎረር” ነበር፡፡ የመጀመሪያው ዓላማ የሚያስገነዝበው ለአበበ ገንዘብ ምን ያህል ዋጋ እንዳለውና (ገንዘብ ከሁሉ ነገር የቀደመ ታላሚነት እንዳለው) ከሕይወትም ገንዘብ ብልጫ እንዳለው ነው፡፡ ሁለተኛ አላማው ደግሞ ራስን በሌሎች ፊት ማስከበር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለያዛት ወፍ የሰጣት ስብራትና ህመም አያሳስበውም፡፡ የሱ ጉዳይ አንድም ገንዘብ ማግኘት፣ ካልሆነም በጓደኞቹ ዘንድ ክብርን መሻት ነው፡፡

ዳዊትና ቤተሰቡ እነ አበበ ቤት ማህበር ተጠርተው ሲሄዱ ሳር ተጎዝጉዞ ነበር፡፡ ይህንን ሳር ያጨደው አበበ መሆኑን ሲያውቅ ዳዊት ይናደድና ምግብ አልበላም ብሎ ይወጣል፤ ቤቱም ሄዶ ያለቅሳል፡፡ ቤተሰቦቻቸው አበበን እያደነቁት ነበር፡፡ አበበም ሳር ማጨዱን ዎፏን ያስመለጠበትን ማካካሻ በቀል አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡ የአበበ ቤተሰቦች ለሕይወታቸው ዘላለማዊነትና ለመዳናቸው ሲሉ ዝክር ያደርጋሉ፡፡ ግን ለዝክሩ ሲሉ ሳሩን ያጭዱታል፡፡ ሳሩ ምግብ ነው፣ ማረፊያ ነው፣ መሸሸጊያ ነው፤ የራሱ እንኳ ሕይወት ቢቀር ስለሌሎች ሕይወት መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

እነሱ እረጋግጠው አውጥተው ለሚጥሉት ነገር ሁሉ ፋይዳውን ያሳጡታል፡፡ ቢጠቀሙበት እንኳ ሁሉም ተፈጥሮ ለሰው ልጅ ግልጋሎት የቆመ ነው ተብሎ ሊታመን ይችል ነበር፡፡ (ለቤት መስሪያነት ቢገለገሉት ተጠቀሙበት እንጂ አባከኑት ለማለት አልደፍርም ነበር፡፡) ነገር ግን ይረግጡታል እንጂ አይገለገሉበትም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ርዕሱ ነው፡፡

ርዕሱ "የሳር ልጆች" ይላል፡፡ የሳር ልጆች ተብለው አንዱ ሳሩን ለማረፊያው፣ ለማጣጣም ሲጠቀምበት እና ከውበት፣ ከግብረገባዊነት፣ ከሰላም ጋር አያይዞ ሲረዳውና ሲጠቀመው ሌላው ሳሩን ለመረጋገጫነት ይጠቀመዋል፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ አባል ቢሆኑም ተቃራኒ ተግባር አላቸው፡፡

ይህ የገጸ ባህርያት ግጭት በሽፋን ገጹ የሚገኝ ነው፡፡ የዎፍና የሳር፣ የአበበና የዳዊት፣ በአቧራ መሸፈንና በተማሪዎች መጸዳት፣ የመቼት ገለጻው ከቤት ውስጥ ወደ ሜዳ በድጋሚ ወደ ቤት ውስጥ መመላለሱ እርስ በርስ ተጻራሪ የሆኑ ሃሳቦችንና ተቃራኒ ተጣማጅ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችን ዘንቀዋል፡፡ ይህም ፊት ለፊት ከቀረበው የሁለት ጓደኛሞች ግጭት በስተጀርባ የቀረበ አንዳች ጭብጥ እንዳለ ይጠቁማል፡፡ በመቀጠል ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን በመጠቀም ፍቺዎችን ለመፈልፈል እሞክራለሁ፡፡

የሁለቱ ጓደኛሞች ጸብ የጀመረው በዎፍ ነው፡፡ ዳዊት ያሰበው ዎፏ ተይዛ በመሸጧ "ከቤተሰቦቿ" ተነጥላ መቅረቷን፣ ነጻ የሆነችውን ፍጡር በመያዝ ነጻነቷን መንፈጉን እና ሞቷን ነበር፡፡ ዳዊት ያላየው አቅጣጫ ዎፏ ሟች መሆኗን ነው፡፡ ዎፏን ለፈረንጅ ቢሸጣት አድርቀው ሊሰቅሏት እንደሚችሉ ያሰበው አበበ ምናልባት ዎፏ በጫካ ውስጥ ብትሞት ትበሰብሳለች፣ አፈር ትሆናለች፤ ደርቃ ብትሰቀል ግን አንድም ረጅም ጊዜ በጌጥነት ታገለግላለች፤ ለሰው ልጅም የመንፈስን ደስታ ትፈጥራለች፤ አንድም ምስሏ በፎቶ ቢቀረስ ዘላለማዊነትን ልትላበስ ትችላለች (ቢያንስ በብዙ ሰዎች ዘንድ የመታወቅና የመታወስ ዕድል ይኖራታል)፡፡

በሌላ በኩል አበበ የሳተውና ዳዊት ደግሞ የተቆረቆረለት ነጥብ፣ በጫካ ውስጥ ኑሮ አንዱ ያንዱ ጥገኛ መሆኑን ነው፡፡ አንዱ እንስሳ ለህልውናው ሲል ሌላውን መመገብ አለበት፡፡ ዎፏ በሕይወት ብትኖር ወይም ብትሞት ለምግብነት የሚያውሏት እንስሳት አሉ፡፡ የዎፏ ከዛ ጫካ መውጣት ምግብነቷን ያስቀረዋል ማለት ነው፡፡

እንዲሁም ዳዊት ማድረግ የማይችለውን ነገር አበበ ይችላል፡፡ ዎፍ ይዟል፤ (የዳዊት አለማድረግ ካለመፈለግ ጋራ ተያይዞ የሚነሳ ቢሆንም እንኳ) ስለዚህ እራሱን እንደ አዋቂ

ይቆጥራል፡፡ ዳዊት ደግሞ ለአበበ አላዋቂነቱን ማሳየት ይፈልጋል፤ ስለዚህ ዎፏን ያስመልጠዋል፡፡ አበበ በጉልበት፣ ዳዊት በብልጠት ስለሚስተካከሉ እኔ እበልጣለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ በማለት ሃያልነታቸውን (አዋቂነታቸውን) ለማሳየት አንዱ ያገኘውን ሌላኛው ያስጥለዋል፡፡

የሳሩም ጉዳይ ከዎፏ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሳሩ ሲታጨድ ምግብነቱን፣ መጠለያነቱን፣ ማረፊያነቱን ያጣል፡፡ ነገር ግን ዝክር ብለው በፈጣሪያቸው ፊት ስለሚያነጥፉት አንድም ከመዘከሪያነት አንዱ አድርገው በማቅረባቸው ክብር ሰጥተውታል፤ አንድም ቤታቸው ተጎዝጉዞ በማየታቸው ሰዎች ደስታን አግኝተውበታል፤ ተፈጥሮ ለሰው ልጆች መገልገያነት የሚያገለግል ከሆነ ደግሞ ይህ ምንም ስህተት የለውም፡፡ እንዲሁም ሳሩ በክረምት ቢለመልምም በበጋ መድረቁ አይቀርም፤ አጭደው እቤታቸው ባይወስዱትም በመንገደኞች በመረጋገጥ መክሰሙ አይቀርም የሚለውን የተረዳው አበበ ሳሩን አጭዶታል፡፡ ዳዊት ሳሩና በደን ውስጥ የሚገኙትን ተፈጥሮዎች በሙሉ በማቀናጀትና ልዩ ትርጉምን በማበጀት ምድራዊ ገነትን ይፈጥራል፡፡ በእርሱ ውስጥም ተፈጥሮን በማስጠበቅ ዘላለማዊነትን ለመቀዳጀት ይጥራል፡፡ አበበ ደግሞ በፈጣሪው ፊት በመስዋዕትነትም ይባል በሌላ መንገድ በማቅረብ ዘላለማዊ ሕይወትን ለመውረስ ይጥራል፡፡ ስለዚህ ሁለቱም መንገዳቸው ይለያይ እንጂ የመጨረሻ ግባቸው አንድ ነው፡፡

"የአካባቢ ጫና" የተሰኘው ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ተደርጎ ይህ ጉዳይ ሲመረመር የአንድን ሰው ባህሪ ከመግራት አንጽር አስተዋጽኦ ያላቸው በዙሪያው ያሉ ሰዎች (ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ አስተማሪ፣ ጎረቤት፣ ኅብረተሰብ) እና ተፈጥሮ (እንስሳት፤ እጽዋት እና ግዑዛን ነገሮች) ናቸው፡፡ ግብረገባዊነትን ለመፍጠርም በእነዚህ መጠቀም ግድ ነው፡፡ አበበም፣ ዳዊትም ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአንድ ክፍል የሚማሩ፣ ጎረቤታሞች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ እሴቶቻቸው ተመሳሳይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ አልሆነም፤ ለምን? ጓደኛሞቹ በአንድ አካባቢ ኖረው ተመሳሳይ ግብረገባዊ እሴቶች አለመያዛቸው ደግሞ ሌላ ነገር ይጠቁማል ካልሆነ ለዳዊት ማመጽ ማን አስተማረው?

የአበበን ሰብዕና የገነቡት ቤተሰቦቹ ናቸው፡፡ ከእነሱ ይሁንታን ስላገኘም ነው በእኩይ ድርጊቱ የሚገፋበት፡፡ "ዎፏ ሰብኣዊ ፍጡር ስላልሆነች ግብረገባዊ ጉዳይ አይመለከታትም እኮ" የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል፤ ግን ዎፏም ትሁን ሳሩ የሚያሳዩት ሕይወትን ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ለሕይወት ክብር የሌለው እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ማኅበረሰቡ ለልጆቹ ግብረገብን ማስተማር ይፈልጋል፤ በመርሖቹም የታነጹ ልጆች እንዲኖሩት ይሻል፡፡ ስራቸው ግን በግብረገብ የተቃኘ

አይደለም። ልክ በ"ዴስኮቹ" እንደሞላው አቧራ ኢ-ግብረገባዊ ምግባሮችን ለብሷል። ሐሜት፣ ሕይወት ማጥፋት፣ ስካር፣ ቂም በቀል ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶች ናቸው። "... ውብ ምንጮች ሲደርቁ ሰው መልካነትን ከማን ይገልብጥ?......ማኅበረሰብ መርቀቁ በዝቶበት ደም ያጎርፋል......ወፍ ይገላል፣ መነኩሴ ይሰዋል......" (14) እያለ ማኅበረሰቡ የሰብዕና ዝቅጠት ውስጥ እንዳሉ ያሳያል፤ ደመነፍሳዊነት ገኖ ግብረገብ እንደመነመነ ይገልጻል። የሁለቱ አለመጣጣምም የጀግንነትን፣ የሕይወትን፣ የክብርን፣ የሰብዕናን ትርጉሞች አዛብቷል። ይህ መዛባት ደግሞ ግጭት እንዲፈጥሩ አድርጓቸዋል።

ዳዊት እና አበበ ተፈጥሯዊ ስሜታቸውን ይከተላሉ። አበበ ዎፍ መያዙንና መሸጡን ታላቅ ወንድሙ እንዳይሰማበት ይፈልጋል፤ የሚያደርገው ነገር ትክክል ስላልሆነ እንደሚቆጣው ስለሚያውቅ ደመነፍሳዊ ስሜቱ ግን ከታላቅ ወንድም ፍራቻ አይሎ የዎፏን እግር ሰብሮ እንዲይዛት አድርጎታል። ታላቅ ወንድም ተገቢውንና ኢ-ተገቢውን የሚያስለያቸውና የሚፈሩት ስለሆነ፣ በተጨማሪም ግዘፍ ነስቶ የሚከሰትበት አጋጣሚ ስለሌለ የግብረገብ ተምሳሌት ነው። ዳዊትም በተመሳሳይ ታላቅ ወንድሙን ይፈራዋል፤ ተፈጥሯዊ ስሜቱን መከተል ይፈልጋል፤ የማኅበረሰቡን እሴቶች ላለመጠበቅ ይጥራል፤ የተለየ አቋምን ይይዛል።

አበበ ግብረገብን የቀሰመው ከአካባቢው ነው። በአካባቢው ደግሞ ክብር የሚሰጠው ለሞት እንጂ ለሕይወት አይደለም። ቤተሰቦቹ ተዝካር የሚያደርጉት ከሞት በኋላ የሚኖራቸውን ሕይወት በማሰብ ነው። ለነሱ ይህ አለምና በዙሪያቸው ያሉ ተፈጥሮዎች አላፊ ጠፊ (ከንቱ) ናቸው። ሰው ሲሞት ይከበራል፤ ንጉስ እንኳ ሳይቀር ቆሞ ያሳልፈዋል። አበበ ሕይወት ስለቀጠፈ ጀግና ይባላል፤ ይሞካሻል። ዳዊት ይህን አላደርግም ስላለ ይንኳሰሳል፤ አበበ ሕይወትን በመግደልና በመረጋገጥ ይደሰታል፤ ዳዊት ሕይወትን በማጣጣምና በማድነቅ ይደሰታል። ዳዊት ለሕወት ዋጋ አለው፤ የሚጫወተው በሞቱ "አሸኖች" ክንፍ ነው። ይህም ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ልማዱን የሚቃረን ነው፤ ከአካባቢው ያፈነገጠ ነው። በዚህም ከባህሉ ጋር ይጋጫል። እንዴት ቤተሰቦቹ ትክክል ናቸው ብለው የደነገጓቸውን እሴቶች በመቃወም፣ ሕይወትን በመንከባከብና ሕይወት ላላቸው ነገሮች ዋጋ በመስጠት፣ ተፈጥሮን በማጣጣም፤ ከዚያም የራሱን ግብረገብ ይነድፋል።

ዳዊት ከግጭቱ ለመውጣት እንደ መፍትሔ የወሰደው ለራሱ አዲስ ግብረገብ መፍጠርን ነው። የሚወደውን አይነት፣ ጭካኔ የሌለበትን፣ መሸሻ የሚሆን አለም ፈጠረ። የታሪኩ መቼት ገለጻ የሚጀምረው ክረምቱ በደንብ ያልለቀቀው (እሱ እንደሚለው ቀፋፊ ክረምት) የአየር ሁኔታ፣

የመማሪያ ክፍሉ እንደተገለጸው አሮጌና አስቀያሚ ነበር፡፡ "… ዝብርቅርቅ ያለ ነገር……በጭንቀት የሚቆነጥጥ…… አእምሮዬን ይሄ ይሄ ስላደከመው ራሴን ላፍታታ ከቤቴ ወጣሁ" (12) የወጣው ከቤቱ ነው፤ ቤቱ ደግሞ እስካሁን የኖረበት ነው፡፡ ያንን ጥሎ ወደ ጫካ ይሄዳል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የሚገኘው መቼት ግን በሙሉ በፍቅር፣ በመተጋገዝ የሚኖሩበት፣ ሰላም የሰፈነበት፣ የሚረብሽ ነገር የሌለበት ነው፡፡

"ሁሉ ነገር ውብ ነበር……

ሕብር ነበር……ከቅጠሎች ውዝዋዜ……ከርጥበቱና ከሳሩ ሽታ ጋር ያነበብኩት ግጭት……ጦርነት……ደም……አውሬ ትርጉም ያጡ መሰለኝ……" (13) ቦታው የገነት ተምሳሌት ነው፤ በኋላም እራሱም አዳምና ሄዋን ያስወጡን ከእንደዚያ አይነት ቦታ እንደሆነ ስለሚገልጽ፡፡ ሁሉም ይደጋገፋሉ፡፡ የሚረብሽ ነገር የለም፤ ሰላም የሰፈነበት ስፍራ ነበር፡፡ ይህ ነው አዲሱ ግብረገብ በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ፣ ተፈጥሮን ማጣጣምና ማለሳለስ የሚችል ግብረገብ፣ ሞትን ሳይሆን ሕይወትን የሚያመልክ እሴት፤ ምክንያቱም የቦታው ገለጻ ገነትን ስለሳለ ገነትን ደግሞ ምድር ላይ እንድትወርድ ስላደረገ "… ውበት ከሰማይ እምብርት……ወደ ምድር ሳታቋርጥ የምትፈስ ትመስላለች……" (13-14)፡፡ ዳዊት አዲስ እሴትን ለመመስረት ይጥራል፤ ግን አጋዥ የለውም፤ እንዳውም ይቀጣል፡፡ ቤተሰቦቹም፣ አበበም ይቀጡታል፡፡ እነሱ የሆኑትን እንዲሆን፣ ሕይወት የቀጠፈውን ጀግና ብሎ እንዲያወድስ ይገፋፉታል፡፡

ምፏ ስለበረረች አበበ እንደተጎዳ፣ እሱ ግን ምንም እንዳልሆነ ይገልጽና ዘግይቶም ቢሆን ስለመቀጣቱ ያስባል፡፡ (12) ይህ እንዳለ ሆኖ ትላንት፣ ዛሬ፣ ነገ ብሎ በሚያቀርበው ሀቲት ውስጥ ትላንት "አርሙኝ" የተሰኘ መጽሐፍ እያነበበ እንደነበር ይገልጻል፡፡ መጽሐፉ ማኅበረሰቡ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች የሚወክል ነው፤ በልጅነት አእምሮው አንብቦ የገበየውን የሚጠቁም ነው፡፡ በተጨማሪም ትላንት ላይ የሚገልጸው ከአበበ ጋር በምፏ ሲጣሉና በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሳለፈውን (ያየውንና ያደረገውን) ነው፡፡ ዛሬ ላይ የሚገልጸው በከፊል መጽሐፉን ሲያነብ፣ በከፊል ደግሞ ከዚያ ገነት ከሆነው ቦታው ሄዶ ያሳለፈውን ነገር ነው፡፡ ሁሉ ነገር ጥርት ብሎና አምሮ ይታየው ነበር፣ ሰላሙን እያጣጣመ ባለበት ወቅት በድንጋይ ይመታል፤ ያመዋል፤ ያቃስታል፡፡ መቺው አበበ ነው፤ ግን አይታየውም፡፡ የሚመታውን ለማሸት እንኳ በማይችልበት ቦታ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የባህሉን ቅጣት ነው፡፡ እየቆየ እየጨመረ ይሄዳል እንጂ በዚሁ አያበቃም፡፡

### 3.1.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

በድንጋይ በመመታቱ ቀደም ሲል የተገለጸው ደስታው ሁሉ ይጠፋና እሱም ወደ አሳዳጅነት ይቀየራል፤ ልክ እንደ ቤተሰቦቹና ጓደኛው ይሆናል፤ ሲበሩ የነበሩትን ቢራቢሮዎች ማሳደድ ይጀምራል። ከአካባቢው የተማረውን ዕውቀት ለመተግበር። ዳግም እንዳያፈነግጥም አዲስ ያበጀው ገነት ኃጢያተኛ ናቸው፤ ኢ-ግብረገባዊ ናቸው፤ ሕይወት አጥፍተዋል ብሎ በሸሻቸው ሰዎች ገነቱ ይደፈራል፤ እንዲህ አይነት ሰዎች ከገቡበት ደግሞ ወይ ገነትነቱ ይቀራል፤ (ስለሚረክስ) ወይ ደግሞ ያጎደፈው ይባረራል።

በማኅበረሰቡ በኩል የገነባው የእኩልነትና ነጻነት ወለል ይፈርሳል፤ የሚወደው የሚያርፍበት ሁሉም ሕይወት እየነካው የሚያልፈው ሳር ይታጨዳል፤ ገነት የነበረውን ቦታውን ያጠፉበታል። በተጨማሪም ነገ ወደ ማይፈልገውና ወደ የሚያስጠላው ቦታና ሕይወት እንደሚሄድ ይጠቁማል።

አስቀድሞ የተቀመጠ ንግር አለ። ዳዊት ወደ መማሪያ ክፍሉ ሲገባ  የአስተማሪነትን ሚና ይወስዳል፤ ነገር ግን አስተማሪነቱን ይፈራዋል፤ የፈራው አንድም አስተማሪነት ከተማሪነት የበለጠ ሃላፊነት ስላለው ነው። ተማሪ ሁሉ አንድ አስተማሪውን ብቻ ነው የሚያየው። አስተማሪ ግን በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ሁሉ አይን ያያል። የአይኑ መብዛት በራሱ ያስፈራል። አንድም ሆኖ የሚያውቀው ተማሪ እንጂ አስተማሪ አይደለም። ሆነው የማያውቁትን ነገር መሆን ደግሞ ይከብዳል። ይህም የለመዱትን ሕግ ጥሶ የራስን ምርጫ መወሰን የሚፈጥርበትን ኀሊናዊ ፍራቻና ስጋት ያሳያል። ሲፈራ በፍጥነት አይኖቹን ከተማሪዎቹ ላይ ነቅሎ በቀጥታ ወደ መሬት ያያል። ወደ መሬት ማየት አንገትን መድፋት ነው፤ ፊት ለፊት ለማየት ድፍረትንና ጥንካሬን ማጣት። ይህ ጥንካሬውን ማጣቱም ይበልጥ የሚረጋገጠው መጨረሻ ላይ በማልቀሱ ነው።

ዳዊት እነ አበበ ቤት መቆየትም፣ መብላትም አልቻለም። እንባ ያንቀዋል፤ ይጠራጠራል "አንተ ቤት ድሮም አልበላም.......መብላትም አልፈልግም......ወደፊትም አልበላም፣ ወጥህ የርግብ ሥጋ ይሆን ይሆናል።..." (17) እዚህ ጋ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የሳሩ መታጨድ የገነቱን መጥፋት የሚያሳይ ስለሆነ የገነባው ግብረገብ በነባሩ ባህል ቅጣት ምክንያት መፍረሱና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ መግባቱ ልብ ሊባል ይገባል።

ዳዊት ወደ ማኅበረሰቡ መቀላቀሉን የሚጠቁመው ክስተት በድንጋይ ከተመታ በኋላ የሚያደርገው ድርጊት ነው። መጀመሪያ ለሕይወት ተቆርቋሪ ሆኖ ተፈጥሮን ባለበት ሁኔታ (ሳይቆርጡ፣ ሳያጭዱ) ለደስታ ስለማዋል እየሰበከ የነበረው ልጅ ድንጋዩ ሲያርፍበት ቢራቢሮ ወደ ማሳደድ ይሄዳል፤ የሚያሳድዳቸው ሊገላቸው ነው፤ ይህም እሴቶቹን ተቀበለ ወደሚለው ይወስዳል። ነገር ግን በምን መልኩ ነው የማያምንበትን፣ ሊቀይረው የጣረውን ባህል የሚቀላቀለው?

በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ የግብረገብ መርህ የለውም (እርሱ ፈርሷል)። የመጨረሻው የመቼት ገለጻ የቤቱ ሳሎን ውስጥ ነው። ይህም ትቶት ወደ ወጣበት መመለስን ያመለክታልና ወደ ነባሩ ባህል መምጣቱን ይጠቁማል። አዲሱን ባህል ለመመስረት ወደ ጫካ ሲሄድ ቤቱን ትቶ ነበር የሄደው። በስተመጨረሻ ግን ብቻውን እንደወጣ ብቻውን በቅጣቱ እያነባ ተመልሷል። "… በቀስታ አለቀስኩ……እንባዬ አቃጠለኝ……የቤቴን በር ከፍቼ ስገባ ልቅሶዬ ጨመረ……ሳሎን ውስጥ እኔ ብቻ ነበርኩ……" (18) ኅሊናው ያካበተው ዕውቀት ውድቅ ሲሆንበት፣ ሌላ ለማወቅ ሲጥር፣ በዚህ አምኖበት ሳይጨርስ ደግሞ ከአከባቢው የሚደርስበት ጫና ተዳምረው ጭንቀት ስለሚፈጥሩበት በፍጥነት መፍትሔ ማግኘት ስላለበት ወደ ባህሉ ተመልሷል። ግን በአካል አብሯቸው ቢሆንም ከማኅበረሰቡ ተነጥሏል። እነ አበበ ቤት ከሰው ጋር መሆንን ጠልቶ የወጣው ህመሙ እየበዛበት ስለሄደ ነው። በመነሻው እያንዳንዱ ተማሪዎች "ዴስካቸውን" ሲጠርጉ የራሳቸውን ልብስ በማቆሸሽ እንደተገለጸው እያንዳንዱ ሰው የዳዊትን ዓይነት ማንነት ይዞ በመምጣት የገነባው ማኅበረሰብ በመሆኑ ነው። ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶችና ምግባሮች የሞሉበት። ዳዊት በማስመሰል ይኖራል እንጂ ውስጣዊ ፍላጎቱ ሌላ ነው።

በሌላ አቅጣጫ ሲታይ ዳዊትና አበበ ተቃራኒ ሰብዕና አላቸው የተባለው ነገር ውድቅ ነው፤ ምክንያቱም አበበ ለህይወት ክብር ስለሌለው ሳር አጨደ፤ ሳሩም ሕይወትን ይወክላል ብያለሁ። ዳዊት ደግሞ በተቃራኒው ነው። ዳዊት በጫካ ውስጥ እያለ በድንጋይ ከመመታቱ በፊት ሳር በጥሶ እያኘከ ነበር፤ በጀርባውም ተኝቶበት ሳለ የሚሰጠውን ደስታ እንጂ ሳሩን እየተጫነው፣ እየረገጠው እንደሆነ አላሰበም፤ አላሳሰበውም ነበር። በዚህ አካሄድ አበበም፣ ዳዊትም ነፍስ አጥፍተዋል። ታዲያ ለምን ዳዊት አበበን ተጠያቂ ያደርገዋል? ይወቅሰዋልስ? በተጨማሪም በገነባው ገነት ውስጥ አንዱ በአንዱ በመጠቃቃት የሚኖሩበትና ነጻነትና እኩልነት የሌለበት ስፍራ መሆኑንም በመግለጽ የዳዊት ሃሳብ እኔ አውቃለሁ ባይነት የፈጠረው ከንቱ ድካም እንደሆነም መጥቀስ ይቻላል።

ይህም የሚያሳየው ማኅበረሰቡ ግብረገብን በሚገባ መቅረጽ ስላልቻለ፤ ተተኪዎቹ ራሳቸውን የተለየና የተሻለ አድርገው ቢቆጥሩም፤ ለድርጊታቸው ሃላፊነትን መውሰድ የማይችሉ፣ ጥፋታቸውን በሌሎች ላይ የሚያሳብቡ፣ እንዲሁም ሁሉን እኔ አውቃለሁ ባይ፣ ግብዝነት የሞላው በአጠቃላይ ኢ-ግብረገባዊ ሰብዕና ያለው ትውልድ እንዳፈሩ የሚያስቃኝ ስራ መሆኑን መጥቀስም፣ ዳዊትና አበበ ተመሳሳይ እንጂ ተቃራኒ እንዳልሆኑ መግለጽም ይቻላል፡፡

## 3.2 “እራት”

### 3.2.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚቃኙት ወይዘሮ ደብሪቱ፣ አበበች እና ታሪኩ በተከሰተበት ዕለት እንግዶች የሚሆኑት የደብሪቱ ልጆችና ጓደኞዎቻቸው ናቸው፡፡ በዋናነት ደብሪቱና አበበች የጉዳይ ማጠንጠኛ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ታሪኩ የሚከወንበት መቼት በደብሪቱ መኖሪያ ቤት ውስጥ ደብሪቱ ልጆቻቸውንና ጓደኞቻቸውን በእንግድነት በጋበዟቸው እለት ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ነው፡፡

ደብሪቱ ከአበበች ጋርና ከእንግዶቹ ጋር የሚፈጥሩት ግጭት አለ፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚከሰቱት ግጭቶች አንዱ በግልጽ የሚታይ ነው፣ ሌላው ግጭት ውስጥ ለውስጥ የሚነድና በቅጣት የታጀበ ነው፡፡ በደብሪቱ ቤት የተሰበሰቡት እንግዶች መክሰስ እንቁላል ከበሉ በኋላ ለእራት የሚጠብቁት ሰው እስኪመጣ ድረስ እየተጨዋወቱ ነበር፡፡ የሚጨዋወቱት በጉራማይሌ ቋንቋ ነበር፡፡ ለደብሪቱ ይህ አልተዋጠላቸውም፡፡ የሚጨዋወቱት ነገር ስላልገባቸውም ተበሳጩ፤ እሳቸውን ያበሳጫቸው ማንኛውም ሰው ደግሞ መቀጣት እንዳለበት ያምናሉ፤ ስለዚህ ልጆቹን ሊቀጧቸው ፈለጉ፤ ቡና እንዲፈላ አዘዙ ስኳር የበዛበት ቡና ሲጠጡ የምግብ ፍላጎታቸው እንደሚዘጋ ያውቃሉ፡፡ የተደገሰላቸው ዶሮ ወጥ፣ ክትፎና ሌሎችም ቅባት የበዛባቸው ምግቦች ደግሞ ከስኳሩ ጋራ ተዳምረው ልጆቹ መብላት እያማራቸው እንዲቀሩ ያደርጋቸዋል፡፡

እንግዶቻቸው አድርገው የጋበዟቸውን፣ ለእነሱ ሲሉ ዶሮ አሳርደው፣ ስጋ አስገዝተው፣ ቅቤ አስነጥረው፣ ደግሰውና ተዘጋጅተው የጠበቋቸውን እንግዶች ለዚያውም የገዛ ልጆቻቸውን ቢያንስ እጮኛዎቻቸውና ጓደኞቻቸው እንኳ ቢቀሩ ልጆቻቸውን ገና ለገና ጉራማይሌ ቋንቋ ስላወሩ መቅጣት ተገቢ ነው? ለምን መቅጣት ፈለጉ? ለምንስ የመቅጫ መንገዳቸው ምስጥራዊ ሆነ? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስና የተለያዩ ፍቺዎችን ለማግኘት ዲኮንስትራክሽናዊ ዘዴን መጠቀም ያሻል፡፡ ልጆቹ እናውቃለን (የተማርን ነን) ብለው ነው እንግሊዘኛ ከአማርኛ እየደባለቁ

የሚያወሩት፡፡ እናት ደግሞ አለማወቃቸውን ለማሳየት፣ እሳቸው (ያልተማሩት) ከልጆቹ የተሻለ ዕውቀት እንዳላቸው ማሳየት ይፈልጋሉ፡፡ እራት እየበሉ የሚሉት ነገርም ይህን ያረጋግጣል፡፡

"እናቷ ፈገግ አሉ፡፡ በመቅጣት ችሎታቸው ይኮራሉ፡፡ ልጅ፣ እንኳን በሆዱ በነፍሱ መቀጣት አለበት......ካበዛው......አውቅ አውቅ ካለ፡፡ ከምሳ (ስህተቱ ከመጽሐፉ ነው) በፊትስ ምን ያህል ከብቶች ቢሆኑ ነው ወፍራም ስኳር የሰረገበት ቡና የለጠጡት፡፡ የዘመኑ ልበ-ቢስ ምሁር፡፡ የት አለ አንጎላቸው?" (85-86) ደብሪቱ ቡና እንዲፈላ አስተያየት ሲያቀርቡ ልጆቹ ባይፈልጉና ምግብ እንደሚዘጋቸው ቢያውቁም እንኳን እንቢ አይሉም፤ ምክንያቱም አንድም እንግዳ ናቸው፣ አንድም ቡና ለእንግዳ መፈላቱ አንድ እሴት ነው፣ አንድም "ቡና ያጫውታል" የሚለውን ብሂል ታሳቢ በማድረግ፤ እሺ ማለታቸው አይቀርም፡፡

ይህ ጉዳይ በሌላ አቅጣጫ ሲታይ ደብሪቱ ባህላቸውን ለማስጠበቅ የሚደክሙ ናቸው፡፡ ከባህል መሰረቶች ውስጥ አንዱ ቋንቋ ነው፡፡ ይህ ቋንቋ ከጠፋ የማኅበረሰቡ ህልውና ይጠፋል፡፡ በዚህ ስጋት ውስጥ ስለገቡም ነው ልጆቻቸውን ለመቅጣትና ለማረም የሚጥሩት፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ በልጅነታቸው ያልቀረጹባቸውን አድገው እጮኛ ይዘው በመጡበት እድሜ ለማስተካከል በመጣራቸው አንድም ቅጣታቸው በራሱ ውስጥ ውስጡን የቀረበ በመሆኑ ግቡን ሊመታ ባለመቻሉ፡፡ እንዲሁም ቅጣት ብቻውን አስተማሪ ስላልሆነ ውጥናቸው ሳይሳካ ቀርቶ እንዲያውም ራሳቸውን የሚያበሳጭ ክስተት ይፈጠራል፡፡

በሌላ በኩል ደብሪቱ ከአበበች ጋር የሚያደርጉት ግጭት አለ፡፡ ደብሪቱ ሰራተኛቸውን አበበች የሚይዟት በሎሌ ግብረገብ ስርዓት ነው፡፡ አበበችን ሲያማት "ያልተለመደ ራስ ምታት?" ይሏታል እንጂ አይዞሽ፤ እረፊ፤ ይተውሻል፤ ወይም ፈጣሪ ይማርሽ አይሏትም፡፡ እንደ ኒቼ ፍልስፋና ከሆነ ይህ ነገር ትክክል ነው፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ነጻነትና ክብር አለው ለሚለው ፍልስፍና ግን አይሰራም፡፡ አበበች ከእሳቸው እኩል ነጻነትና መብት የላትም፤ አበበች ለጌታ የሚቀርብን ምግብ መስራት እንጂ መብላት አትችልም፡፡ የአበበች ድርሻ የተበላሸን ማስተካከል እንጂ የተስተካከለን መካፈል አይደለም፡፡ ይህን እምነታቸውን የሚያስረዱ ማስረጃዎች አሉ፡፡

የመጀመሪያው ትዕይንት የጌታን ክብር በመንካቷ የሚፈጠር ግጭት ነው፡፡ አበበችን ስጋ ክተፊ ብለው ወጡ፤ ሲመለሱ አበበች ድልህ መክተፊያ ላይ አድርጋ በምትከትፈው ስጋ ለውሳ ስታላምጥ ደረሱ "ለራስሽ ደገስሽው" ብለው ይቆጣሉ፡፡ ደብሪቱ እዚህ ጋ ያላቸው የቋንቋ አጠቃቀምም ሆነ ድርጊታቸው ይለያል፡፡ ለአበበች ሲሆን ቢላ በመቃጣት፣ በስድብና

በማስፈራሪያ ነው፡፡ "ቢላውን ቀምተው ቃጡባት ‹አንገቷን ማለት ነው› አሉ፡፡" (78)፤ ብትደግመው ደግሞ የተቃጣባት ቢላዋ ሊሰነዘርባት ይችላል፡፡ እመቤቷ በሕይወቷም ጭምር መብት እንዳላቸው ያምናሉ፡፡ ሎሌዋም በዚህ ነገር ታምናለች፤ ምክንያቱም ሲመጡባት ከመደንገጥና ሲቃጡባት ከማፈግፈግ የዘለለ ቃል እንኳን አትናገርም፡፡ ህመሟን እንኳ ስትገልጽ የትኛው ቃል ተገቢ እንደሆነ አማርጣ እንጂ በመጣላት ቋንቋ አታወራም፡፡

ሁለተኛው አበበች ታማ ነበር፤ ድግሱን ለማዘጋጀት አቅም አልነበራትም፤ ድሪቱ አግዝሻለሁ ብለው ቃል ገቡላትና መስራት ጀመረች፤ (ባይገቡላትም መስራቷ የማይቀር ጉዳይ ቢሆንም) ቃላቸውን አልጠበቁም፡፡ ትተዋት ስልክ ላውራ ብለው ወጡ፤ የተመለሱት ሁለት ጊዜ ነው፡፡ አንደኛ ስጋውን የጎረሰች ጊዜ፤ እሱንም ዶሮውን አልጫ፣ ስጋውን ቀይ ወጥ ስሪው ለማለት፤ በመቀጠል ሁሉን ነገር ሰራርታ ስትጨርስ ነበር የመጡት፡፡ ከዚያም አላረፈችም፡፡ እንግዶች መጡ፡፡ መክሰስ እንድትሰራ ታዘዘች፣ ቀጥሎ ቡና እንድታፈላ ታዘዘች፣ እራት ስታቀርብ፣ ወይን ሲደፉ ስታጸዳዳ፣… ጠዋት ለደብሪቱ ቁርስ ሰርታ ስትጨርስ የጀመራት ራስ ምታት እስከ ምሽት ድረስ አልተዋትም፤ የተገባላት ርዳታም አልተደረገላትም፡፡ የመጨረሻው ትዕይንት እንግዶች ስለ ምግቡ ጥሩነት ሲመሰክሩ ደብሪቱ የሚሰጡት ምላሽ ምንም ሳትሰራ ተኛታ እንደዋለች ነው፡፡ አንድም ድካሟን ሁሉ ከንቱ አስቀርተው ምስጋናዋን እንኳን ይነፍጓታል፡፡ አንድም ጥሩ ላደረገ መልካም ምልሽ መስጠቱን ይዘነጉታል፡፡

በዚህ በአበበችና በደብሪቱ ተራክቦ እና በደብሪቱና በእንግዶቹ ተራክቦ ውስጥ የሚፈጠሩት ግጭቶች የግብረገብና የተፈጥሮ ግጭቶች ናቸው፡፡ የደብሪቱና የአበበች ግጭት ውስጥ ከተፈጥሯዊ ስሜት የመነጨ እኔ አውቃለሁ ባይነት፣ ግብዝነት፣ እራስ ወዳድነትና የበላይነትን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶችን የሚያሳዩ ባህሪያት አሉ፡፡ ግብረገብ ይህንን ባህሪ ማለሳለስ ሲያቅተውና ቤቱ በጥፋት ሲሞላም ይቃኛል፡፡ የደብሪቱ ከላይ በጥቂቱ ተዳሷል፤ በኋላም ይመጣል፡፡ በመቀጠል የአበበችን እቃኛለሁ፡፡

የደብሪቱ ልጅ ሶፍት ስትፈልግ ሌላዋ ሴት የተጠቀመችበትን "በሊፒስቲክ የተጨማለቀ" ሶፍት ታወጣለች፡፡ ተጸይፋ ስትወረውረው ጢም ብሎ የሞላው ዶሮ ወጥ ውስጥ ይገባል፤ በፍጥነትም ከወጡ ቅባት ጋር ይዋሃዳል፡፡ አበበች ዶሮ ወጡ ውስጥ ቆሻሻው ሲገባ "ሲያሳዝን" ትላለች፡፡ አንድም እመቤቷ ያዘዟት አልጫ ዶሮ እንድትሰራ ነበር፡፡ እሷ ግን በበርበሬ ሰራችው፡፡ ይህም ባንድጎን እመቤቷ የነገሯትን መስማቷን ግን አለማስተዋሏን ይጠይቋል፡፡ በራስ ምታቷ ቢመሃኝም ቅሉ ሽፋን ነው እንጂ ምን መስራት እንዳለባት ታውቃለች፤ ያንን ሁሉ ምግብ

በአይነቱና በልኩ ስትሰራ ራስ ምታቱ አላገዳትም። ስለዚህ ትዕዛዛቸውን አለማክበሯን፣ ንቀቷን፣ ምንም እንደማያመጡ ማሳያዋ ነው። በሌላ በኩል የሚመጣው እንግዳ የሚፈልገው ዶሮ መብላት ነው፤ አልጫ ዶሮ። ቃልም ተገብቶለታል። ይህም በራሱ ሊበላ ጓጉቶ የመጣውን ምግብ የምታዘጋጀው ሎሌይቱ ስለሆነች ጓጉቶ እንዲቀር ታደርገዋለች። በዚህ አበበች ሰርቶ የመብላት አቅማቸው በሷ ቁጥጥር ስር እንደሆነና የሷ ሃያልነት እንደሚበልጥ፣ ሰርታ የምታበላቸው የምግባቸው እመቤት እሷ ሎሌዋ እንደሆነች ለማሳየት ትጥራለች። በሙያዋ የጌቶቹን አድናቆት ማግኘቷ አይቀርም።

በሌላ አቅጣጫ ሲታይም ዶሮው አልጫ ታዞ ቀይ ቢሰራም እንኳ ለመብላት ጀምረው ነበር። በርበሬ አቃጣይ ነገር ነው። ልታቃጥላቸው ነበር። እንዳይተውት የምግቡ ሽታ እንዲበሉ ይጋብዛቸዋል። ስለዚህ ሎሌይቱ የፈቀደችውን እንዲበሉ ይገደዳሉ፤ የእነሱ ፍቃድ የሚሰራው በንግግር፣ በስድብና ሊታይ በማይችል ረቂቅ ሃሳብ ነው። አበበች ግን በድርጊቷና በስራዋ ታሳያቸዋለች።

አበበች በወጡ መጉደፍ ያዘነችው በቀጥተኛ አቀራረቡ በራስ ምታት እየተንገላታች ለመደነቅ አጣፍጣ የሰራችውን ምግብ በቅጡ ሳያጣጥሙት ሊደፋ በመሆኑ ነው። እንደዚሁም አበበች ያዘነችው ለቅጣት ያዘጋጀችው በርበሬ ዓላማውን ከግብ ባለማድረሱ ነው። በጣም ያሳዘናት እንዳውም ይህ ይመስለኛል። በሌላ በኩል ወጡ ውስጥ ቆሻሻው ሲገባ ደብሪቱ የሚናገሯትን ማየት ይቻላል።

የዚህ ጊዜ ደብሪቱ ለአበበች "አሻሽለሽ ብይው" ይሏታል። አበበች የሰጠችው ምላሽ "እኔ እቴ"(88) የሚል ነው። ለምንድን ነው አሻሽላ ለመብላት ያልፈቀደችው? አንድም እነሱ ያጎደፉትን ሲጨመር የተጸየፉትን እንደማትነካው መግለጿ ነው። ወጡን ያቆሸሸው የጌቶቹ ዘር ነው። የሚጸየፉት ራሳቸውን እንጂ ሎሌውን አይደለም። አበበች የሰራችውን ምግብማ ሁሉ ሊበላ ጓጉቶና ተዘጋጅቶ መጥቶ ነበር። የሎሌዋን ንጽህና ስላጎደፉት ነው ያዘነችው። እሷ ብቻ አይደለችም፤ ጌቶቹም አዝነዋል እንዳውም በሽቀዋል። "አሻሽይው" ሲሏትም እነሱ ያጠፉትን ጥፋት እሷ ማደስ እንደምትችል እየገለጹ ነው። የሰራው ነው ማሻሻል የሚችለው በሚል እምነት።

ይህ ይዞት የሚመጣው ሌላ ጉዳይ አለ። ይኸውም እነሱ የእሷን ትራፊ እንጂ እሷ የእነሱን ትራፊ እንደማትበላ መግለጫዋ ነው። እንዴት? ቢሉ እየከተፈች ሳለች እንዳማራት በድልህ

ለውሳ ጥሬ ስጋ የጎረሰችው አበበች ናት። ወጡንም ስትሰራው ለጨውም ለጣዕምም መስተካከል መቀማምሷ አይቀሬ ነው። እመቤትየዋ ግን ራሳቸው በፈጠሩት ስርዓት ታስረው ያማራቸውን ማድረግ አይችሉም፤ የሰራተኛቸውን ያህል ነጻነት እንኳን የላቸውም።

"‹አንቺዬ……ድንቅ አይደል ይሔ ነገር……ወጡን ብዙ ድልህ አድርጊበት› አሉና ተመልሰው ወጡ። ‹ብዙ ድልህነቱ› ውሸት መሆኑ ለአቤ ይገባታል። ድልህ መላሳቸው እንዳያስገምታቸው የሰጥዋት ለተወሰኑ ሰከንዶች አገልግሎት ብቻ ያላት ምክንያት እንደሆነች ታውቃለች።" (79) ሰራተኛቸውን እንዲህ የሚያፍሯት ከሆነ፣ እኩያዬ ነው፤ ብለው የሚያምኑትን ምን ያህል እንደሚያፍሩና በስጋት እንደሚኖሩ መገመት አያቅትም። እያንዳንዷ እንቅስቃሴያቸው በጥንቃቄና በስጋት የተሞላች ናት። ካጎደፉት በኋላ እንኳ ትደፋዋለች እንጂ አትበላውም። በሌላ በኩል ደግሞ በበርበሬ ሰርታ ልትቀጣቸው የነበረው ጌቶቹን ነበር። እርሷ ለምን ትቀጣለች። ለዚያ ነው "እኔ እቴ" ብላ በግልጽና በደፈናው የመለሰችው። ደብሪቱ የልጆቻቸውን አላዋቂነት በብልሃት ሊያሳዩቸውና ሊቀጧቸው እንደሚፈልጉ ሁሉ አበበችም ይህንን መንገድ ትከተላለች። ተቀጪው የተሻልኩ ነኝ ብሎ እያሰበ ተበልጦ ይገኛል። የሚከተለው መርህ ሌላ፣ የሚኖረው ኑሮ ሌላ ይሆናል። ይህንንም ደብሪቱ እመቤትነታቸውን፣ የበላይነታቸውን አስጠብቀው የኖሩ እየመሰላቸው ግን ሳይሆን ሲቀር የሚያስቃኝ ማስረጃ ላቅርብ።

ሌላው ትዕይንት ቤቱ ተተረማምሶ የሰራችውን ሳያጣጥሙት ሲበላሽ "‹እንዲህ ለፍቼ› አለች አበበች። ‹ምን ለፋሽ…….ለራስዋ አሞአት……ተጋድማ ነው የዋለችው።› አሉ ደብሪቱ።" (86-87) አበበች ሁሉን ነገር ስትሰራ፣ ስትለፋ እንደዋለች ያውቃሉ፣ ግን ይክዷታል። "ምን ለፋሽ" ይሏታል። ይህ ንግግር አንድም ውሸት ነው፤ አንድም መልካም ነገርን በእኩይ መመለስ ነው። አበበች ለሰራችው ጥፋት (አንድም ስጋውን በመጉረሷ፣ አንድም ዶሮውን በበርበሬ በመስራቷ) ድኳሟን ከንቱ በማስቀረት ይቀጧታል። የሁሉም ጥፋቶች ውጤት ወደ አበበች ድካምነት ይቀየራሉ፤ በዚህም እሷ በማቃጠል ልትቀጣቸው የነበረውን ይበቀሏታል።

ደብሪቱ በበኩላቸው እሳቸው የሌላቸውን ግብረገባዊነት ለልጆቹ ለመስበክ ይጥራሉ። ይህም ከልጃቸው እጮኛ ጋር በሚያደርጉት ጭውውት ወቅት ይገለጻል። ጉዳዩ ከብሔር ጋር ተቆራኝቶ የቀረበ ቢሆንም ስለ አንድ ጉድጓድ ቆፋሪ ሰው ያወጋሉ። ሰውዬው የደብሪቱን ጉድጓድ ቆፈረ። በመጀመሪያ የተስማሙት አምስት ብር ነበር። እራሳቸውም እንደሚገልጹት "ትራክትር አይሰራውም የሰራውን ስራ። እውነቴን ነው። ምጥማጥ እንደዚያ አትሰራም።" (83) ሰርቶ ሲጨርስ አስር ብር ነው አለ፤ ምንም እንኳ ታሪኩ የውሸት ፈጠራቸው ውጤት ቢሆንም።

ምናልባት ስራው ስለበዛበት ይሆናል ገንዘቡን የጨመረው፡፡ በታሪኩ ሊያስተምሩ (ሊሰብኩ) የሚፈልጉት ነገር ምንድን ነው? በታሪኩ ተመርተን ከሄድን ጉራጌ ለስራ የሚወዳደረው የለም፣ ኅበዝ ነው፤ ግን ገንዘብ ይወዳል፡፡ ገንዘብ አብዝቶ መውደድ ደግሞ ጥሩ አይደለም ነው፡፡ ይህን ለማለት በግቢያቸው ተቆፍሮ ስለማያውቅ ጉድጓድ ምን አስወራቸው? ለምንስ እያሞካሹ ስለ ስራው ድንቅነት ያወራሉ? በመጀመሪያ ደብሪቱ አይነኬነታቸውን ማሳየት ፈልገዋል፡፡ አምስት ብር የተዋዋሉትን ስራ አስር ብር ነው ሲላቸው፡፡ “ውሸታም፣ ሌባ” አላሉትም፡፡ “ባይሆን ላንተ ስድስት ብር ላድርግልህ” እንዳሉት ነው የሚገልጹት፡፡ ከዚህም በኋላ አይሆንም ብሎ ወደ ሕግ ሰዎች ለመሄድ ሲነሳ ከንትርኩ ብለው አስር ብሩን ረግመው ሰጡት፡፡

ስራውን ሲነጋገሩ መጓጓቱንና ደሃ መሆኑን ገምተው እሱ እንዲሰራው በማድረጋቸው ደግነታቸውን ይገልጻሉ፣ እሳቸው ለብር ፍቅር እንደሌላቸው ለመግለጽም ያልተዋዋሉትን ገንዘብ ሰጡት፡፡ ሲሰጡት ረገሙት፤ እርግማናቸውም ደርሶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መኪና ገጭቶት እግሩ ተሰብሮ አገኙት፤ በዚህም እሳቸው ሊነኩ የማይገቡ፣ ሊከበሩ ሊገዙላቸው እንጂ ሊጋፏቸው እንደማይችሉ እመቤት መሆናቸውን ይገልጻሉ፤ ውሸት፣ ማጭበርበር፣ ቃል ኪዳንን አለማክበር ተገቢ እንዳልሆነ በታሪካቸው ለማስተማር ይሻሉ፡፡ በዋናነት ደግሞ ገንዘብን አጥብቆ መውደድ የመጥፊያ መንገድ መሆኑን ለማስገንዘብ ይጥራሉ፡፡ ግን ይህ እንደታሪካቸው ሁሉ አፋቸው ላይ እንጂ ኅሊናቸው ውስጥ የለም፡፡ የሰራው ስራ በጣም ብዙ ነው፤ ጥሩም ነው፡፡ በዚህ እንኳ ይገባዋል ብለው አልጨመሩለትም፤ ወይም የዋሸው ስራው ስለበዛበትና በሚገባ ስለሰራው ነው ብለው አላሰቡም፡፡ ክብራቸው ተነክቷል፤ ሎሌ ሆኖ እመቤቱን ዋሽቷልና፣ ሲቀጥል እርሳቸው የገንዘብ ፍቅር ከሌላቸው ለምን የጠየቃቸውን አልሰጡትም? ርግማኑንስ ምን አመጣው? በሌላ በኩል ግብረገባዊ የሆነው፣ አስተምህሯቸው እንጂ ተግባራቸው ስላልሆነ ግብረገብን ሊያስተምሩ አይችሉም፡፡ የእርሳቸው ውጤት የሆኑት ልጆአቻቸውም ተመሳሳይ የሖነ ባህሪ ነው ያላቸው፡፡

ድግሱን ከደገሱ በኋላ ለምን መልሰው እንዳይበሉ በማድረግ ሊቀጧቸው ፈለጉ? ደግሞም ቅጣታቸውን ምግቡ ያወቀ ይመስል ማንም ሰው ሳይበላው ተተረማምሶና ተበላሽቶ ለምን ቀረ? እንዳይበላ የፈለጉት ምግብ ሲደፋ ለምን ተበሳጩ? ለምንስ አጉረመረሙ? ሌሎችን ለመቅጣት ቢያስቡም እራሳቸውም ጭምር ናቸው የሚቀጡት፡፡ መብላት እየፈለጉ የሚወዱት ምግብ ተበላሽቶ ይደፋል፡፡ የደብሪቱ የቅጣት ቀስት አቅጣጫው ወደ ሌላ ቢሆንም እሳቸውም የቅጣቱ ሰለባ ናቸው፡፡ ጥፋቱን ያስነሱ ሰዎች ሁሉ፣ የሌላውን ስራ የማበላሸት፣ በሌላው ላይ ስራ

ለመጨመር፣ ፍላጎት ለመዝጋት ምክንያት ይሆናሉ። ስርዓቱን ጠብቆ ሲገነባ (ሲሰራ) የተዋለውን ሁሉ ይንዱታል። አንዱ ያስተካከለውን ሌላው ያበላሻል። አበላሺው የጥፋተኛነት ስሜት ስለሚሰማው ይከፋል፤ ይደበራል። ከድብርቱ የሚወጣው በሌላው ሰው ጥፋት ነው። መጀመሪያ ባጠፋው ሲስቅ የነበረውም ሌላ ጥፋት ውስጥ ተሳታፊ ይሆናል። ሁሉም ሰው በጥፋት ሲሳተፍ ነው ተመሳሳይ ስሜት የሚናራቸው። በራሳቸው ካልደረሰ በቀር የሌላው ሃዘን ተካፋይ አይሆኑም።

ሌሎች ሊያደርጉት አይገባም የሚሉትን ነገር እራሳቸው ያደርጉታል። ግብረገብዊ ለመሆን የሚጥሩት በደመነፍስ ነው። እሴቶቻቸው ከጥፋትና ከግጭት ሊያድኗቸው አልቻሉም። የግብረገብ መሰረታቸው ደመነፍስ ነው። ለደመነፍሳቸው የሚስማማውን ነው ለሽፋንነት የግብረገብ እሴት አድርገው የሚደነግጉት። ለዚህም ነው ግብረገብ ደመነፍስን መግታት የሚያቅተው። የቤቱ በትርምስ መሞላት፣ ሁሉም የጥፋት ተሳታፊ መሆኑ ለዚህ ማሳያ ይሆናል። የተሰናዳው መበለሻሸቱም የግብረገብ ቅጥ መጥፋትን ያሳያል። የሚታመንበት ነገር ሌላ፣ የሚወራው ነገር ሌላ፣ የሚደረገው ነገር ሌላ በመሆኑ ተፈጥሮና ባህል ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ሁሉም ሆዱ ሻክሯል።

ገጸ ባህሪያት እርስ በርስ ይናቆራሉ፤ ያጠፉትን ጥፋት በሌላ ላይ ለማመሃኘት ይጥራሉ። ሌላ ያልኩት ሰው ብቻ አይደለም ከዛም የበለጠ ወደ እምነት ውስጥ የሚገባ ነው። ዶሮ ወጡ ውስጥ ቆሻሻ ሶፍት ማን እንደጣለ እያወቀች “ቄስ አልባረከውም መሰል” ብላ የደብሪቱን መንፈሳዊ ሕይወት ለማብጠልጠል ትሞክራለች። በሌላ አንጻር ደግሞ በጥፋተኛነታቸው ውስጥ የልዕለ ተፈጥሮ እጅ እንዳለበት ለማመላከትና ራስን ከተጠያቂነት ለማዳን ነው።

የእናትነት ርህራሄ፣ ጭንቅና ባህሪያት ዋጋ አጥተው እናያለን። ደብሪቱ ልጆቻቸው ሲያጠፉም እንግዶቹ ሲያጠፉም እኩል ስሜት ነው ያላቸው፤ እኩል ነው ሊቀጧቸው የሚፈልጉት፤ ምንም የተለየ እንክብካቤም ሆነ አያያዝ አያደርጉም። ለክብራቸው መጠበቅ እንጂ ለፍቅራቸው ሲብሰለሰሉ አይታይም። ክብራቸው ግን ሲጠበቅላቸው አይታይም። ሰራተኛቸው እሳቸው ከመብላታቸው በፊት ለሳቸው የሚዘጋጀውን ትበላለች፤ ጉድጓድ ቆፋሪው እሱ የፈለገውን የጉልበት ዋጋ እንጂ እሳቸው ያሉትን አይቀበልም፤ ምክንያቱም ክብር ብለው የገነቡት ነገር ከሌሎች የሚችልን እንጂ ውስጣዊ ሰብዕናን የሚያሳይ አይደለም። እንግዶቹ በጉራማይሌ ቋንቋ ቢያወሩ የደብሪቱን ሰብአዊ ክብር አይነካም።

በሌላ ጎን ተቃራኒ ነገሮች ተጣምደው ይታያሉ፡፡ "...ከማቀዝቀዣ የወጣ የበሬ ሽንጥ ሥጋ መክተፊያው እንጨት ላይ ቀይ የህጻን ልጅ ሹራብ መስሎ ወድቆአል፡፡ የተባ ቢላ መሐሉ ላይ ተጋድሟል፡፡ ቢላውና ሹራቡ ሽርክ ይመስላሉ፡፡ ፍቅረኛ ነገሮች ምናምን......." (77) ስጋው በመጀመሪያ ሕይወት ያለው በሬ ነበር፡፡ በድን ያደረገው ቢላው ነው፡፡ አራጁ ሰው ቢሆንም ማረጃው ቢላው ነው፡፡ ቀጥሎም ወደ ትንንሽ ቅንጣት የሚቆራርጠው ቢላው ነው፡፡ ታዲያ ለምን "ሽርክ እና ፍቅረኛሞች" ይመስላሉ ብሎ ገለጸው፡፡ አጥፊና ጠፊ እንዴት ሽርክ ወይም ፍቅረኛ መሆን ይችላል? ሽርክ ሁለት ትርጉም አለው፡፡ አንደኛው በጣም የሚቀራረቡና የሚስማሙ ሰዎችን ቅርበት የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው በጋራ የሚሰሩ (ሽርክና) ገንዘብ ያገናኛቸውን ሰዎች የሚገልጽ ነው፡፡

አበበችንና ደብሪቱን በጋራ የሚያገናኛቸው ነገር ምንድን ነው? የጌታንና የሎሌነትን ማእረግስ የሚያሰጣቸው ምንድን ነው? ገንዘብ ነው፡፡ ምናልባት አበበች ባለ ሃብት ብትሆን ኖሮ ይሄ ሁሉ ታሪክና ተራክቦ አቅጣጫውን ይቀይር ነበር፡፡ ሽርክናቸው (የስራ ግንኙነታቸው) ግን ልክ እንደ ቢላዋና ስጋው ነው፡፡ አንዱ ሌላውን እየቆረጠ፣ እየጎመደ ሌላው እየተቆራረጠ፡፡ ደብሪቱ እመቤት ናቸው፡፡ አበበች ደካማዋ ስጋ ነች፡፡ በደብሪቱ ቤት ስራ እየተገዘገዘች እድሜዋን፣ ጤናዋን፣ ጉልበቷን ቀስበቀስ ቀነጣጥባ የምትጨርስ፡፡ ስጋ ይበላል፤ ንጥረ ነገሩ ወደ በይው ሰውነት ሌላው ወደ መጸዳጃ ቤት እንደሚገባው ሁሉ የአበበች ጉልበት ጠቃሚ ንጥረ ነገር ነው፡፡ ደብሪቱ ተኝተው የሚውሉት፣ በልተው የሚያድሩት፣ ደምቀው የሚታዩት፣ እንግዳ ጋብዘው የሚያበሉት፣ የቆሸሸን የሚያጸዱት በአበበች ጉልበት ነው፡፡ ይህን ጉልበት የሚገዙትም በገንዘባቸው ነው፡፡ እንደፈለጉ በዚህ ጉልበት ማዘዝ ይችላሉ፡፡

በሽርክናው ውስጥ ጥቅም እንደየብልጫው ይለያያል፡፡ 60% ድርሻ ያለው ሰው 40% ካለው ሽርኩ ጋር እኩል ድምጽ የለውም፡፡ አበበችም እንደዚያ ናት፡፡ ትልቁ ባለድርሻ እመቤቷ ናቸው፤ ገንዘብና ክብር ያላቸው እሳቸው ናቸውና፡፡ እሷ የምትገብረው ግን ይበልጣል፤ የሷ ግብር ጉልበቷ ሲሆን የደብሪቱ ገንዘብ ነው፡፡ አበበች ብዙ አውጪ ትንሽ አትራፊ ናት፡፡ ደብሪቱ ደግሞ በተገላቢጦሹ ትንሽ አውጪ ብዙ አትራፊ፡፡ ይህ እየሰራ ያለ የዘመናችን አካሄድ ነው፡፡ ይህንን ስርዓትም በጉድጓድ ቆፋሪው ሰው ትረካ ደብሪቱ አጉልተው ያሳያሉ፡፡

ደብሪቱ ትርጓሜው ደብር ነው፤ ደብር ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ግብረገብ ከሚቀሰምባቸው ቦታዎች አንዱ ነው፡፡ አበባ ተክል ነው፤ የሚያብብን፤ የሚያድግንም ይጨምራል፡፡ ሁለቱ ያላቸው ተራክቦ ሲታይ ግን እንደ ስጋውና ቢላው ሆኗል፡፡ ደብሪቱም የደብርነታቸውን አበባም

የአበባነቷን ስርዓት ይዘው አይታዩም፡፡ በሁለቱ መካከል ልክ የመሰለ፣ ግን ያልሆነ ግንኙነት አለ፡፡ ይም የግብረገብ አስተማሪዎችንና ተማሪዎችን የሚወክል ነው፡፡

### 3.2.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

እርቁ የሚፈጠረው በፍላጎትና በፈቃድ አይደለም፡፡ ደመነፍሳዊነቱ ያየለበት እሱን ለማንገስ ጥረት ቢያደርግም ከአካባቢ በሚመጡ ቀውሶች ጭንቀት፣ ድብርት፣ አሊያም ብስጭት ውስጥ ይገባል፡፡ ሁሉም እንዲህ ሲሆኑ ይታያል፡፡ የዚህ ታሪክ ዕርቅ በተለያዩ መንገዶች ለማጠቃለል ምቹ ነው፡፡

አበበች ስሟ እየተለዋወጠ ይጠቀሳል፡፡ በዚህም ሁለት ነገሮችን ላንሳ፡- አንደኛ "አበበች" የሚለው ስም የሚለወጠው "አበባ" በሚለው ነው አንድ ላይ ሲጠራ "አበበች-አበባ" የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል፡፡ አበባ ተወዳጅ፣ የሰውን ልጅ ቀልብ ማራኪ ነገር ነው፤ ደግሞ እንዳበበች ይገልጻል፡፡ ተራኪው "አቤ፣ አቡ" እያለ ሲያቆለማምጣትም ይስተዋላል፡፡

ደብሪቱን ሲጠራ "ወይዘሮ ደብሪቱ" አንድ ጊዜ ከዚያ በኋላ ግን ደብሪቱ እያለ ነው፡፡ እንደ አበበች አያንቆለጳጵሳቸውም፤ ተጨማሪ ስምም አይሰጣቸውም፤ እስከመጨረሻው ድረስ ደብሪቱ እንዳለ ይዘልቃል፡፡ ልጆቻቸውንና እንግዶቹንም ሲገልጽ "ልጅቷ፣ እንግዳዋ…" እያለ አሰፈረ እንጂ ስማቸውን አልጠቀሰም፡፡

የታሪኩ ማብቂያ ትዕይንት ሲጠበቅ የነበረው ልጅ መጥቶ የተራረፈውን ምግብ ሊበላ ሲል መብራት ጠፋ፤ "መብራቱ አንድ ሁለቴ ተብለጭልጮ ድርግም አለ፡፡ አበበች ሻማ ፈልጋ እስክታመጣ…….ሁሉም ጨለማ ውስጥ በዝምታ ተቀመጡ፡፡" (89) እንግዲህ በታሪኩም ማብቂያ የሚያሳየው አበበች ብርሃንን እስክታመጣላቸው በዝም ጨለማ ውስጥ መቀመጣቸውን ነው፡፡ ምናልባት እሷ ሳታመጣ በፊት መብራቱ ይመጣል፡፡ ምናልባትም ሻማውን አምጥታ መብላቸውን ይጨርሱ ይሆናል፡፡ ደብሪቱ ግን ከገበታው ተነስተዋል፡፡ ምንም እንኳ በገንዘባቸው ሃያል ቢሆኑባትም፣ መብት አልባ ቢያደርጓትም፣ በተለያየ ነገር በሷ ቁጥጥር ስር ሲወድቁ ይታያል፤ ይህም የጌታንና የሎሌን ግብረገብ ተቀባይነት የሚያሳጣ አተያይ ነው፡፡

ከጥንቃቄ ጉድለት የመጣ መስሎ ቢቀርብም አንዱ የሌላውን ጥፋት እያየ ሊጠነቀቅ ባለመቻሉ ሆን ብለው ንቀታቸውንና እነሱ የባሱ ቀጪዎች እንደሆኑ ለደብሪቱ ሊያሳዩ ያበሩ ይመስላሉ፤ ምክንያቱም በስተመጨረሻ ቀድመው ከገበታው ወይም ከመቀመጫቸው የሚነሱት እሳቸው ናቸው፡፡ የሌሎችን የምግብ ፍልጎት ለመዝጋት ቢያሴሩም የእርሳቸው ከሁሉ ቀድሞና ብሶ

ይዘጋል። ምንም አልበሉም ማለት ይቻላል። ቀድመው መነሳታቸውም የሽንፈታቸው ምልክት ነው። እርስ በርስ የሚደርስባቸው መሸናነፍ ቅስማቸውን ስለሚሰብረው ወደ ዝምታው ይሄዳሉ። ይህ አንድም በጽሞና ስለ ግብረገባዊ እሴቶቻቸው እንዲያስቡ እድል ይሰጣቸው ይሆናል።

"…አደፍራሽ ካለ ንፁህ ውሐ መጠጣት ያዳግታል ይላሉ። ውሐውን ማን ደፍርስ አለው? የማንም ደካማ ውሃ በደፈረሰ። ቡናና ወሬ መቼም ቦላሌና ዚፕ ናቸው። ቦላሌው ሃፍረት መሸፈኛ። ቦላሌዎች ሁሉ ደካማ ባለ ቀዳዳ ሊከዱ ያኮበኩቡ። ዚፑም ይህን የድክመት ሃፍረት መሸፈኛ። መሸፈኛ በመሸፈኛ።" (81) ይህ ሀቲት አንደኛ እራት ቀርቦ ድብልቅልቁ ከመነሳቱ በፊት የሚደረግ ስለሆነ ለቀጣዩ ክስተት ጥቁምታ ነው። "አደፍራሽ ካለ ንፁህ ውሐ መጠጣት ያዳግታል ይላሉ።" ይላልና። በሁለተኛነት ጥፋትን ማመን ሳይሆን በሌላ ላይ በማሳበብ ሃላፊነትን ላለመውሰድ የሚቀርብን እርባና ቢስ ምክንያት ያስቃኛል። ውሃ የሚያደፈርሰው ነገር እስከ ሌለ ድረስ እንደማይደፈርስ ይታወቃል። ቢደፈርስ ግን የአደፍራሹ እንጂ የውሃው ድክመት አይደለም። ሦስተኛው ቡናውና የወሬ ነገር ነው። ወሬ ለማውራት ቡናን ሽፋን ያደርጋሉ። ቡና እየተጠጣ ዝም አይባልም፤ ስለ ፈለጉት ነገርም ይወራል፤ ስለ ሌላው፣ ስለ ራስ ሲወራ አይታይም። ወሬ የቡናው መሸፈኛ ሲሆን ቡናው ደግሞ የወሬው መሸፈኛ ይሆናል። ይህ የቦላሌና የዚፕ ምሳሌም የባህል ወኪል ነው። አንዱን ድክመት ለመሸፈን ወይም ኢ ግብረገባዊ ድርጊትን ግብረገባዊ ገጽታ ለማላበስ የሚፈጠር "አርቴፊሻል" ባህልን የሚያሳይ ነው። "መሸፈኛ በመሸፈኛ።" የሚለውም ይህን ለማስረገጥ ነው።

"በቋፍ ያለን ሕዝብ፣ ቂም የሚያደንቀውን፣ ብድር በምድር የሚቀናውን ሕዝብ መቼም ማባላት ቀላል ነው። ዋናው ማስጀመሩ ነው።" (84) ይህን የሚለው እራት እንዲጀመር አስተያየት በሚሰጡበት ወቅት ነው። የሕዝቡን የሰብዕና መዝቀጥ ከሚያሳይባቸው ሀቲቶች ውስጥ አንዱ ነው። የዚህ ማኅበረሰብ መጨረሻ የሚሆነው ደግሞ ጨለማና ከገበታ መነሳት ነው። የሁሉም የጋራ ጉዳይ የሚሆነውና የሚካፈሉት ገበታውን ነው። ይህ ገበታ ግለሰቦችን ከተለያየ ቦታ በአንድ አምጥቷቸዋል። የዚህ ገበታ መበላሸት መተራመስ የገበታው መፈጠር ምክንያት የሆኑት ደብሪቱ ደግሞ ከገበታቸው ይነሳሉ። መነጠል አለ፤ መገለል የራስን አቋም ይዞ መውጣትን የእያንዳንዱ ሰው መነጠል ደግሞ የፈጠረው የማኅበራዊ ቀውስ አለ። ከዚህ የከፋው ደግሞ ከራስ ጋር መጣላት ነው።

ደብሪቱ አበበችን ይክዷታል፤ ሲክዱ ግን ራሳቸውን እንጂ አበበችን አይደለም። አበበችማ ስራውን ሰርታ ጨርሳለች። ይህን ደግሞ እሷም እንግዶቹም ያውቃሉ። ሁሉም የሚያውቀውን ነገር መካድ ደግሞ ራስን ማታለል እንጂ ሌላን አይሆንም። ለራሳቸውም ትክክልና ስህተቱ ተምታቶባቸዋል። የፈጠሩት ታሪክ እንኳ የውሸት መሆኑን እያወቁ "እኔ እውነቴን ነው" ደጋግመው እያሉ ነው የሚተርኩት። ሊያስተምሩት የሚፈልጉት ነገር በመጀመሪያ ራሳቸው አልገባቸውም፤ አላመኑበትም፤ አልኖሩትም፤ በማስመሰልም የተሞላ ነው። ለዚያም ነው የጀመሩትን መጨረስ እስኪያቅታቸው ድረስ የሚያወሩት ግራ የሚገባቸው።

በስተመጨረሻ መብራቱ ይጠፋል። ጨለማ ውስጥ ይቀራሉ። ይህም ወደፊት የሚፈጠሩትን የሰብዕና ዝቅጠቶችና እኩይ ምግባሮች መስፈን እንደ ራዕይ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። ለአሁኑ ግን ይህንን ጨለማ እንድትገፍ የምትጠበቀው አበበች ናት፤ አበበች ሁሉም ሰዋዊ መብቶቿ የማይጠበቁላት፣ ድካሟ ከንቱ የሚቀር፣ እኩልነትና ነጻነት የተነፈጋት ናት፤ ስለዚህ ግብረገብን ወክላ የመጣች ናት። በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሰረተች ግብረገብ። በስሟም እንደሚገለጸው አበባዋ አብባለች። አበባ አበበ ማለት ሌላ ዘር ለመተካት ዝግጁ ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ የገቡበት ጨለማ ብጥብጡና አሽሙሩን አስቀርቶ ጸጥ ሲሉ፤ "ሁሉም ጨለማ ውስጥ በዝምታ ተቀመጡ።" ተረጋግተው ደመነፍሳዊ ስሜታቸውን ከግብረገብ ለይተው (ጨለማው ደመነፍሳዊነትን ስለሚወክል) ሲያውቁ ሎሌ አድርገዋት የነበረችውን አበበችን ብርሃን እንድትፈጥርላቸው እንደጠበቋት ሁሉ ግብረገባዊነት የማስፈን ተስፋን ይይዛሉ።

ለዚህ የሚያግዛቸው አንድም የበፊቱን ድንጋጌ፣ በቀልን ያነገበ ቅጣት፣ ኢ-ግብረገባዊነት የተሞላ ሰብዕናን ይዘው የነበሩት የደመነፍሳዊ ፍላጎት ወካይ የሆኑት ደብሪቱ ከገበታው፣ ከቡድኑ፣ ከማዕዱ ተነጥለው መውጣቸው ነው። ከቡድኑ ቢወጡም በአንድ ቤት ውስጥ ስለሚኖሩ እሳቸውንም ያማከለ ግብረገብ ይፈጠራል እንጂ ተፈጥሯዊ ስሜትን የሚገፋ ወይም ያገነነ ባህል አይመሰረትም።

## 3.3 "ስንዝሮ"

### 3.3.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

በዚህ ታሪክ ውስጥ ዐቢይ እና ደሳለኝ እንዲሁም ጥንቅሽና ወለላ የጉዳይ ማጠንጠኛ ናቸው። የመጀመሪያው የመቼት ገለጻ የሚያመለክተው አንድ ያረጀን ቡና ቤት ነው። በዚያ ቡና ቤት ውስጥም "ፍቅርና ጥላቻ፣ ክፋትና ደግነት፣ ጥፋትና ልማት" እንደተከናወኑበት ይነገራል። ይህ

ገለጻም በታሪኩ ውስጥ ለሚከሰቱ ተቃራኒ ተጣማጅ ተግባሮች ምልክት የሚሆን ነው። በአጠቃላይ ስለ ቦታው ሲገለጽ መድረክ፣ የሚመጣውም ሰው ደራሲና ተዋናይ እንደሆነ ነው። ዐቢይና ደሳለኝ የተዋወቁት እዚህ ቡና ቤት ውስጥ ነው። ጓደኛሞች እንዲሆኑ ያመቻቸው ደግሞ ደሳለኝ ነው። ዐቢይ በሱቅ ንግድ ይተዳደራል። የቤተሰቦቹ ነው። ቤተሰቦቹ በሕይወቱ ውስጥ ሰፊውን የውሳኔ ደርሻ ይወስዳሉ፤ ስለዚህ ጥንቅሽ የምትባልን ልጅ የስለት እጮኛ አድርገው ይሾሙለታል። አቢይና ጥንቅሽ አይስማሙም። ደሳለኝ ቡና እንዲጠጡ ወደዚያች ያረጀች ቡና ቤት ይወስደዋል። በዚያ የምትሰራውን ወለላን ሲያያት ደስ ትለዋለች። እርሷም ደስ ይላታል። እዚህ ጋ ልብ ሊባል የሚገባው አንደኛ ወለላ ደስ የሚል ልጅ እንደሆነ ስትናገር ስራዋ ይህን በማድረግ የሚጀመር ስለሆነ ከልቧ ላይሆን እንደሚችል ነው። ሁለተኛው ነገር ዐቢይና ወለላ እንዲተዋወቁ፣ እንዲቀራረቡና እንዲግባቡ ሲረዳ የነበረው ደሳለኝ ነው። ከዚያን እለት አንስቶ ግንኙነታቸው እየጠነከረ መጣ። ደሳለኝ ስለራሱ ሕይወት ትንሽ ነገሮችን እየነገረ ብዙ የዐብይን ሚስጥሮች ሊያውቅ ቻለ። በዚህ ጊዜ ጥንቅሽ አብሮ አደጉ እንደሆነችና ቤተሰቦቻቸው እንዲጋቡ እንደሚፈልጉ ነገረው። (…ቀደም ብሎ፣ ከአንዲት ደስ ከምትል ቀይ ልጅ ጋር በመንገድ ሲጓተት በተደጋጋሚ አጋጥሞኛል በማለት መግለጹ ልብ ይባልልኝ።) በመጨረሻ ደሳለኝና ጥንቅሽ፣ ዐቢይና ወለላ ሲጋቡ ወንዶቹ ለሰርጋቸው ይጠራራሉ።

በዚህ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ግጭቶች አሉ። አቢይ የመማር ፍላጎት ነበረው። “ገና አስራ አንደኛ ክፍል ሲጀምር ትንሽ ሱቅ ቢጤ ቀልሰው እዚያች ውስጥ ወተፉት።” (35) ቤተሰቦቹ ግን እንዲማር፣ እንዲለወጥ፣ አልፈቀዱለትም። “መንፈሱን ነፋፍቶት የነበረውን የዕውቀት ፍላጎት ያተነፈሱበትን እናትና አባቱን እየቆየ ጠላ……ጠባብ ሱቅ ውስጥ በማበጠሪያ፣ በርካሽ የቆዳ ቀበቶ ሽታ፣ ከአናቱ በላይ በሚንቦገቦግ 60 ቁጥር አምፖል፣ በፀጉር ቅባት፣ በሞሪንጋ ቆርቆሮዎች መሃል……አለበት መርገጡ……ነፍሱ አለመለወጡ እየቆየ አስጠላው።” (35-36) ሱቁ ውስጥ ለአስር አመት ሰርቷል፤ ለውጥ የለውም ተመሳሳይና ዘወትራዊ ነገሮችን ይሸጣል፤ እዚያ ውስጥም ይኖራል፤ ለውጥ የለውም፤ እንደሚያስበውም ከዚያ የተለወጠ ወይም የሰፋ ነገር ማየት አይችልም። አስተሳሰቡ፣ የሕይወትን መንገድ ማያ መነጽሩ እንዳይማር በማድረግ ገድበውታል። እናቱን ማሳዘን ስለማይፈልግ አድርግ የተባለውን ነገር ሁሉ እሺ ይላል፤ ነገር ግን ሁሌ በረብሻ ውስጥ ነበር፤ ይናደዳል፤ ተስፋ ይቆርጣል፤ ኑሮውን ይጠላል፤ ቤተሰቦቹንም ይጠላቸዋል። በቀጥታ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚያደርገው ግጭት ባይኖርም ኅሊናው ውስጥ ብጥብጥ አለ።

በሌላ አንጻር ሲታይ ዐቢይ መማር የሚፈልገው እንደፈረንጆቹ ለመሆን ነው፡፡ እንደነሱ መሆን ማለት ዕውቀትን ማካበትና በሱም መመራመር ብቻ አይደለም፡፡ የእሱን ማንነት አጥቶ የነሱን ባህሪ ይወርሳል፡፡ ልክ ጥንቅሽ ፈረንጅ አምላኪና የነሱን የኑሮ ብሂሎች (በተወሰነ መልኩም ቢሆን) ተከታይ ሆና የማህበረሰቧን እሴቶች እንዳፈረሰችው፡፡ (በተክሊል እንድታገባና ወሲብ ከትዳር በኋላ እንዲመጣ የሚያሥተምሯትን የቤተሰቦቿን ድንጋጌ ትታ በስውር ካማራት ጋር ወሲብ መፈጸሙን መርጣለች፡፡ ይህም በዘመናዊነቷ ውስጥ የመጣ እንደሆነ ቆየት ብሎ ይጠቁማል፡፡) ስለዚህ ቤተሰቦቹ እንዳይማር ሲያደርጉት እሴቶቻቸው እንዲጠበቁና ባህላቸው እንዳይበረዝ በመስጋት ነው፡፡ በቀጥታ እንደሚገለጸው ዘመናዊነትን ለመውረስ ሲጥሩ ደመነፍሳዊ ስሜታቸውን ለማርካት የሚጠቅማቸውን እንጂ አንዳች ፋይዳ ለማኅበረሰቡ የሚያበረክት ነገርን አይደለም፡፡ የሚወርሱትንም ነገር ከእሴታቸው ጋር እንዲጣጣም አድርገው መጠቀም ስላልቻሉ የባህል ወረራ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ ሁለት ጽንፍ ይፈጠራል፡፡ ቤተሰቦች ፍጹም የራሳቸውን ባህል ተቀባይና ሌላውን የሚገፉ፤ ተፈጥሮን አምቀው ጭምት ማድረግ የሚፈልጉ ሲሆኑ ልጆች ደግሞ የራሳቸውን ትተው የውጪውን አለም ባህል ወርሰው ባሻቸው መንገድ ተፈጥሯዊ ስሜታቸውን ለማርክት የሚተጉ ይሆናሉ፡፡ ይህም እንዲበጣበጡ ያደርጋል፡፡

ዐቢይ ትምህርት እንዳይማር ታግዶ ሱቅ ውስጥ ቀርቷል፡፡ ጥንቅሽ ደግሞ ተፈቅዶላት ትማራለች፡፡ በሁለቱ መሃከል ከሚፈጠረው ግጭት ውስጥ አንዱ በስልጣኔ ዙሪያ የሚነሳ ነው፡፡ "ሥጋ ወደ ለበሱ ምድር ላይ ወዳሉ ራሱን ወደ መሰሉ አበሾች አታሳየውም……በአይነ ሥጋ ወዳላያቸው፣ በስልጣኔ ስለገፉ የሚንቁት የሚመስሉትን፣ እሱም መኾን ወደሚመኛቸው ነጮች ነው፡፡" (37) አቢይና ጥንቅሽ የተለያየ አስተሳሰብ ያላቸው አድርጎ ቢያቀርባቸውም ሁለቱም አንድ አይነት አስተሳሰብ አላቸው፡፡ ሁለቱም የፈረንጆቹን የኑሮ ዘይቤ መውረስ ይሻሉ፡፡ አቢይ ቤተሰቦቹ ስላልፈቀዱለት እቤት ቢቀርም በምኞትና በጥንቅሽ አማካኝነት ይኖረዋል፡፡ ጥንቅሽ መንገዳቸውን ተከትላ በመሄድ የሰለጠነች ቢመስላትም በስጋት ውስጥ ነበረች፡፡ በገለጻው እንደሚጠቁመውም ውስጧ ያልሰለጠነ ላይዋ ግን ስልጡን ነው፡፡ ለዚህ ነው ከባህሏ ጋር መግባባት ያልቻለችው፤ የምታስበው፣ የምትኖረውና መኖር የምትፈልግበት መንገድ ተጣጥመው መጓዝ ስላልቻሉ፤ ወይም እሷ ማስኬድ ስላልቻለች፡፡

የዐቢይ ቤተሰቦች እራሳቸው የማኅበረሰቡን እሴት ጠባቂዎች አይደሉም፡፡ ወንድ ልጅ ቤት ውስጥ ከመዋል ይልቅ የመማርና ወጥቶ የመስራት እድል አለው፡፡ ይህን እሴት በመገልበጥ እነሱ የሌላቸውን ልማድ በልጃቸው ሕይወት ውስጥ ለመኖር ይጥራሉ፡፡ እነሱ የሌላቸው

ለመሆኑ እናትየውና አባትየው ያላቸውን ተራክቦ ማየቱ በቂ ነው። በዚህ አይነት ቤተሰብ ውስጥ ስላደገም ነው በራሱ መወሰንና ሃላፊነትን መውሰድ የሚያቀውተው።

ዐቢይ እሴቱን ለመጠበቅ (በግድም ቢሆን) እየሞከረ እንኳ ደመነፍሳዊ ፍላጎቱ እኩይ ድርጊትን እንዲያደርግ ይገፋፋው ነበር። ወሲብ ተፈጥሯዊ ስሜት ነው፤ ይህ ስሜት እንዲስተናገድ ካልተደረገና ከታመቀ በራሱ ሰብሮ ይወጣል። ይህ ሲሆን ደግሞ ተፈጥሮ ይገዛል፤ ባህል አቅም ያጣል። ጥንቅሽ አቢይ እንዲጋቡ ሲጠይቃት ትምህርት እንድትጨርስ፣ ሌላም ሌላም ምክንያት ትነግረዋለች። እሱ ደግሞ ዘመናዊ የሚላቸውን ፈረንጆችን መሆን ስለሚፈልግና ተፈጥሯዊ የወሲብ ፍላጎቱ ስለሚያይልበት ለግብረገብ መገዛት ያቅተው ተቅበዝባዥ ይሆናል። ይህ ነገርም ጥንቅሽ ጋ አለ።

ማኅበረሰቡ ወሲብ መፈጸሚያ ጊዜውን ሲያዘጋጅ ከትዳር በፊት ለሚፈጠሩ ክስተቶች (ማርገዝን የመሳሰሉ) ዕልባት ለመስጠት እንዲሁም ከአንዱ ወዳንዱ እየተገለባበጡ መሄድን ከለመዱ ወሲባዊ ችግሮችን መቋቋም አይችሉም። በትዳር ውስጥ ከሆኑና በድንግልና ተጋብተው ከተቀመጡ ግን አንድም ሁለቱም ሌላ ሰውን ስለማያውቁ ችግር እንኳ ቢፈጠር ሳያስተውሉት እንዲኖሩና የፍቺዎች ቁጥር እንዳይበዛ ያደርጋል። አንድም ባሉበት ሁነት ውስጥ እርካታን አግኝተው እንዲኖሩ ያደርጋል። ለምሳሌ አንዲት ሴት ከማግባቷ በፊት ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ ፈጽማ ከነበረ ስታገባ ከባሏ ጋር የምትፈጽመውን ወሲብ ቀድማ ከፈጸመችው ጋር ታወዳድራለች። ምናልባት የበፊቱ የተሻለ ሆኖ ካገኘችው ያንን ማስታወስና እርካታን ማጣት ትጀምራለች። እነዚህን የእርስ በእርስ መጠባበቂያ ድንጋጌዎች ግን በልጆቻቸው ላይ ማስረጽ አልቻሉም፤ ወይም ልጆቹ ያልኖሩትን ሕይወት መልካም ጎን ብቻ ቃኝተው የተሻለ ስለሚመስላቸው ያንን መከተል ይሻሉ።

በሌላ ጎን ማኅበረሰቡ ለድንጋጌዎቹ በቂ ምክንያታዊነት ያለውን ያህል ልጆቹም አላቸው። ተፈጥሯዊ ስሜት መስተናገድን ይሻል። በዙሪያቸው ያሉ ነገሮች ይህ ስሜታቸው ይበልጥ እንዲቀሰቀስ ሊያደርጉ ይችላሉ (ተቃራኒ ጾታ፣ የጓደኛ ወሬዎች…)። ይህ የሆርሞኖችና የተፈጥሮ ክስተት እንጂ የልጆቹ ኢ-ግብረገባዊነት ውጤት ሊሆን አይችልም። ቤተሰቦቻቸው ያሻቸውን እየፈጸሙ እነሱን እንደከለከሏቸው ሊሰማቸውም ይችላል። ቤተሰብ ወይም ማኅበረሰብም ለወጣቶቹ እሴቶችን መስበር አስተዋጽኦ አለው። እሱም ማኅበረሰቡ የልጆቹን ግብረገብ በቋሚ መሰረት ላይ አለመመስረቱና ደመነፍሳዊ ፍላጎታቸው ገኖ ለመውጣት ሲጥር አይሆንም የሚል ኅሊናዊ መርህን መቅረጽ አለመቻሉ ነው። ይህ ማለት ግን ልጆቹ ምንም

አይነት ግብረገባዊ እሴትን አላዳበሩም ማለት አይደለም፡፡ ጽናት እንዲኖራቸው ማድረግ አልቻሉም ማለት ነው እንጂ፡፡

ዐቢይ ከጥንቅሽ ጋር ለመጋባት በድንግልና መቆየት እንዳለበት ያውቃል፤ ግን አያምንበትም፤ ቢሳካለት ኖሮ አንድ ቀን ድንግልናዋን ሊወስድ ሄዶ ነበር፡፡ የተፈጥሮን ጥያቄ መመለስ እንዳለበት (ወሲብ ማድረግ መፈለጉንም) ያምናል፡፡ በዚህ መሃል የሚፈጠረው ግጭት የከረረ ነው፡፡ ሕጉን ቢጥስ አሽሙሩን አይችለውም፤ የእናቱን ሃዘንም ማየት አይፈልግም፤ ቢያከብር ተፈጥሮውን አይችለውም፤ መወሰን አቅቶት ከወዲያ ወዲህ ሲንገላታ፣ በብጥብጥ ውስጥ ራሱን መሆን አቅቶት ዚያናውዝ የሚረዳው ደሳለኝ ነው፡፡ (ደሳለኝ ለአቢይ የሚያዝንለት፣ የሚረዳው ቢሆነም በሌላ ጎን ከታየ ሊያገኘው ያሰበውን ጥቅም ምክንያት እድርጎ ነው፡፡) ቤተሰቦቹ የባህል ተምሳሌት ናቸው፡፡ ይህ ባህልም በእያንዳንዱ ውሳኔ ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ነው፡፡ ማድረግ መሆን የሚፈልገውን ነገር የሚከለክለው ነው፡፡ የአቢይ ቤተሰቦች በተለይ እናትየው ባላቸው ያደረገውን ማድረጋቸው፣ የሆነውን መሆናቸው፣ በእርሱ ፈቃድና ቁጥጥር ስር መውደቃቸው፣ ልጃቸውንም እንደሳቸው እንዲሆን ለማድረግ መጣራቸው አሮጌውን ባህል ያሳየናል፡፡

ወለላ ሰዓቱን ተመልክታ "ለምን የእኔን ወስደህ ይሄን አትሰጠኝም?" (21) ስትለው እንዲለዋወጡ ነበር፡፡ ዐቢይ ይደነግጣል፡፡ መደንገጥን ምን አመጣው? ምክንያቱም ጥያቄው ተራ የሰዓት ልውውጥን የሚመለከት አይደለም፡፡ የወለላና የዐቢይ ሰብዕና ተቃራኒ አይነት ነው፡፡ ወለላ "…ቀልጣፋ ናት፤ የሚብረቀረቅ ልጅነት በረዥም ቁመናዋ ውስጥ የሰበሰበች፡፡ ውድ ናት ሲባል እሰማለሁ……የፈለገችውን ካዘዘች መስማማት ነው፤ ካልሆነ ሁለተኛ አታናግርም አሉ…" (21) የተባለላት ናት፡፡ ያሻትን የምታስደርግ፣ የተቃወሟትን የምትቀጣ፣ ለዚያውም በተፈጥሮ ሊቆጣጠሩት በማይችሉት፡፡ አቢይ ደግሞ ሌሎች በፈቀዱለት የሚመራ ባወጡለት ጎዳና የሚመራ ነበር፡፡ ይህ የግብረገብን ለውጥ መንገድ መክፈቻ ነው፡፡ "ኦ! የሰው ነው ደስ ይለኝ ነበር" (21) በማለት ድንግጥ ብሎ እርስ በእርሱ የተምታታ መልስ ይሰጣል፡፡ ይህ የተፈጥሮና የባህል ነገር በምግብም ይነሳል፡፡

ምግብ ጋብዘኝ ትለዋለች፤ እሺ ይላታል፡፡ ምግቡ መጥቶ ብላ ሲባል አቢይ አይበላም፡፡ ወለላ ላጉርስህ? ስትለው ግን ጉርሻ እንደሚወድ፣ እቤቱም እንዲያጎርሱት የማያደርገው ጥረት እንደሌለ ይገልጻል፤ ግን አይጎርስላትም፤ አልፈለኩም ይላታል፤ ስትጎርስ ግን አይን አይኗን ያያል፡፡ አይን አይኗን ማየቱ መጓጓቱን ያሳብቃል፡፡ የወለላ የላጉርስህና ሰዓቱን ልቀይርህ ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች ለማድረግ ፍላጎት እያለው ግን ሌላ ሃይልን በመፍራት መተውን

ታከው የቀረቡ ናቸው። ወለላ ዐቢይ የያዘውን ባህል እንዲተውና የሷን ባህል እንዲይዝ እየጋበዘችው ነበር።

የሷ ባህል በፈቀደችው ጎዳና መጓዝና የተፈጥሮ ነጻነትን መከተል ነው። የተፈጥሮ ነጻነትን በበጎ ፈቃደኝነት በመተው የማኅበረሰቡን ድንጋጌዎች በራስ ላይ ማስገዛት የማኅበራዊ ሕይወት ምንጭ ነው። ወለላ ይህን አታደርገውም። ሴተኛ አዳሪነት በተለያዩ አሽሙሮች እንደሚወገዙ ያሳያል። ነገር ግን እሷ ያንን ሆናለች። ለምን ሆነች? ፈቅዳ ነው? ወይስ ሁኔታዎች አስገድደዋት? የሚሉት ጥያቄ እዚህ ጋ መነሳት አይችሉም። ምክንያቱም በቀጥታ የቀረበው ነገር የእሷ ሴተኛ አዳሪነት እንጂ ታሪኳ አይደለም። ስለዚህ ወለላ ወደ እሷ አለም እንዲመጣ ትጋብዘዋለች። የእሱ ኅሊና ግን ይህን ይቃወማል (ለጊዜውም ቢሆን)። እኩይ ነው ሲለው የነበረውን ባህሪ ሊቀላቀል ነውና።

በኅሊና የተሰነዱት እሴቶች በመጣሳቸውና ለማመጽ በመነሳሳቱ ምክንያት ጸጸት ውስጥ ይወድቃል። ጥያቄዎቿ ደመነፍሳዊ ስሜቶቹን ከማርካት አንጻር ተገቢ ስለነበሩ አይሆንም ብሎ ሊያልፋቸው አልቻለም። በተጨማሪም የሚማረክላትና የሚመኛት ሆና አግኝቷታል። ግን ያሰረው ነገር አለ። በዚህ መካከል ከሰው ይሰወራል፤ ማንም እሱን አያገኘውም፤ ቤተሰቦቹም፣ ደሳለኝም አያገኘውም። ከተሰወረበት ሲመለስ የሚሰጠው ሃቲት ምን አይነት ቀውስ ውስጥ እንደቆየ ያሳያል።

> *"ከጥንቅሽ ወደ ወለላ መሄድ ከበደኝ......በልጅነቴ ያሹት ጭንቅላቴ........እስከ ዛሬ ድረስ አላንሰራራ ብሎኛል......በርግጥ ወለላ ደህና ባህሪ አላት......ጥሩ ፀባይ አላት......ጥርሴን ነክሼ ለመወሰን ስነሳ በተለያየ ቋንቋ ሰዎች የሚያወሩብኝን የነገር ማዕበል የምችለው አይመስለኝም......እንደ ትንሽ ጆልባ እሰቃያለሁ......የሽሙጡን፣ የአሉባልታውን እሾህ አልችለውም.......እንደ ቁልቋል አለቅሳለሁ" (31)*

ቁልቋል የሚያለቅሰው በራሱ እሾህ እየተወጋ ነው። ይህ ገለጻ የሚያሳየው በራሱ ኅሊና የጎለበቱ ግበረገባዊ መርሖችንና በራሱ አካል ውስጥ በተፈጠረ ደመነፍሳዊ ስሜት መካከል የተፈጠረውን ውጥረት፣ እንዲሁም ውጥረቱ የፈጠረበትን የአእምሮ ህመም ነው። ዐቢይ ምን ያህል እንደተሰቃየና መወሰን እንዳቃተው ሲገልጽ የሚመክረውና የራሱን መንገድ እንዲከተል የሚያደፋፍረው ደሳለኝ ነው።

ሌላኛዋ ገጸ ባህሪ ጥንቅሽ ቤተሰቦቿ አቢይን የስለት እጮኛዋ አድርገው እሱን እንድታገባ ይጠብቃሉ። (የሁለቱ ቤተሰቦች አላማ ፍቅራቸውን ወደ ልጆቻቸው በማስተላለፍ “ዘላለማዊ” ማድረግ ነው።) እሷ ደግሞ እሱን ማግባት አትፈልግም። በተጨማሪም ትምህርቷን እስክትጨርስ እና እስኪጋቡ ድረስ አመታት ይወስዳል። አመታት ታግሳ በተክሊል እንዳታገባ ደግሞ ወሲባዊ ፍላጎቷ ያይላል። የምታምነውና የምታደርገው የተለያየ የሆነ ባህሪን ትይዛለች፤ ቤተ ክርስቲያን ትሄዳለች፤ መጥታ ግን እምነቷ የሚያወግዘውን ነገር ታደርጋለች። ለእራሷ ልታደርገው የፈቀደችውን ነገር ሌላው እንዲያደርገው አትፈልግም።

### 3.3.2 የተፈጥሮና ባህል ዕርቅ

ታሪኩ በአሮጌ ቡና ቤት ውስጥ ይጀምርና፣ ግንኙነቶች የሚያድጉት በሲኒማ ቤትና የመኖሪያ ቤት፣ የሚያልቀው በመኝታ ቤት ውስጥ ነው። ከጋራ ወደ ግል እየጠበበ ይመጣል። ወደ የጥንቅሽ መኝታ ቤት። ብዙ የለውጥ መሰረት የሆኑ ትዕይንቶች ይከናወኑበታል። በዚህ ክፍል ነው ዐቢይ ገላዋን እንዲመኝና እንዲቋምጥ ተድርጎ ሳይቀምስ የሚባረረው። በዚሁ ክፍል ነው በመስኮት እየገባ ደሳለኝና ጥንቅሽ የድብቅ ፍቅራቸውን ሲቀጩና ከባህሉ ሲያፈነግጡ የነበረው። ይህ ክፍል ነው ባህል ንጉስም አሽከርም የሚሆንበት። በዚሁ ክፍል ነው ጥንቅሽና ደሳለኝ የሚፈልጉትን እያደረጉ የእናትየውን ሳቅ የሚሰሙት።

እነ ዐቢይ በቤተሰቦቻቸው ይሉይኝታ የማይፈልጉትን ሕይወት ሲኖሩ ያለ ይሉኝታ በራሷ አለም የምትኖር ነበረች። ከዐቢይ ጋራ ሲጋቡ ግን ከሁለቱም ጽንፍ የወጣ፣ ሁለቱንም ስሜቶች የሚያማክል ኑሮን ያበጃሉ። ዐቢይ ጭምትና የቤተሰቦቹን ፍላጎት የሚኖር ነበር። ይህ ማለት ባህሉ ጭምት ያደረገው ጽንፍ ነው። ወለላ በተቃራኒ ጽንፍ ለእሴቶቹ ደንታ የሌላት ደመነፍሳዊ ፍላጎቷን ተከትላ የምትኖር፣ የሁለቱ መታረቅም ማዕከላዊነትን ይፈጥራል። ጥንቅሽ ዐቢይ ሰዓቱን እንዲሰጣት ብትጠይቀውም አልሰጣትም። በእሷ ባህሪ ዐቢይን መዝጋት ነበረባት ግን አላደረገችውም። እንደጥንቅሽ እንደፈለኩ ላድርግህ አትለውም፤ አትቀጣውምም። ተፈጥሯዊ ጥያቄዎችን በራስ ፍላጎት ማድረግ ግን ከእሴቶች አለመውጣት ነው። ምክንያቱም አሁንም ቢሆን ወሲብ ከትዳር በኋላ የሚመጣ ስለሆነ ድንጋጌውን አክብረዋል። የግድ ቤተሰብ በፈቀደው መንዝ የለብንም ሊሆን ይችላል። ከዚህ በኋላ እኩልነት ይፈጠራል። ደሳለኝ ጥንቅሽን ካገባ ማንም በማንም አያሳብብም፤ ማንም ማንም ላይ አይዘባበትም፤ ማንም ማንንም ጥፋተኛ አያደርግም። አቢይ ከጠፋበት ሲመለስ ለግጭቱ የሰጠው መፍትሄ ትዳር መሆኑ ለዚህ ማስረጃ ነው።

የሁሉም መጨረሻ በነጻት የራሳቸውን ሕይወት ለመኖር መወሰን ነው፡፡ አስገዳጅና ተገዳጅ የለም፡፡ በእኩል ይስተናገዳሉ፤ ነጻነትም እኩልነትም አለ፡፡ ጥንቅሽ ባህልን በድብቅ መስበርን የደፈረች ናት፤ በግልጽ ግን አትሞክረውም፡፡ ጥንቅሽ ለባህሉ ሌላ፣ ለተፈጥሮዋ ሌላ ናት፡፡ ሁለቱንም ታስኬዳቸዋለች፤ ግን እርሷ እንደወለላ አይደለችም፤ መቀጣትን ትፈራለች፡፡ ባህሉን ብትጥስ የሚደርስባትን ታውቃለች፤ በመስኮት ከምታስገባው ደሳለኝ ጋር ግን ተፈጥሮዋ የፈለገውን፣ የፈቀደችውን ታደርጋለች፡፡ ይህን ነጻነቷን ወደ አደባባይ የምታመጣው በደሳለኝ አማካኝነት ነው፡፡ በደሳለኝ አንድም ከማትፈልገው ከዐቢይ ትላቀቃለች፤ አንድም የምትፈልገውን እርሱን ታገባለች፡፡

ወለላ የጠየቀችውን ያላደረገን ዳግም አታናግረውም ተብሎ ሃያልነቷ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን የምትጠይቀው ገንዘብ ሊያሟላው የሚችልን ነገር ነው፡፡ ገንዘቡን ያወጣ ደግሞ እሷን በፈለገ ጊዜ የማግኘት መብት አለው፡፡ እሷ በነጻነትና በፈቃዷ የምትኖር ቢመስላትም በተቃራኒው ገንዘብ እንደፈለገ የሚገዛት ቁስ በመሆን ሰብኣዊ ፍጡርነቷን ታጣለች፡፡ ይህም ነጻነትን መከተል በራሱ ሌላ ባርነት ውስጥ እንደሚከት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ዐቢይ ከዚህ ሕይወት የሚያወጣት በጋብቻ ነው፡፡ ጋብቻ ደግሞ የጋራ ሕይወት መመስረቻም፣ ትውልድ ማስቀጠያም ነው፡፡ ከሁለቱ የሚመጣው ትውልድ ምን እንደሚመስል (የጥንቅሽንና የአቢይንም ጨምሮ) የሚጠቁም ንግርም ነው፡፡

ወለላ ምንም እንኳ ነጻነቷን ተጎናጽፋ የምትኖር ብትሆንም ሴተኛ አዳሪ ነበረች፡፡ ይህን ሕይወት ብትጀምረውም እንኳ ተጠቃሚ ቢኖር ኖሮ ምንም ማድረግ አትችልም ነበር፡፡ አንደኛ እኩይ ተብለው የሚወገዙ ነገሮች በማኅበረሰቡ ውስጥ ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ ድንጋጌዎቻቸው ግን ይህንን ነገር ማጥፋት አልቻሉም፡፡ እንዳያውም ተጠቃሚ በመሆናቸው እኩይ ድርጊት ፈጻሚው እየጨመረ ሲሄድ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ባይኖር ወይም ሴተኛ አዳሪ ቤት ሄዶ የሚያድር ባይኖር ይህ እኩይ የሚባለው ምግባር መጥፋት ይችል ነበር፡፡ እዚህ ጋ የማነሳው ዋና ነገር እሴቶቹ ጽኑና ተተግባሪ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ሌሎች ሲያደርጉ ያየውን ነው ተተኪው ሊያደርግ የሚችለው፡፡ ስለዚህ በድብቅ የተለማመደውን የእሴትን ማፍረስ በአደባባይ ያወጣዋል፡፡ ለተፈጥሯዊ ስሜቱ በመገዛት ደመነፍሳዊነት የሚገዛበት እሴት ያበጃል፡፡ ኅሊናው በጸጸት ሊመልሰው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ቀድሞውኑ ግብረገባዊ ጽናት የሌለውና ቀስ በቀስ ተሸርሽሮ ያለቀ ሰብዕና ያለው ትውልድ እንዲፈጠር ያደረገው ማኅበረሰቡ ነው፡፡

የማኅበረሰቡን እኩልነት የሚያስጠብቀው ግብረገብ ነበር፤ ይህን ግብረገብ ደግሞ አምጸው የወጡት እነ ወለላ በገንዘብ እየተገዙ እና “ባሪያ” እየሆኑ ነው፡፡ እነሱን አርአያ ያደረጉት ዐቢይን የመሰሉት ደግሞ ተገዝተውለት የኖረውን እሴት ገፍተው ተከትለዋቸዋል፡፡

የታሪኩ መጨረሻ ሳቅ ነው፡፡ ሳቁ የሚጀምረው ከጥንቅሽ እናት ነው፤ ምክንያቱ አይታወቅም፡፡ ግን ጥንቅሽ መኝታ ቤት ያለው ደሳለኝ ለምን አብረን አንስቅም ይላል፡፡ “…አፌን አፏ ላይ መድፋት ስጀምር፣ ከሳሎን የሚፈልቀው የእናቷ ድቡልቡል ሳቅ እየነጠረ መጥቶ እየነጠረ ጠፋ፡፡ ለምን ሁላችንም አንስቅም? ! ሃ!ሃ!ሃ!ሃ!......ሃ!ሃ!ሃ!ሃ!” (39) በመጀመሪያ ሳቁ የጥንቅሽ እናት ነው፤ ምናልባት ውጥናቸው ስላልተሳካ የብሽቀት ሳቅ ሊሆን ይችላል፡፡ “እየነጠረ መጥቶ ጠፋ” ብሏልና እዚሁ ጋ እናትየውን የሚያስደስት ነገር ልጆቹን እንደማያስደስታቸው የሚገልጽ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም እናትየው ያሉት ሳሎን ሲሆን ልጆቹ ጓዳ ናቸው፡፡ ሳቁም ከሳሎን ተነስቶ መኝታ ክፍል እስኪደርስ ድረስ እየቀዘቀዘ መጥቶ ይጠፋል፡፡ ሲቀጥል ሳቁ ድቡልቡል ነው፤ ብንሰነጣጥቀው ለእናትየው የብሽቀት ለልጆቹ የደስታ ይሆናል፡፡ የሚፈልጉትን አግኝተዋልና፡፡ በዚያ ላይ ሳቁ የሚፈልቅ ነው፡፡ በዚያ ላይ ደሳለኝም ሁላችንም እንሳቅ ይለናል፡፡

ሌላኛው ዕርቅ መፍጠሪያ መንገድ ነባሩን ባህል ተቀብሎ መኖር ነው፡፡ ዐቢይ ከሱቅ ወጥቶ ወደ ቡና ቤቱ ሄዷል፤ ወደ መድረክ ወጥቷል፡፡ ጥንቅሽ ግን እዚያው መኝታ ቤቷ ውስጥ ነች፡፡ (በመቀጠል የሚቀርበው ሃቲት ከስልጣኔ ጋር ተያይዞ መጠቀሱምንም ልብ ይሏል፡፡)

> *“በህብረተሰቡ ታላቅ የባርነት ጅረት ውስጥ የሚቀላቀሉ ገባሮች ስንት እሷን የመሰሉ ይኖራሉ! ክረምት ክረምት የምንፈልገውን እናውቃለን ብለው አምፀው፣ ድንጋይ ወርውረው፣ እግር አንስተው ደረት ገልብጠው……ፈረሰኛ ኾነው ዘለው……ሌላ መስመር እናበጃለን ብለው ደንፍተው፣ ግን ኩልል እያሉ ድምጻቸውን አጥፍተው ያለማፈር ወደ ዋናው የአድርባዮች ወንዝ የሚገቡሩ? የጥንቅሽ ውስጥዋ ድንፋታ ነው፡፡” (38)*

ይህን ገለጻ ተከትለን የምናገኘው ትርጉም ከማኅበረሰባቸው ባህል አፈንግጠው ወጥተው የራሳቸውን መንገድ ተከትለው ቢጓዙም መጨረሻው ግን ያው የነባሩ ባህል እስረኛ ሆነው እንደሚመለሱ ነው፤ ምክንያቱም ጸጸቱና ቅጣቱ ከአፈንጋጭነታቸው ይመልሳቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚኖረው “ሰው ምን ይለኛል?” ብሎ ፊት ለፊት ባህላዊ መሆንን በድብቅ ግን ውስጣዊ ፍላጎትን ማርካትን የሚጠቁም ነው፡፡ በድብቅ የጀመረችው ግንኙነት ከሰጣት ደስታ ይልቅ

ሰላሟን ስለነሳት ነው ይፋ እንዲወጣ የምታደርገው፡፡ በደሳለኝ በኩል እንዲሰማ ማድረጓ ደግሞ ያው የተለመደውን ባህል መከተሏንና ለሱ መገዛቷን ያመለክታል፡፡ የሳቁ ድቡልቡል መሆንና የመቼት ገለጻውም አስረጂ ነው፡፡ ጥንቅሽ መጨረሻ ላይ ዞራ እናቷ ቤት፣ ራሷ መኝታ ቤት፣ እኔ እንዳዘዝኩት ሊኖር ይገባል ስትል በነበረው ወንድ እቅፍ ውስጥ ትገባለች፡፡

## 3.4 “የሐር ነዶ”

### 3.4.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሶፊያን፣ የሶፊያ ጓደኛን እና የጓደኛዋን አባት ተራክቦ እናገኛለን፡፡ ሶፊያ በጣም በይሉኝታ፣ በየድርጊቷና ንግግሯ ሀሉ “ሰው ምን ይለኛል?” የምትል ጭምት መሳይ ጸጉረ ቆንጆ ሴት ናት፡፡ ጓደኛዋ ታደፋፍራታለች፣ እንደፈለገች እንድትሆን ትመክራታለች፡፡ ሶፊያ ምንም እንኳን በግላጭ የፈለገችውን ነገር ከመግለጽና ከማድረግ ብትቆጠብም የምታስበው፣ የምታደርገውና የምትሆነው ግን ሰው ምን ይለኛል? ብላ የምትፈራውን ተቃራኒ ነገር ነው፡፡

ሶፊያ ከጓደኛዋ ጋር ሁለት አይነት ባህርያት አሏት፡፡ አንደኛው ሌላ ሰው ጋ ሆና የማታደርገውን፣ ለሌላ ሰው የማትነግረውን እሷ ፊት ታደርጋለች፣ ትነግራታለችም፡፡ በዚህ በኩል ከሌላው የሸሸገችውን ሳታፍራት በግላጭ ታደርጋለች፤ ለምሳሌ፡- ለአለቃዋ “ስሎው ዳንስ” ነው የምወደው ትለዋለች፡፡ እሷ ግን ከዚያ ተቃራኒ የሆነውን ዳንስ በጓደኛዋ ደንሺልኝ ጥያቄ መሰረት ትደንሳለች፡፡ የጓደኛዋ አባትም እንዳያያት እየተሽማቀቀች (የተሽማቀቀች እያስመሰለች) በድብቅ ትደንስላታለች፡፡ በግልጽም አለቃዋ ያደረገውን ትነግራታለች፣ ጸጉሯን እርሷ ፊት ታበጥራለች፣ አበጥሪልኝም ትላታለች፡፡

ሁለተኛው ከጓደኛዋ አባት ጋር ወዳጆች ናቸው፡፡ ይህን ነገር ትደብቃታለች፡፡ ግን አባትና ልጅ ተመሳጥረው ነው ወዳጆች የሆኑት፡፡ በሁለቱ መሃል ያለች የሶፊያ ጓደኛ ለአባቷ ሶፊያ የድብቅ ፍቅረኛው እንድትሆን ትረዳዋለች፤ ግን እንደማታውቅ ትሆናለች፡፡ ሶፊያም ጓደኛዋ እንዳታውቅ ለማድረግ ትጥራለች፡፡ አባትየው ከልጁ ጋር እንደተመሳጠረ ሶፊያ እንዳታውቅ፡፡ በማድረግ ከሶፊያ ጋር ሲሆን ልጁ ግንኙነታቸውን እንደማታውቅ፤ ከልጁ ጋር ሲሆን ደግሞ ያላወቀች እንድታስመስል ያደርጋል፡፡ በዚህ ውስጥ የሁሉም ትኩረት ሶፊያ ናት፡፡ ምንም እንኳ ሶፊያ ብልጥ አድርጋ እራሷን ብትቆጥርም በተቃራኒው ብልጥ ይሆኑባታል፡፡

“‹ፋስት ነኛ። አንተስ ከሰው ጋር ሲሆን አባት፣ ከእኔ ጋር ሲሆን ላቨር ምናምን ትሆን የለ? ሁላችንም አክተሮች ነን›” (57) ሰው ፊት ሲሆኑ አንቱ፣ ብቻቸውን ሲሆኑ አንተ ስትለው አለመሳሳቷን ሲነግራት የምትሰጠው ምላሽ ነው። ተራኪው “ፋስት ነኛ” ፋስት የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ለምን ተጠቀመ? በዚህ ተረካ ውስጥ የተጠቀማቸውን “ላቨር” እና “አክተሮች” የሚሉ ቃላትን አማርኛ ትርጓሜያቸውን ያስቀመጠ ሲሆን የዚህን ቃል ብያኔ ለምን አላስፈረም? ፋስት ፍጥነትን የሚገልጽ ቃል ነው። ፍጥነት ከሩጫ ጋር፣ ነገሮችን በቶሎ ከመጨረስ ጋር፣ ጉዳዮችን ከሚጠበቅ ወይም ከተለመደው ፍጥነት አስቀድሞ ከመጨረስ ጋር። ሶፊያም ይህንን ቃል የተጠቀመችው ነገሮችን በአውዳቸው ሳይሳሳቱና ሳያምታቱ በትክክለኛው መንገድ መጠቀም መቻሏን ለመግለጽ ነው። ምንም እንኳን ምልልሱ አንተና አንቱታን በሚመለከት ቀላል ነገር ቢቀርብም ከዚህ የተለየ ትርጉም አለው። በመጀመሪያ ግን “ፋስት” ትርጓሜ ያልተሰጠው የአዕምሮዋን ንቁነት፣ ሁነቶችን በጊዜያቸው መጠቀም መቻሏን እና የዕውቀት ደረጃዋን ለመግለጽ ስለተጠቀመችበት ነው።

ብልጥነት ወይም ብልህነት አስመስሎ የመገኘትን እሳቤ ሲያቀነቅን ይታያል። ሶፊያ ጓደኛዋን ጨምሮ ሌሎችንም ስለሸወደች፣ ጓደኛዋና አባትየው ሶፊያን ስላታለሏት ብልህ የሆኑ ይመስላቸዋል። ሶስቱም የበላይነታቸውንና አዋቂነታቸውን ለማሳየት (ለመሆን) ይጥራሉ። በዚህ ፍላጎታቸውም ከግብረገባዊነት የራቀ ቡድንን ፈጥረዋል። ሃሳብ፣ ምግባርና አስተምህሮ ሊጣጣሙ አልቻሉም።

አንቱና አንተ የመደብ ጉዳይ ነው። ይህ መደብ ግን አስከትሎት የሚመጣው እሴት አለ። እድሜው የገፋ ወይም አንዳች ጠቃሚ ነገር ለማኅበረሰቡ ያበረከተ አንቱ ይባላል። የፖለቲካ ሰዎችና መሪዎች እንዳሉ ሆነው። ሶፊያ አንቱ እያለች የምትጠራው ሌሎች ሰዎች ፊት ነው። አንቱ ያለችውም በእድሜ በመግፋቱ ነው። ይህም እርሷ በምትሰጠው ምላሽ ውስጥ ተጠቁሟል። “አንተስ ከሰው ጋር ሲሆን አባት፣ ከእኔ ጋር ሲሆን ላቨር ምናምን ትሆን የለ?” (57) ይህ ገለጻ እሱ በእርሷ ማስመሰል መቻል ሲደነቅ፣ እራሱም የሷው ተመሳሳይ እንደሆነና ሁሉም አስመሳዮች እንደሆኑ ይገልጻል። ስለዚህ ለአባትነቱ ሰዎች ፊት አንቱ ትለዋለች። አንድም ውሸታምና አስመሳይ በመሆኑ፤ አንድም በሁለቱ መካከል ወሲባዊ ግንኙነት ስላለ አንተ ትለዋለች።

የሚኖሩበት ማኅበረሰብ በእድሜ የገፋ ሰው እንዲከበር ያስገድዳል። አክብሮቱ በሁሉም ቦታ መፈጸም አለበት። ይህ ሰው ግን ክብሩ በሰዎች ፊት የሚታይ እንጂ በውስጣዊ ማንነቱ የተገነባ

ሰብኣዊ ክብር አይደለም፡፡ ሶፊያ አንተ ብላ ስትጠራው ማቅለል ነው፡፡ የካበውን የሰው ፊት ክብር ትንደዋለች፡፡ አባት ሆኖ እንደ አባት መሆን ስላቃተው፡፡ ባህሉን በልጆቹ ላይ መቅረጽ ስለተሳነው ይህ ክብር ይነፈገዋል፡፡

እየተመላለሰች ስለምታስታምማቸው አክስቷ በምሬት ሰው እንኳ እንዳይሰማኝ ሳትል ወጣትነቷን እንዳትጫወትበት፣ እንደፈለገች እንዳትሆንበት እያገዷት እንደሆነ ትገልጻለች፡፡ ምሬቷ የሚጀምረው በጸጉሯ ነው፡፡ በልጅነቷ የእርሷን ጸጉር ይቆርጣሉ፤ የእርሳቸውን የሸበተ ጸጉር ግን ሹርባ ይሰራሉ፡፡ በዚህም የእርሷን ውበት ገድለው የራሳቸውን ያረጀ ውበት እየተንከባከቡ እንደሆነ ይሰማታል፡፡

አክስት ጸጉሯ የወንድን አይን እንደሚስብና ከእሴታቸው ያፈነገጠ ተግባር እንዲፈጽሙ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ያውቃሉ፡፡ ይህን ፍንገጣ ለመቋቋም የተጠቀሙት መንገድ ጸጉር ቆረጣ ነው፡፡ ተፈጥሮን ማመቅ ላይ ትኩረት እንዳደረጉ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አንድም ከማለሳለስ ይልቅ ማመቁ ላይ ስላተኮሩ፣ አንድም ሶፊያ እሳቸው የተረዱበትን መንገድ እንድትረዳ ማድረግ ስላልቻሉ የሚያተርፉት ጥላቻና ፍንገጣን ነው፡፡

በታሪኩ ውስጥ ተፈጥሮን ለማመቅ መጣር አለ፤ ውበትን መደበቅ አለ፤ ይሉኝታ አለ፤ ሶፊያ ተተኪ ትውልድ ናት፡፡ አክስቷ ቤተሰቦቿ እና “ሰው ምን ይለኛል?” የምትላቸው በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች፣ ማለትም ማኅበረሰቧ በፈጠረላት ጎዳና የምትጓዝ ነች፡፡ የጓደኛዋ አባት ደመነፍሳዊ ስሜቱን በእሴቱ መቆጣጠር አልቻለም፡፡ አክስትየውና ቤተሰቦቿ እኩይ ድርጊቶችን ላለመፈጸም ወይም ተፈጥሯዊ ስሜቷን በድንጋጌያቸው ለመምራት የሚያስችላትን ግብረገባዊ ጽናት ሊቀርጹባት አልቻሉም፡፡ እንዲሁም በድብቅ ተፈጥሯዊ ስሜቷን የምታረካበትን እንጂ ባደረገችው ነገር ለመጸጸት የሚያበቃትን ኅሊናዊ ባህርይ አላደረጁላትም፡፡

ይህም ሁለት አይነት ማንነት እንዲኖራት አድርጓል፡፡ በማኅበረሰቧ እሴት መሰረት አንደኛው ፍጹም ግብረገባዊ፣ ሌላኛው ኢ-ግብረገባዊ ነው፡፡ በራሷ መወሰን፣ ውጤትን በመፍራትም ሃላፊነትን መውሰድ ሲያቅታት ይታያል፡፡ በነዚህ ሁለት ጽንፎች ለመጓዝ የምታደርገው እንግልትም የተፈጥሮና የባህል ግጭት ተቃኝቶበታል፡፡ ወዲህ ተፈጥሯዊ ስሜቷን ብቻ ለማስኬድ ብትወስን ከአከባቢዋ የሚደርስባትን ጫና፣ ወዲህ ግብረገባዊ እንዳትሆን እሚደርስባት ግፊትና ትንኮሳ አጣብቂኝ ውስጥ ይከቷታል፡፡ በምታደርገው ሁሉ ስጉና ተጠራጣሪ ትሆናለች፡፡

በሌላ በኩል እሴቶቹን ያረቀቀው እራሱ እንደማይኖርበት ታውቃለች፡፡ "ውሽማዋ" በሰዎች ፊት እንደ አባት እንደሚሆን ሲገለጽ ግብረገቡን ሊሰብካት መጣሩን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው በሌሎች ፊትና በቃል ብቻ ነው፡፡ ውስጡ ያለው ሌላ ነው፡፡ እውነተኛው ስሜት ውስጡ ያለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወሲብ ነው፡፡ በተግባሩ መቃረንም ሳቢያ ውጥረት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ሰው ፊት አባት፣ ልጅ ፊት ውሽማ፣ ሶፊያ ፊት ፍቅረኛ፣ በጋራ ሲመጡበት ደግሞ የጓደኛ አባት ሆኖ መቅረብ አለበት፡፡ እነዚህን ሁሉ ማንነቶች ስልቱ ሳይፈርስ ይዞ መጓዝ ሊቻል ይችላል፤ ግን እስከመቼ ነው? ከዚህ የከፋው ደሞ እርስ በርስ የሚጋጭ ማንነትን እንደየ አውዱ እየተለዋወጡ መኖሩ ነው፡፡

የሶፊያ ጓደኛ ከአባቷ ጋር በሚያደርጉት ውይይት ውስጥ እንደሚጠቀሰው ሶፊያ ላይ ወሬ እንዲወራባት በማድረግ እንድታገባው ማድረግ እንደምትችል ይገለጻል፡፡ ሰውዬው በባህል አስሮ ሶፊያን የእርካታ ማግኛው ያደርጋታል፤ ምንም እንኳን በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ወዳጅነት ቢኖራቸውም ፊት ለፊት ከሱ ጋር እንደፍቅረኛ ሆና ለመታየት መስጋቷ ልታገባው አለመፈለጓን ይጠቁማል፡፡ እንደዚሁም ሶፊያ ፍላጎት እንዳላት ብታሳይም መጀመሪያውኑ ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖራት ማድረግ የቻለው "ምን ይሉኛልን"ና የታላቅን ፍልጎት መፈጸም ከፍተኛ ቦታ እንዲይዙ አድርጎ በመቅረጽ ነው፡፡ እነዚህም በልጅቷ ውሳኔ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ስለሚኖራቸው ምርጫዎቿ ወደ ነሱ ያመዝናሉ፡፡

እንዲሁም የሶፊያ ጓደኛ የተሰማትን ትናገራለች እንጂ አትሸፋፍንም፤ አትደባብቅም፡፡ ስሜታቸውን እንዲከተሉ የምትገፋፋቸውም እርሷ ናት፡፡ ከባህሉ እንዲያፈነግጡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ትረዳቸዋለች፡፡ በተጨማሪም እኩይም፣ ሰናይም ባህሪያት አሉዋት፤ እና ይህንን ሳትደብቅ ታወጣዋለች፡፡ ልውጣ ልውጣ የሚለውን ደመነፍስና እንዳይወጣ ያገደውን ግብረገብንም አጣምራ የያዘች ናት፡፡ ዝብርቅርቁ የሚያሳየን ባህሉ ተፈጥሮን ማለሳለስ እንዳቃተውና ለደመነፍሳዊ ስሜት ተገዢ እንደሆነ ነው፡፡

### 3.4.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

ሶፊያን አለቃዋ ፊት፣ ከጓደኛዋ ጋራ፣ ከፍቅረኛዋ ጋራ፣ ቤተሰቦቿ ጋ፣ ሌሎች ሰዎች ፊት የተለያየ እርስ በእርስ የሚቃረንና የሚጣረስ ሰብዕና ነው ያላት፡፡ ይህን ጠብቃ ማስኬድ መቻሏ ነው ራሷን እንደ ብልህ እንድትቆጥር ያደረጋት፡፡ ግን ሁሌም በስጋትና በፍርሃት ውስጥ ነች፡፡ አክስቷ እንዲሞቱ ትመኛለች፤ ጓደኛዋ ፊት የምር ሲሆንና ሲሞቱ ግን እርሷ እንድትሞት ትመኛለች፤ በሞታቸው ውስጧ ደስተኛ ነው፡፡ ላዩዋን ግን ጥቁር ለብሳ ጸጉሯን ተቆርጣ በሃዘን

የደቀቀ ታስመስላለች። ይህ በማስመሰል የተሞላ ሕይወትም ይደክማታል። መደበቁ፣ ማስመሰሉ ሁሉ። ገቢሩ ሌላ፣ እሴቱ ሌላ በሆነ ስርአት ውስጥ በማደን ተመሳሳይ ባህል ይኖራታል። ሰብሮ የሚወጣና የሚያወጣ በመጥፋቱ እንጂ ሁሉም አንዳች ነገርን ማስተካከል እንደሚፈልግ ይገባታል፤ ለዚያም ነው "ሁላችንም አክተሮች ነን።" የምትለው።

የደመነፍሷ ማየል ከመስልቸቷ ጋር ተዳምሮ ውስጧ የተፈጠረውን ግጭትና ቅጣት ፍራቻ የፈጠረባትን ዝብርቅርቅ መስመር ታሲይዛለች። በመድፈር "እወድሃለሁ በዕውነት……ግን የጓደኛዬ አባት ነህ። ድክም አለኝ መደበቅ። ስትፈልገኝ ጥራኝ። ሁልጊዜም አለሁ ለአንተ" (55) የሚለውን ሃቲት ስንመለከት ፍንገጣውም፣ ግጭቱም፣ ፍርሃቱም፣ ድካሙም፣ እርቁም፣ አዲሱ ጎዳናም አለበት። አዲሱ እሴት የፈቀዱትን መኖር ነው። እርሱም ሰዎች ከልጁ ጓደኛ ጋር ተወዳጅ እንዳይሉት ከልጁ ጋር እንድትጣላ ይመክራታል፤ ነጻ መውጣት ይፈልጋል። ማኅበረሰቡ በፈቀደለት ሳይሆን በጋራ በፈቀዱት መንገድ መጓዝን ይመርጣል።

ሶፊያን አባትና ልጅ እየተመሳጠሩ በወሲብ እንድትማረክ ሲያደርጉ የሚታየው ነገር የልጁን ባህሪ እሱ በሚፈልገው መልኩ መቅረጽ መቻሉን ነው። ሶፊያም እንደ ልጁ የምትቆጠር ናት። አባትም ልጅም በአንድ መስመር መጓዝ ይፈልጋሉ። አስተማሪና ተማሪነታቸው ቀርቶ በደመነፍሳዊ ስሜት እየታገዙ እርካታ የሚያገኙበትን መስመር ያበጃሉ። ይህ የሚያሳየውም ነባሩ ባህል ሲወርድ፣ ሲዋረድ እየላላ የመጣና የባህሉ የባለቤትነት ስሜት በውስጣቸው ያልዳበረ መሆኑን ነው። ስለዚህ ቀስ በቀስ ተሸርሽሮ ያልቅና ጭራሹን ተጥሶ እሴቶቹን ይገፉቸዋል። ይህም ግብረገባዊነት አሳሳቢነት ደረጃ ላይ መውደቁን ሲያሳይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግብረገብ አይሎ ደመነፍሳዊ ስሜትን ሲያለሳልስ ባህል መሪ፣ ተፈጥሮ ተመሪ ይሆናል፤ በታሪኩ ውስጥ ግን ይህ ስርዓት አቅጣጫውን በመቀየር ተፈጥሮ መሪ ባህል ተመሪ የሆኑበትን ስርዓት እንደመሰረቱ ወይም ለመመስረት እየጣሩ እንዳሉ የሚጠቁም ነው።

"ውሽማዋ" ጸጉሯ ረጅም እያለ ያፈቅራት ነበር፤ ተቆርጦም ውበቱ ስላለ ሁሌም ያፈቅራታል፤ አብሯትም ይሆናል። የአክስቷ መሞት ጸጉሯን እንድትቆረጠው አድርጓታል። ጸጉሯን አልተላጨችውም፤ ተቆረጠችው እንጂ። የፍቅረኛዋ የጸጉርን ማድነቅ በርዝመቱ አይደለም በውበቱ እንጂ፤ ለዚያም ይመስለኛል መቆረጡ ትርጉም ያልኖረው። ጸጉሯን ስትቆረጠው የጸጉሯ ቅርፅ ይቀየራል። ይህም በፊት የነበራትን ማንነት ትታ አዲስ መያዟን ያመላክታል። በአዲስ እይታ ነው የምትቀርበው። አክስቷ ሲሞቱ መላጨት ሁሉም ፈልገው "ቆረጡኝ" እንጂ ላጩኝ አትልም። በተጨማሪም ጸጉሬን ተላጭቼውም ትወደኛለህ ስትለው "እይው እስኪ

እንዴት ለሽ እንዳለ…" (57) ይላታል፤ ስለዚህ አልተላጨችውም። ይህም ለሰው ስትታይ እንደድሮዋ ብትመስልም የተቀየሩ ማንነቶች እንደሚኖሯት ያሳያል። በተምሳሌቱ የሚመራው ፍቺም እሷ በፊት የነበራትን ቅርጽ ቀይራለች፤ እሱም ተከትሏታል። ስለዚህ ከእሴታቸው ማፈንገጣቸውን ወይም መነጠላቸውን የሚያሳይ ነው።

ስለ ስልጣኔ የተነሳ ነገር አለ፤ አንድም እሷ የተማረች እንደሆነች ይጠቀሳል፤ ሁለትም የምትደንሳቸው ዳንሶችና የምታደምጣቸው ሙዚቃዎች ከውጪው አለም የተቀዱ ናቸው። እንደነሱ ለመደነስ ለመዝፈን መጣሯ (መደነስ መቻሏም ጭምር) የሚጠቁመው ነገር አለ።

## 3.5 "ሕማማትና በገና"

### 3.5.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

ለመጽሐፉ መጠሪያነት የተሰየመው ታሪክ ሕማማትና በገና ከሌሎቹ ታሪኮች ሰፋ ያለ ኖቬላ ነው። ብርሃኑና ቴንሳ ደማቅ ሌሎች ገጸባህሪያት ደግሞ ፍዝ የጉዳይ ማቀንቀኛ ሆነው ቀርበዋል። ብርሃኑ በጣም ጭምትና አክስቱ ያዘዙትን ሁሉ የሚያደርግ ዝምተኛ ሰው ነው። በመጀመሪያ ብቸኛ ነበር፤ ሰውን አይን ለአይን ማየት የማይችል። ብርሃኑ "አንድ ቃል ለመናገር አስር ጊዜ ሰማይ፣ አስር ጊዜ መሬት፣ አስር ጊዜ ግድግዳ፣ አስር ጊዜ የአድማጮቹን ፊት ያያል።" (117) ተብሎ የተገለጸለትን አይናፋር ነበር።

ብርሃኑ ሚስት ማግባት አይፈልግም፤ እራሱ አብስሎ ይበላል፤ የሚፈልገውንም ያደርጋል፤ በብቸኝነቱ ደስተኛ ነበር። ፍየሉ ሱሬውን እንደ በላበት እየተናገረ እያለ ታይታ የማትታወቀው አክስቱ ድንገት ትመጣለች። አክስትየው ሚስት ማግባት እንዳለበት ታምናለች። ብርሃኑ በፍየሉ ሲቀልድ እንዳላፈነዳው የሚለው መራቢያውን ነው። የወንድነት አንድ መለኪያው አግብቶ መውለድ መቻል ነው። ስለዚህ አክስትየው ሱሪዬን በላው ሲል ፍየሉ ወንድነቱን እያሳጣው ነው ብላ በማሰብ ሚስት እንዲያገባ ታመጣለታለች። (ምናልባትም የፍየሉ ቆለጥ ጎልቶ እንዲታይ መደረጉ፣ ብርሃኑ ሚስት ለማግባት አለመፍቀዱ፣ ጓደኝነት የሚፈጥረው ከቴንሳ ጋር መሆኑ የተመሳሳይ ጾታ ፍላጎት አለው ብሎ ለመደምደም ያስችል ይሆናል።) አክስትየው የኖረችው፣ ሲኖሩ ያየችውና ያመነችው የሕይወት ዘይቤ ትዳር ነው። ብርሃኑ ትዳርን ባይፈልግም እሷን ላለማስቀየም ያለችውን ያደርጋል። አክስት ሰራተኛ ትሁንህ ብለው ሴት ያመጡለታል። ሴቲቱ ግን ሚስት እንደምትሆን ይገባታል። ቤቱን፣ ሰፈሩን፣ ጓደኞቹን፣ ብርሃኑንም ቀስ በቀስ መተዋወቅና በውሳኔዎቹ እጇን ማስገባት ትጀምራለች። ሚስት መሆን

የጀመረች ሰሞንም ብርሃኑ ላዩ እያማረበት ውስጡ ግን ባዶ እየሆነ ይሄዳል፡፡ "ዐይኖቹ ባዶ ይመስላሉ፡፡ …ቅጡ እንደጠፋው ሰው በእጆቹ ልብስ ያለበሰውን መላጣ የጠረጴዛ ጠለል በጸጥታ ሲዳብስ ቆይቶ…" (140) ሚስቱ ቤቱ የገባች ሰሞን ባዶ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ ሌሎች አባላቱን ሙሉ ያደርጋል (ቢያደርግም ባያደርግም) ብለው የሚያምኑትን ትዳር የያዘ ሰሞን ባዶ ሆነ በፍርሃትና በስጋት መኖር ጀመረ፡፡

አክስትየው እሳቸው የሚፈልጉትን ነው  በብርሃኑ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩት፡፡ ባህል ብዙ ሰው በስምምነት የፈጠረውና ለሚፈጥረውም ትውልድ እያስተማረ ዘላቂ የሚያደርገው የኑሮ መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ ብዙዎችን ደስተኛ አድርጎ ቢያኖርም የማይደሰትበትና የማይፈልገው ግን ይኖራል፡፡ በርግጥ የተፈጥሮ ሃብትን አመጣጥኖ ለኀብረተሰቡ ለማብቃት፣ ደስታን የሚፈጥሩ የሕይወት መንገዶችን ለማሳየት፣ ግብረገቡን ቀርጾም ሰላማዊ ሕይወትን ለመፍጠር ይህ ባህል የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ከልጅነት እስከ እውቀት የተማረውን፣ ያወቀውን እና የለመደውን ስርዓት ተገቢና ከሱ ሌላ ያለው ምቹ ያልሆነ መስሎ ይሰማዋል፡፡ እናም የራሱን ባህል ለማስቀጠል አዲስ ስርዓት ልፍጠር ያለውን ለመቅጣት ጥብቅና ይቆማል፡፡

የብርሃኑና የአክስትየውም ተራክቦ የሚያሳው ይህንኑ ነው፡፡ "‹ከከአክስቴ ጋር ንግግር አይሆንም፤ ልልታስገድሉኝ ነው፡፡›" (144) ብርሃኑ አክስቱ ምን ያህል ጫና እንደምታደርግበትና እንደሚፈራት ያሳያል፡፡ አክስቱ ብዙ ውለታ ውላለታለች፤ እናም በምትኩ የሆነ ነገር ትፈልጋለች፡፡ እሱ ደሞ እሷ የምትለውን እንዲያደርግ ነው፡፡ ብርሃኑ በውለታ ታስሮ የሌሎችን (የበላዮቹን) ፍላጎት ይፈጽማል፡፡ ይህ ሌሎችን እያየ፣ ወይም በሌሎች እየተመራ የሚያደርገው ድርጊት ግን ሕይወቱን በፈለገው መንገድ እንዳይመራ ሲያደርገው፣ እንዲያውም መውደቂያው ሲሆን ይታያል፡፡

የብርሃኑ ሰራተኛ የተባለችው ሴት አረገዘች እነ ቴንሳ ቤት ብርሃኑ ተጠርቶ ሲወያዩ ብርሃኑ ያረገዘችው ከእሱ ይሁን ወይ ከሌላ አያውቅም "የት አአአውቃለሁ እኔ ያለችኝ ነው" (143) ይላል፡፡ የብርሃኑ ፍላጎትና ብቸኝነት ነገር እዚህ ጋ ያከትማል፡፡ ባልነቱ ይረጋገጥና በዘነበች ትቆጣጠረዋለች፡፡ "‹ነገሩ እኮ አልቋል፡፡ የየየት እሰዳታለሁ?›" (144) ይላልና፡፡ ቁጥጥሯ የት ወጣህ ፣ የትገባህ፣ ምን አደረክ የሚል አደለም፡፡ እራሷን ከአካባቢ ጋር ማለማመድና ተሰሚነትን ማግኘት ነው፡፡ አካባቢ ከፍተኛ ጫና እንዳለው የተረዳችው ሚስት ማርገዟን ምክንያት አድርጋ ከጎረቤቶቿ ወዳጅነት ትፈጥራለች፡፡ ከዚያ በኋላ ብርሃኑ ሳይፈልግ ለምን? ብለው ይሟገቱለት የነበሩት፤ እንዳይጎዳ ይጨነቁለት የነበሩት ሁሉ ወደ እሷ ይወግናሉ፡፡

የእሷን አቋም ደጋፊና የብርሃኑ ተቃዋሚ ይሆናሉ። ስለዚህ ዙሪያው በሌሎች አጥር ይቀጠራል። ይህ ቅጥር ለብርሃኑ እስር ነው። መኖር የማይፈልገውን፣ መሆን የማይፈልገውን እያስደረጉት ነው። ነገሮችን ለመወሰን ያለውን ነጻነት ይነፍጉታል፤ እነሱ ሊኖር ይገባል ብለው ያመኑትን ኑሮ በመቀየስ ሃላፊነትን ይሰጡታል።

ለርሱ የሚቆም የለም፤ ስለዚህ እራሱን እንደጥፋተኛ ይቆጥራል፤ ሌሎቹ በትክክለኛው መስመር እየተጓዙ እርሱ ያፈነገጠ ይመስለዋል፤ ዝም ማለት ይጀምራል፤ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ የእሱን ማንነት የሚጋፉ ቢሆኑም እንኳ ትክክል ናቸው ብሎ ስለሚያስብ እራሱን ይጠላል፤ ሌሎች የሚሉትን ይኖራል፤ የሚፈልጉትን ያደርጋል፤ ከራሱ ጋር ይጣላል። እራሱን ይደብቃል። የብርሃኑ መጥፋት የሚጠቀስባቸው ቦታዎች፡- አክስተየው የመጣች ሰሞን፣ ዘነበች ቤቱ የገባች ሰሞን፣ ያረገዘች ሰሞን ሲሆን የሚጠፋውም ቤቱ ነው፤ ከስራ አምሽቶ እየወጣ፣ ወይም ከቤቱ ሳይወጣ ከሰው በመሸሽግ መሆኑን ልብ ይሏል።

ብርሃኑ የማኅበረሰቡ አንድ አካል ነው። ወጣትም ስለሆነ ተተኪ ትውልድ ነው። የብርሃኑ አላገባም ማለት ለማኅበረሰቡ የዘላለማዊነት ህልውና ጉዳይ ነው። እሱ ላለመውለድ ካመጸ ዘራቸው ሊቀጥል ስለማይችል ይህን ሃሳብ ለማስቀረት ነው እንዲያገባ የሚያስገድዱት።

ባለማግባቱ ብቻ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እሴቶች ይጣሳሉ። ካላገባ ለአመት በዓል በየ ሰው ቤት እየዞረ ይውላል (ይበላል) እንጂ እሱ መጋበዝ አይችልም፤ ካላገባና የአባትነትና የባልነት ማዕረግን አግኝቶ ማስተዳደርና ሃላፊነትን መወጣት አይችልም፤ ካላገባ የተማረውን ባህል ማስተማርና ማስተላለፍ አይችልም። እነዚህን ሁሉ እሴቶች ሊጥስ የሚጥረውን ብርሃኑን በተለያዩ ቅጣቶች ወደነሱ መንገድ እንዲገባ ጥረት ያደርጋሉ።

ብርሃኑ ደግሞ ባህል የአኗኗር ስርዓት ነው። ይህ አኗኗር ስርዓት ምቹ የሆነ ሕይወትን ለሰው ልጅ የሚሰጥ ነው፤ የአድርግ አታድርግ ድንጋጌዎችም ሰላማዊ ሕይወትን ከማስፈን የዘለለ ትርጉም የላቸውም። ስለዚህ እሱ ብቸኝነት ሰላሙ የሚሰጠው ከሆነ፣ ምቹ የኑሮ መስመሩ ከሆነ የሚያገባበት ምንም ምክንያት የለም። ሁሉም የተመቸውን ኑሮ የመኖር ስርዓት መያዝ እንዳለበት ያምናል፤ ያንንም በተግባር ለማሳየት ይጥራል። ከጎሊናውና ከአካባቢው የሚደርስበት ጫና ግን እንዳሰበው ውሳኔውን ቀላል አላደረጉትም።

እነዚህን አስተሳሰቦች እንዲይዝ ያደረገው የሌላ ሕዝብ ባህል በመያዙ ነው። ብርሃኑ ከአካባቢው የሚነጥሉት ወይም ልዩ የሚያደርጉት ነገሮች አሉ። ጎረቤቶቹ የቤታቸው አሰራር፣ የእጽዋቱ

አይነቶች፣ ልብሶቻቸው ወዘተ. አገር በቀል እንደሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ይገለጻል፡፡ ብርሃኑ ደግሞ ከፈረንጆቹ በሚያገኛቸው ነገሮች የተዳቀለ የኑሮ ዘይቤ ሲኖረው ይታያል፡፡ ምንም እንኳን በሚኖርበት አካባቢ ማኅበራዊ ሕይወትን ቢመሰርትም፣ አንድም እንደሌሎቹ ከማኅበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው  አይደለም፡፡ አንድም እሱ ከእነሱ ላቅ ያለ ደረጃ ላይ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ ላቅ ያለ ደረጃ ሲባል፣ አንድም እሱ ከማኅበረሰቡ አንጻር  ለራሱ የሰጠው የበላይነት ነው፤ አንድም ማኅበረሰቡ ለሱ የሚሰጡት ቦታ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች የሚያስቃኙ ነገሮች፡-

አንደኛ የብርሃኑ ቤት አቀማመጡ ኮረብታ ላይ ነው፡፡ እሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሲመለከት ዝቅ ብሎ ነው የሚያያቸው፡፡ በተጨማሪም የሁሉንም (የመንደሩን) ቤቶች መመልከት ይችላል፡፡ የሰፈሩ ሰዎች ግን የእሱን ቤት የሚያዩት ወደ ላይ አሻቅበው ነው፡፡ "ያን ቀን ከቆምኩበት ቦታ ወደ ታች ሳይ፣ የሰፈሬ አቀማመጥ እንደ ፎቶ ቁልጭ ብሎ ይታያል፡፡" (121) ሁለተኛ የብርሃኑ ተክለ ሰውነት ሲገለጽ ረዥምና ከሰው መሃል ተለይቶ የሚታይ መሆኑ ተገልጿል፡፡ "…ቁመቱ ከመርዘሙ የተነሳ እንደ አላማ ሰንደቅ ከሩቅ የሚታይ ነው፡፡" (117) ሦስተኛ ብርሃኑ በገና መስራት ይችላል፤ ይህ ችሎታ በዙሪያው ካሉ ሰዎች ሁሉ የእሱ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚያስመሰግነው ስራ ነው፡፡ "‹ምኑ ያሳፍራል? ይኸ ዐይነት ሙያ አለው እንዴ? ኧረ እጅህ የተባረከ ነው›…የበገናው ሆድ የሚገርም ትልቅነት አለው፡፡" (158) የበገናው ሆድ ዘግየት ብዬ እንደማስረዳው ብርሃኑን የሚወክል ነው፡፡ አንድም ትልቅነቱን፣ አንድም ቻይነቱን፣ አንድም የዕውቀትና ችሎታውን ነገር ያሳያል፡፡ አራተኛ በብርሃኑ ግቢ ውስጥ ሃገር በቀል የሆኑና ያልሆኑ እጽዋት ሲገኙ የዚህን አይነት አትክልቶች የሚገኙት በፈረንጆች ግቢ ውስጥ ብቻ እንጂ በአካባቢው ሰው ግቢ ውስጥ የለም፡፡ "…ታች ሠፈር ካለው የጣሊያኖች የኮክ እርሻ ሌላ ፍራፍሬ የበቀለበት ግቢ የእርሱ ነው፡፡" (118)

እነዚህ ገለጻዎች ናቸው ብርሃኑ ከአካባቢው ሰዎች የላቀ ደረጃ ላይ ያለ ተደርጎ ተስሏል ያስባለኝ፡፡ ይህ አሳሳሉ በአንድ ጎን ማኅበረሰቡ እነሱን ባለመምሰሉ ትኩረታቸውን ሁሉ እሱ ላይ እንዲያደርጉና እንዲከታተሉት ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል እሱ ከማኅበረሰቡ የተሻለና እንደፈለገው የሚኖር አድርጎ እራሱን እንዲያስብ አድርጎታል፡፡ ወይም ብርሃኑ አፈንጋጭነቱን ስለሚያውቅ እራሱን ያገላል፡፡ የመኖሪያ ቤቱ ከሌሎች የተነጠለ መሆኑ፣ ብቸኛ መሆኑ፣ ሌሎች ወደ እርሱ ሲሄዱ እንጂ እሱ ወደ ሌሎች ሲሄድ አለመታየቱ ይህንን ይጠቁማል፡፡ ስለዚህ ብርሃኑ ከአካባቢው ሰዎች የተለየ አስተሳሰብ አለው፡፡

ሌላው ጉዳይ ጓደኞቹ ልጆች መሆናቸው ነው፡፡ ከዘነበች የሚመጣው ተቀዳሚ ሂስም ይኸው ነው፡፡ ከልጆች ጋር ሊወዳጅ የቻለው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛ ብርሃኑ ርቱዕ አንደበት ስለሌለው ብዙ ሰው አያዳምጠውም፤ ማለት የሚያወያየው፣ ሃሳብ የሚያካፍለው የለም፡፡ የአፉ ተብታባነት ወይም ጥሩ ተናጋሪ አለመሆኑ ግድ የማይሰጣቸው ልጆች ስለሆኑ እነሱን ጓደኛ በማድረጉ መሳቀቅና ለሚያወጣቸው ቃላት ማማጥ አይጠበቅበትም፤ ሁለተኛው ደግሞ ዕውቀቱን ሊያካፍላቸው፣ እሱ ወደ ደረሰበት የላቀ ደረጃ ለማድረስ የመረጣቸው ልጆች ናቸው፡፡ እነሱ የሚለውን ይሰሙታል፤ እሱም ሌሎች ሲጠይቁት ሲመልስ እንጂ በፍላጎቱ ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ ሲያወራ አይታይም፡፡

ብርሃኑ ከሌሎች በተለየ ከተፈጥሮ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ በተከላቸው እጽዋት፣ በስራው፣ በፍየሉ፣ በአከባቢው የሌሉ ዎፎች እሱ ግቢ በመገኘታቸው፣ ጸሃይን ቦታ እየለዋወጠ በመሞቁ ወዘተ. ተገልጿል፡፡ ይህ የሚያሳየውም ለተፈጥሯዊ ስሜቱ ፏሪ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም የሰው ልጅ በተፈጥሮ ተጠቃሚ ነው፡፡ ወይም የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት እንስሳትን እጽዋትንና ሌሎች ነገሮችንም ያጠፋል፤ ሰው ከጠፋ ግን ተፈጥሮ ያለአጥፊ ሊኖር ይችላል፤ የሚል ፍልስፍና አለው ማለትም ይቻላል፡፡ ይህ ለተፈጥሮ ጥብቅና የቆመ ፍልስፍናውም ከሰው ልጅና ከእሴቶቹ ጋር ግብግብ እንዲፈጥር ያደርገዋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አላገባም ሲል ተፈጥሮን አላስቀጥልም ነው፡፡ በሌላ አንጻር ደግሞ ተፈጥሮን ለማመቅ ሲጥርም ይታያል፡፡ ለተፈጥሮ የቆመላትን ያህልም ሊያጠፋት ይጥራል፤ የተዘበራረቀ ስሜትን ይዞ ቀርቧል፡፡ ይህ ስሜቱም የአእምሮ እክሎች እንዲገጥሙት ያደርጋል፡፡

ብርሃኑ የሚያምነውና የሚያደርገው የተምታታበት ሰው ነው፡፡ ሚስት ማግባት እንደማይፈልግ ይገልጻል፡፡ ዘነበች መጀመሪያ የመጣችው በሰራተኝነት ነው፡፡ ፍላጎት ከሌለው ለምን ግንኙነት ይፈጽማል? ለምንስ ያስረግዛታል? ደመነፍሱ አይሎ እንዳስረገዛት እንኳን በግልጽ አያምንም፡፡ ምክንያቱም ማስረገዙን ሲጠየቅ በጣም ወደ መካዱ አስጠግቶ ነው የሚመልሰው፡፡ ከእሱ ጋር እየኖረች አላስረገዝኳትም ቢል እምነት እንደማያገኝ ስላሰበ ነው "ያው" እያለ የሚመልሰው፡፡ ስለዚህ የራሱ እምነት እንኳ ተዛብቶበታል፡፡ የማኅበረሰቡንም እሴቶች ላለመጠበቅ፣ ለተፈጥሮም ጥብቅና ላለመቆም መወሰን የተቸገረ ባህሪ ነው ያለው፡፡

እንዲህ እንዲሆን ያደረገው ደግሞ ኅሊናው ነው፡፡ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ግብረገባዊነታቸው ያመዘነ በመሆኑ ያደገባቸውን እሴቶች ጥሶ ለመውጣት ማሰቡ እንዲጸጸት ሲያደርገው እንዲኖር

የሚፈልገው ሕይወት ደግሞ ለእሴቶቹ እንዳይገዛ ያደርጉታል፡፡ ይህም ከራሱም፣ ከማኅበረሰቡም እንዲጋጭ ያደርገዋል፡፡ በራስ መተማመኑንና የሚቆምለትን ማንነቱን ያጣል፡፡ ሁሉም በተናገረው (ምንም ይናገር ምን) ፈገግ ይላል፡፡ ይህ ድርጊቱም እንደ ጅል ከሚያስቆጥሩት ውስጥ ቀዳሚው ነው፡፡ ሌላ የሚያሳየው ነገር ደግሞ ከሰው ጋር ሲሆን አካሉ እንጂ ሃሳቡ አብሮ እንደሌለ ነው፡፡ ትኩረቱን ሰጥቶ የማያዳምጥ ሰው ፈገግ ይላል ያደመጠ ወይም የገባው ለመምሰል፡፡

ቴንሳ የሚያየው ሕልም አንድ የጉዳይ ማተኮሪያ ነው፡፡ ብርሃኑ የፍየሉ ቆለጥ ጠፍቶበት እሱን በመፈለግ ላይ ነበር፡፡ "‹አየህ ኮዳዬን ሰረቁ፡፡ በቃ አሁን የቤትናም ጦርነት ተጀመረ ማለት ነው፡፡›" አለና ፍየሉን እየጎተተ ወደ ሆነ ደን ገባ......." (135) ፍየሉ ያጣው መራቢያውን ነው፡፡ መራቢያውን አጣ ማለት ህልውናው ወይም ዘላለማዊነቱ ያበቃል ማለት ነው፡፡ ትውልዱን የሚያስቀጥል የዘር ሃረግ አይገኝም ማለት ነው፡፡ ብርሃኑ የፍየሉን ዘር ሃረግ ለማስቀጠል እየፈለገለት ነበር፡፡ ፍየሉ ከሞተ በኋላ ጭራሹን እንዳይዘነጋ በቆዳው በገና ይሰራበታል፡፡ ይህም ዘላለማዊነቱን እንዳያጣ የሚያደርገውን ጥረት ያሳያል፡፡ በዚሁ ምርመራ ከተቀጠለ ብርሃኑ የጠፋውን ነገር ማግኘት አለመቻሉ፣ የበገናውን መጥፋት የሚጠቁም ንግርም ይሆናል፡፡ በሌላ አቅጣጫ የብርሃኑ ዕውቀት አለ፡፡ ይህንን ዕውቀት የሚያወርሰው ሰው የለም፡፡

ብርሃኑ በቅጣት የታጀበ ሕይወትን መምራት ይጀምራል፡፡ ወዲህ ውስጣዊ እረፍትና አቋም የለውም፤ ወዲህ ኑሮው ሁሉ በሌሎች ፍላጎትና ውሳኔ እየተመራ የማይፈልገውን ሃላፊነት እንዲቀበል ግፊት አለበት፡፡ ሽቁጥቁጥና ፈሪ ሆኖም ይታያል፡፡ ሚስቱ ካረገዘች በኋላ አምሮኛልና ፍየሉ ይታረድ ስትል ጎረቤቶችም ያግዟታል፤ ሳይፈልግ ፍየሉ ይታረዳል፤ በቆዳውም በገና ይሰራል፡፡ ሚስቲቱ ያለ ፈቃዱ የሰራውን በገና ለፈረንጆች ትሰጣለች፡፡ የዚህን ጊዜ እቤት አልገባም ብሎ ወንዝ ዳር ተቀመጠ፡፡ ጎረቤቶች ቢመክሩት ቢቆጡትም "‹ምን አገባህ!› እንዴ ያውም ጣቱን እየነቀነቀ፣ እየተንተባተበ ነዋ፤ ‹እኔን ትተህ የምትጮህበት ፈልገህ ጩህ፡፡ በማታውቀው በማያገባህ ነገር አትለፍልፍብኝ› አለው፡፡" (162) ብርሃኑ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ የሚፈልገውን የተናገረበት ክስተት ነው፡፡ የሰፈሩ ሰውም እንደ ጅል ከመቁጠር እሱን ወደ መፍራት የሚቀየረው የዚህን ጊዜ ነው፡፡ በሰዎች ተመርቶ በይሉኝታም ተይዞ ወደ ቤቱ ሳይገባ ቀረ፡፡ "‹ምን ስህተት አለው ወንዝ ዳር መቆም›" (162) ብሎ እርሱው ተቆጥቶ መለሳቸው፡፡ ሲነጋ ቴንሳ ከኮረብታ ላይ ቁልቁል እያየ እጁን ለሰላምታ ሲያውለበልብለት ብርሃኑ ወደ ገደሉ ዘለለ፤ ገደሉ በክረምት ውሃ ሞልቶ ነበር፡፡ ብርሃኑ ሞተ፡፡

የብርሃኑ ሞት መንስኤ በገናው ነው። ሰው ለበገና ብሎ እንዴት ራሱን ያጠፋል? በገናውን የሰራው ብርሃኑ ነው። የተሰራበት ቆዳ ደሞ የሚወደውና ሰው የሚመስለው ፍየል ነው። ሁለት ጉዳዮችን ልበል። አንደኛው ብርሃኑ ከፍየሉ ጋር ለረጅም ጊዜ አብሮት ኖሯል፤ አብሮት የ ነበረው ዘነበች ከመምጣቷ በፊት ነው። በሌላ በኩል ለፍየሉ የሰው ሰብዕናን ያላብሰዋል። “አድርጎት የማያውቀውን ብርሐኑ መከራከር ጀመረ። ‹ሰው ነው የሚመስለኝ። ለለለምጄው እጄ እሱን ማረድ አይችልም› አለ።” (145) ፍየሉን እሱና ሚስቲቱ መብላት ሳይጀምሩ በፊት እንጀራ ቆርሶ ይሰጠው ነበር። እንደ ሰው ነበር የሚቆጥረው።

ፍየሉን የገዛው ብርሃኑ ነው። ፍየሉ የብርሃኑን ሱሪ እየበላ፣ የጎረቤቶቹን የጓሮ አትክልት እየበላ ያስቸግር ነበር። ብርሃኑ በፍየሉ ጥፋት ከመገረምና ከመሳቅ በስተቀር አንድም ቀን አይማረርበትም። ተራኪውና ብርሃኑ እንዲግባቡም መነሾ የሆነው ይህ ፍየል እንደሆነ ልብ ይሏል።

ፍየሉ ለብርሃኑ ብቻ ሳይሆን ለነቴንሳና ለሰፈሩ ልጆች መጫወቻ፣ በተቃራኒውም ለጎረቤቶቹ ውድመት አድራሽ ነበር። ፍየሉ ሰፈሩን ለምዶት ነበር። መልመድ ብቻ አይደለም ሲነጋ ከቤቱ የሚወጣው ሲመሽ ወደ ቤቱ የሚሄደው ያለማንም እረኝነት ነበር፤ ፍየሉ ከሰዎች አዛዥነትና ጠባቂነት ራሱን ነጻ አውጥቶ ነበር፤ ፍየሉ ፍየል ብቻ አይደለም፤ ፍየሉ የሌሎችን ጫና ከራሱ ላይ ገፎ ጥሎ በራሱ መንገድ የሚጠበቅበትን የሚያደርግ ነው፤ ምናልባትም ፍየሉ ለብርሃኑ አርአያው ነበር፤ ብርሃኑ በሌሎች መንገድ መጓዙን ጥሎ የራሱን እንዲኖር የሚያነሳሳውና የሚጽናናበት ነበር፤ የፍየሉ ነጻነትና ነገሮችን በራሱ ማድረጉ ግን ብርሃኑን በሌሎች ውሳኔ ከመመራት አላዳነውም። እንዲያም የብርሃኑ በሌሎች ጫና ውስጥ መውደቁ ለፍየሉ መታረድ ሰበብ ሆኗል። ይህን ፍየል ቢያርደውም እንኳ ጨርሶ እንዲጠፋ ማድረግ ያልፈለገው ብርሃኑ በቆዳው በገና ሰራ። በገናው ትልቅ ነው። ጥሩ ድምጽም ይፈጥርለት ነበር። (ጥሩነቱ ግን እንደየሰዉ ይለያያል።)

ሁለተኛው ነገር በገናው ለብርሃኑ የሚኖረው ቦታ ነው። (የመጀመሪያው ጉዳይ ያ ሁሉ ትርጉም ባለው ፍየል ቆዳ መሰራቱ ነው።) በገናው ዘነበች ከወለደችው ልጅ በተሻለ የራሱ መሆኑን በሙሉ ልቡ ያውቃል። የዚያን ፍየል ቆዳ አድርቆ ጉልበቱንና እውቀቱን ተጠቅሞ በራሱ ችሎታና በፍላጎቱ የሰራው ብቸኛም የመጀመሪያም ስራው በገናው ነው። በገናው ለብርሃኑ ችሎታውን ማሳያው፣ የፈጠራ ስራው ውጤት ነው። ብርሃኑ ዘነበች ከወለደችለት ልጅ በላይ ለበገናው ክብርና ትኩረት ይሰጠዋል።

የማኅበረሰቡን ፍላጎት አሳክቶ የራሱንም ፍላጎት ማሳካት ባይችልም እንኳ በዙሪያው ያሉ ነገሮችን መርሻ መጽናኛም ልንለው እንችላለን ፈጠረ። ይህ ብልሃቱ ነው በገና እንዲሰራ ያደረገው። ከእንቅልፉ እንደተነሳ፣ መሽቶ ከስራ ሲመለስ፣ በገናውን ይጫወታል። በገናው የሚፈጥረው ድምጽ እንደማያምር በገና እንደማይመስል ዘነበች ብትገልጽም እሱ ግን ግድ የለውም። በድምጹ ጩከት ዙሪያውን አጥሮ ከውጪም ከውስጥም ለሚነሱበት ጫናዎችና ውዥንብሮች ከለላ አድርጎት ነበር።

በገናው ለማኅበረሰቡ የቅጣት ማደሪያ ሆኖ አገልግሏል። "‹ትላንት እዚህ ደጃፍ ተቀምጦ ሲከረክር ሰላም ነሳኝ። ሌላ ምጥ እንደያዛት ሴት ሆንኩ። በገናም አይመስል። እንደው ሠፈሩን ሁሉ ያደነቆረ መስሎኝ ነበር› አለች ዘነበች።" (158) ማኅበረሰቡን የሚረብሽ አቋም እንዳለው ነው በጎረቤቶቹ መደንቆር አማካኝታ የምትገልጸው። ያፈነገጠ መቀጣት እንዳለበት እንደሚያምኑም "ከተደነገገለት መስመር የተዛነፈ በመታማት ይቀጣል፣ እንዲፈራም ይደረጋል። የተጠበቀበትን እንደ ሃላፊነቱ ወስዶ ያልተወጣ ይሸሙዋጠጣል።" (150-151) የሚለውን ሃቲት ያስረግጣል።

የቴንሳ ህልም ንግር ሆኖ እዚህም ጋ ይመጣል። ዘነበች ካረገዘችው ልጅ ይልቅ ከፍየሉ ቆዳ ለተሰራው በገና የብርሃኑ እንደሆነ እውቅና መሰጠቱ፣ በስራውም መመስገኑና መወቀሱ፣ የዕውቀት መለኪያውም ሆኖ ተገልጿል። ይህንንም ነገር የሚያሳይ ንግር ይመስለኛል። "የቬትናም ጦርነት" ብሎ የገለጸውም እቃውን ከሰረቁበት ጋራ መሆኑ ተያይዞ ሲታይ ከማኅበረሰቡ ጋራ ግጭት ውስጥ እንደገባና ወደ ጫካ መግባቱም መነጠሉን የሚያሳይ ነው። ከህልሙ በኋላ ስለ ጉድጓዱ ገለጻ መደረጉን ልብ ይሏል።

ይህን ነገር ከርዕሱ ጋር አያይዞ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል። ርዕሱ የሚናገረው በገናን እና ህማማትን ነው። በገናም እንዲሁ ከምንነቱና ከጠቀሜታው ጋር ሲታይ በገና በኦርቶዶክስ ዕምነት ስርዓት ውስጥ በጾም ወቅት የሚሰሙ መዝሙሮች ማጀቢያ የሆነ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በበገና የሚታጀቡ መዝሙሮች ከህመም ጋር የተያያዙ ናቸው። አንድም ሌላ ወገን ስለኛ የሆነውን እያሰብን የሱን ህመም ለማሰብና ለመጋራት፣ አንድም የእኛን በዳይነት ጥፋት ህመም ስለሚሆንብን እሱን እያሰብን በአንድ ወገን ራስን መውቀስ በሌላ ወገን ለጥፋታችን ይቅርታን መለማመን። በገና በሕማማት ሰሞን እንዲደመጥ ምክንያት የሆነውም የሚያወጣው ድምጽ ወፍራም በጣም የማይጮህና፣ (ከሌላዎቹ መሳሪያዎች አንጻር ዝቅተኛ ድምጽ ስላለው) ሃዘን ውስጥ ስለሚከት ነው። የሚያወጣው ድምጽ መንፈስን ሰብስቦ መያዝ የሚችል ነው። ብርሃኑ

በገናውን ሲጫወት ሁለት ፋይዳ ነበረው፡፡ ሃዘኑን ሃሳቡን ሰብስቦ ማዳመጥ እና በዙሪያው ባሉ ነገሮች ላለመረበሽ መከለል፡፡

ቴንሳ ሌላኛው የግብረገብ ጉዳይ የተቀነቀነበት ገጸባህሪ ነው፡፡ ልክ እንደ ብርሃኑ ሁሉ ትክክልና ስህተት የሚባሉት ነገሮች፣ በዙሪያው ያሉ ሰዎች የሚያስተምሩትና የድርጊታቸው አለመመሳሰል የትኛውን መንገድ መከተል እንዳለበት ሲያወዛግቡት፣ ሲያሳምሙትና ሲነጠል ይስተዋላል፡፡ “ግን ራሷ ወሬኛ ሆና ለምን ‹ወሬኛ› ብላ ትሰድበኛለች? ይኼ በልቤ ቋጥሬ የምዞረው እናቴ የምትሰጠኝ አንዱ ሕመሜ ነው፡፡” (119) እነሱ ቤተሰቦቹ እየሆኑ የሚያሳዩትና እርሱ እንዲሆን የሚጠብቁት ነገር ይጣረሳል፡፡

በእናትና አባቱ መካከል መተማመን ጠፍቶ በፊቱ ሲደባደቡና አባት የእናቱን ልብስ ቀዶ እርቃኗን ሲያስቀራት አይቶና አልቅሶ አባቱን ለመምታት ጣሳ ወርውሮ እየሮጠ ከቤት ይወጣል፡፡ ከቤት መውጣቱም እነሱን መጥላት መሸሽ ሊሰማቸው ሊያያቸው አለመፈለግን ያመለክታል፤ ውጪ ቆይቶ ሲመለስ ግን ታርቀው ያያቸዋል፤ ይበልጥ ይጠላቸዋል፡፡

“አስጠልተውኝ ሄድኩ፡፡ እኔን አባረው፣ እነሱ በጎን ይታረቃሉ፡፡ ይሄ ራሱን የቻለ አንድ ህመም ነው፡፡ ሳሎን የበላሁበትን ትሪ በጥፊ መታሁትና ከነያዘው እንጀራና ወጣወጥ ጋር መሬት ላይ ወርዶ ተገለበጠ፡፡” (134) በመጀመሪያ እናትየው በምትሰድበው ቃል ያውም እሷ የሆነችውን ስለሆነ፣ ታሳምመዋለች፡፡ ልጇም እሷን እያየ ወረኛ ይሆናል፡፡ ከአካባቢው ወደየትም ሄዶ ዕውቀትን ሊቀስም አይችልም፡፡ በአከባቢው ካሉ ሰዎች ውስጥ ደግሞ ከዋነኞቹ አንዷ እናቱ ናት፡፡ እሷ ወረኛ ሆና ልጇ ግን ወረኛ እንዳይሆን ትጠብቃለች፡፡ እሷ የሌላትን ባህሪ ከየት ያምጣው? እነሱ የሌላቸው ግብረገብ እንዲኖረው ይጠብቃሉ፡፡ ሁለተኛ ህመሙ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የተቀነጸለው ሃቲት እንደሚያሳየው ቤተሰቦቹ እሱ እንደሚያስበው ሆነው አለመገኘታቸውን ነው፡፡ እንዲያውም አባቱን እስከ መደብደብ የደረሰላት እናቱ እንደጠበቀው አልተንከባከበችውም፤ ወይም ትክክል ነኝ ብሎ የወገነላትን ጭራሽ ከትክክለኛ ነገር አልቆጠረችውም፡፡ ቀውስ ውስጥ ይገባል፤ አብሮት የሚሆነው ሰው ይፈልጋል፤ ይህንን ማድረግ ባለመቻሉ ግን መሸሸግና ከሰው መራቅን ሲመርጥ ይታያል፡፡

ቴንሳ አባቱን ለመምታት በቂ ምክንያት ቢኖረውም ይህንን ማድረግ እንዳይችል የሚከለክለው እሴት አለ፡፡ እሱን ሊጠብቅ ባለመቻሉም “ዱርዬ” እየተባለ ይጥላላል፡፡ ለእሱ የሚሰማው ግን እሴቱን ማፍረሱ ሳይሆን አሳማኝ ምክንያት እያለው እንደ ጥፋተኛ መቆጠሩ ነው፡፡

### 3.5.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

በገናውን ከሰራ በኋላ ለማኅበረሰቡ አካሉን ሰጥቶ በሃሳብና በአመለካከት ግን ተነጥሎ ሲኖር አንድም ልዩነትን አቻችሎ ለመኖር፣ አንድም ባህሉ እንዲገዛው ራሱን በመስጠት ዕርቅ ፈጥሮ ነበር፤ በገናውን ሲነጠቅ በደንብ ቅኝቱን ተለማምዶ አልጨረሰም ነበር። በገናው ባህላዊ መሳሪያ ነው። አዲስ የፈጠረው መንገድ ምንም እንኳ ለሱ ቢስማማውም ለአከባቢው ግን ባዳ ነበር። እንዲሁም ቅኝቱን ተለማምዶ አለመጨረሱ በአዲሱ ውሳኔው ሊደርስበት የሚችለውን ጫና ለመቋቋም የሚያስችል አእምሯዊ ብቃት አለማካበቱን ነው።

ብርሃኑ በእነርሱ ስርዓት አለመስማማቱንና ማመጹን ሚስትየው ስትናገረው ባለማናገርና ተው ስትለው ባለመተው ገልጿል። ስርዓቱን ያልተከተለ መቀጣቱ አይቀሬ ነው። ባህሉ የቀጣው ደግሞ የተመካበትንና የፈጠረውን ነገር በማጥፋት ነው። በዚህ ጊዜ ሊሰማው የሚችለው ነገር ፍጹም ነባሩን ባህል ተቃውሞ መኖር እንደማይችል ነው። ቀደም ብሎ ተነጥሎ ለመኖር ሞክሮ አልተሳካለትም። ሁሉም ነገር ድብልቅልቁ ይወጣል፣ ፍርሃት፣ እሺ ማለት፣ መታዘዝ መንገዱን መከተል ሁሉ ትርጉም አይኖረውም፤ ምክንያቱም የእርሱን አንዳችም ነገር ያገዘውና የተረዳው የለም፤ እሱ ብቻ አይደለም፤ ሊደራደረው በማይችለው እሱነቱ መጡበት እንጂ። በዚህ ጊዜ ሁለት ምርጫዎች አሉት። የገፋውን ባህል አምኖ መቀበል ወይም አለመቀበል፤ ቀጣዩ ምርጫው እስከመጨረሻ ይህንን ነገር መሸሽ ሆነ፤ እናም እራሱን አጠፋ። ።

**የውጪ ሽፋን ትንተና፦** ዙሪያውን ጥቁር ነው። መሃሉ ላይ አራት ማዕዘን (ሬክታንግል) የሆነ ቀይ መደብ። እርሱ ላይ የአረንጓዴ፣ የቢጫ፣ የጥቁር (አረንጓዴው የጎላ) ድብልቅ ቀለም ያለው በገና። በገናው ከቀዩ መደብ ጥግ እስከ ጥግ የሚዳረስ ሲሆን፣ በበገናው አራቱም ጠርዞች በኩል በተለያየ መጠን አፈንግጦ ወጥቶ ጥቁሩ መደብ ላይ ያርፋል። በገናው መስዕብ የለውም፣ ማለቴ ጌጥ የለውም። አሮጌም ይመስላል (በጣም ያረጀ)፣ በትክክል የተሰራ በገናም አይመስልም፤ ከርጥብ እንጨት የተሰራም ይመስላል።

የበገናው ሆድ ብርሃናማ ነው፤ ግን ጥቁር መስመር መሃሉ ላይ የገባበትና ዙሪያውን የከበበው ነው። ይህም ብርሃኑ ብርሃኑን (ገጸባህሪውን) ሲወክል፣ ዙሪያውን የከበበው ጨለማ ደግሞ ከኅሊናውና ከአካባቢው የሚመጣበትን ግጭት ይወክላል፤ እንዲሁም ቀዩ መደብ ራሱን ያጠፋበትን ገደል ያሳያል። (ሬክታንግል መሆኑ ለሬሳ የሚቆፈረውን ጉድጓድ ስለሚጠቁም።) ከአውታሩ አንዱ ተበጥሷል፤ ይህም ብርሃኑ ከቀንበሩ ጥብቅ የነበረና መቃኛው ጋ የተበጠሰ የሚመስለው አውታር ብርሃኑ ሚስት አግብቶ፣ ልጅ ከወለደ በኋላ ከማኅበረሰቡ ተቆርጦ

መቅረቱን (ራሱን ማጥፋቱን) ያሳያል፡፡ እንጨቶቹ ደም የነካቸው ይመስላሉ፤ በተለይም የተበጠሰው አውታር ባለበት በኩል የግራው ምሶሶ በደንብ ደም የነካው ይመስላል፡፡ ሴት ማለትም ሚስት ከግራ ጎን እንደተገኘች በሚቶሎጂ ይታመናል፡፡ እናም ዘነበች ለብርሃኑ ሞት ከፍተኛውን ድርሻ እንደምትወስድ ጠቋሚ ነው የሚል ፍካሬን ማበጀትም ይቻላል፡፡

ብርሃኑ ወንዝ ዳር ካደረ በኋላ ሲነጋ ራሱን አጠፋ፡፡ ብርሃን በብርሃን መውጫው ወቅት ወደ ጉድጓድ ጠለቀ፤ እራሱን አጠፋ፡፡ ይህም ለማኅበረሰቡ መኖርና ለሌሎችም መትረፍ ባለበት ሰዓት መሞቱን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩልም ብርሃኑ እውቀቱን ከእሴቱ ጋር አጣጥሞ መስራት በቻለበት ወቅት መነጠቁ ማኅበረሰቡ መማርን ሳይሻ ሊያስተምረው የሚጥረውን በቅጣት እያጠፋ “ዝግ ባህልን” ይዞ ሌላውን ገፍቶ ለመኖር መምረጡን ያሳያል፡፡ ባህል ከህይወት ጎዳና መሪነት ወደ ገዳይነት ይቀየራል፡፡ ወጣቱ ላይ የሚደርሰውን እየታዘቡ የሚያድጉት ህጻናትም የሚኖራቸው አቋም እሴቱን ለመቀበል እንደማይችል ያሳያል፡፡

ብርሃኑ በቁሙ እያለ ሁሉም የሚጫኑት እንጂ የሚሰሙትና የሚረዱት አልነበሩም፡፡ ሲሞት ግን ሁሉም ያዝኑለታል፤ በሰው ይታጀባል፡፡ ሁሉም ጉዳዬ ብሎ የሞቱን ነገር ይመረምራል፣ ያያል፤ ያዝናል፡፡ ብርሃኑ አስቀድሞ ተነጥሎ ስለነበር፣ አፈንግጦም ስለነበር ሃዘናቸውም የማስመሰል ነበር፡፡ ቶሎ ይረሱታል፡፡ “ዋናው ግን ለምን እንደሆነ አላውቅም ለብርሃኑ በትክክል ግድ የሰጠው ሰው አልነበረም፡፡ አብረውት ቡና ጠጥተው፣ በልተው፣ ስቀውና አሳስቀው የፈለጋቸውን ሆነው፣ ሲረሱት አየሁ፡፡” (166) ሞቶ አመት ሳይሞላው ዘነበች ሌላ ባል አግብታ አረገዘች፡፡ ብርሃኑን ስታገባ ያልነበረ ሰርግ ተሰርጎ ነው ያገባችው፡፡ አስለቃሽ የነበረችው ሴትም ዘፈን አውራጅ ትሆናለች፡፡

ቴንሳ የክፍል አጋሩ የሆነችን አንዲት ልጅ ብዙ ላስቲክ ይዛ ስላያት እንድትሰጠው ይጠይቃታል፤ አልሰጥም ስላለችው ይነጥቃታል፡፡ በዙሪያው ያሉ ሰዎች ያስተማሩት መቀማትን ነውና፡፡ ብርሃኑ ፍየሉን ቀሙት (አሳረዱት)፤ በገናውን ቀሙት (ለሰው ሰጡበት)፡፡ ስለዚህ እንቢ የሚልን መቅጣት ነው እንጂ ማስተማርን አላወረሱትም፡፡ እሱንም በተግባር ያሳያል፡፡ ልጅቷን ቀምቷት ሲሮጥ ሁሉም እየቀሚት ሮጡ፡፡ አንዱ ካንዱ የሚማረው ጥፋትን እንጂ ግብረገብን እንዳልሆነ ያሳየናል፡፡

ቴንሳ በልጅነቱ ያሳለፈው ሕይወት ነበር የብርሃኑ ታሪክ፡፡ በልጅነት ወቅት የሚስተናገዱ ክስተቶች ደግሞ የተገቢነትንና የኢ-ተገቢነትን ደንቦች መማሪያዎች ናቸው፡፡ ቴንሳ አስቦት

የማያውቀው ነገር እንደተከሰተ ይገልጽና ሲያብራራው ጡትና ጭን ነበር ያየው፣ ከዚያ ሁሉም ነገር ይቀየራል፡፡ ወሲባዊ ስሜትን ማጣጣም ጀመረ፤ ወደ ወጣትነት ሽግግር ማድረጉን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የብርሃኑን ነገር፣ የቤተሰቡን ነገር፣ የራሱንም ነገር ሁሉ ይዘነጋና አዲስ ሰብዕና ይገነባል፡፡ ከንጥቂያው ጋር የተያያዘ ነው፡፡

የቴንሳ እናትና አባት አባቶች ናቸው፤ ብርሃኑ ወጣት ነው፤ ቴንሳ ደግሞ ልጅ ነው፡፡ የብርሃኑ ከመሃል መጥፋት፣ አንድም በጎጻናቱና በአባቶች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ይህ በራሱ ይዞት የሚመጣው ችግር አለ፡፡ አባቶቹ ፍጹም ባህላዊ መሆን ሲፈልጉ ልጆች ደግሞ በዚህ አያምኑም ሊያስታርቃቸው የሚችለው ብርሃኑ ነበር፤ በሁለቱ መካከል ቆሞ፣ ሁሉንም ስሜቶች ይዞ ከአንዱ ወደ ሌላው በተጣጣመ መልኩ የሚያሻግር ድልድይ እሱ ነበር፡፡ በዚህ ድልድይ መሰበርም የመጽሐፉ ጭብጥ የሆነው ባህላዊነትና ዘመናዊነት፤ ደመነፍሳዊነትና ግብረገባዊነት "ተሸምኖ" ቀርቧል፡፡

ቴንሳ ወደ ወጣትነት እድሜው ሲሻገር የሚታየው ትዕይንት የገነባው ማንነት ትላንትን መሰረት ያላደረገ እንዲያውም የረሳ መሆኑ ይህን ይጠቁማል፡፡ አውላላ ሜዳ መሐሉ ላይ ጥቁር ለስላሳ ጠፍጣፋ ጥቁር ድንጋይ ተጫውቶ የደከመው የሚያርፍበት እሱን ከቦታው ፈንቅሎ ሲጥለው፤ ቢራቢሮ አገኘ (መሰረትን ትመስለዋለች) ቢራቢሮዋ ሁሉም ቀለሞች አሏት፤ እሷን ካየ በኂላ ሁሉንም የማያውቅ መሰለው፡፡

አውላላ ሜዳው ባህል ነው፡፡ ሁሉም ተጫዋቾች በሜዳው ውስጥ አሉ፡፡ ማኅበረሰብ ደግሞ በፈጠረው ባህል ውስጥ ይኖራል፡፡ በሱ ውስጥም እንቅስቃሴውን ያካሂዳል፡፡ ድንጋዩ ግብረገብ ነው፤ ማዕከላዊ ሆኖ እንቅስቃሴያቸውን የሚወስንላቸው፡፡ ቴንሳ እስኪፈነቅለው ድረስ ሌሎች ይቀመጡበታል እንጂ በስሩ ምን አለ ብለው አይመረምሩም፡፡ አንዱ ሲያደርግ ያየውን ሌላው እየተቀበለ ያደርጋል፡፡ ቴንሳ ግን ድንጋዩን ይፈነቅለዋል፤ ሲፈነቅለውም አዲስ ነገር ያገኛል፡፡ ብርሃኑ ያስነሳውን አይነት አመጽ ያነሳል፤ ሁሉም ለመቀመጫነት ይጠቀመው የነበረውን እሱ ይፈነቅለዋል፡፡ አንድም ነባሩን ግብረገብ ሲገለገልበት ቆይቶ ሃሳቡን ይቀይራል፤ ከስረ መሰረቱ ምን እንዳለ ለማወቅ ይመረምራል፡፡ ድንጋዩ ስር ቢራቢሮዋ ልትቀመጥ አትችልም፤ ይጨፈልቃታላ (ድንጋዩ ጠፍጣፋ ነው፡፡ ጠፍጣፋ ከሆነ ደግሞ ቢራቢሮዋ በየት በኩል ትገባለች እንዴትስ ትወጣለት፣ ተለጥፋም አልነበረም ከስሩ ነበረች፡፡) ያደገበት ባህል ምን ያህል ተፈጥሮን ሲያምቅና በነጻነት እሱ የሚፈልገውን እንዳይሆን ሲያደርገው እንደነበረ ነው፡፡ ስሩን

ማወቅ ነው የፈለገው የግብረገቡ ስር ደግሞ ተፈጥሮን የተጫነ እንጂ ጎን ለጎን የሚያስኬድ አይደለም፤ የሚለውን ፍቺ ያመጣል፡፡

ከዚህ በኋላ ቢራቢሮዋን ይዞ፣ ወደ ዕውቀቱ ይመለሳል፡፡ ራሱን አያውቅም፤ ቤተሰቡን አያውቅም፤ ብርሃኑንንም አያውቅም፡፡ ቀደም ሲል የነበረው ዕውቀት በዙሪያው ያሉ ነገሮች አውቆ ሳይሆን በደፈናው (ሌላው ሲያደርግ ያየውን፣ የሰማውን) ሲከተል እንደኖረና መመርመር ሲጀምር (ቢራቢሮዋን እንዳገኝ ሁሉ) አዲስ ግን የነበረውን ነገር ያልለቀቀ ዕውቀት (ግብረገብ) እንዳገኘ ያሳያል፡፡ ቢራብሮዋን እንዳያት "ጥቁር የምታብለጨልጭ" ነበረች፡፡ በኋላ ግን እየዘረዘረ ሁሉም ቀለሞች እንዳሏት ይገልጻል፡፡ በመጀመሪያ ያየው የግብረገብ መሰረቱ ተፈጥሮን ተጭኖ እንደተገነባ ሰዎችም ስሩን ሳያዩ ሲከተሉት እንደነበረ ነው፤ ምክንያቱም ድንጋዩ ጥቁርና የሚያብለጨልጥ መሲሆን ቢራቢሮዋም መልክ ተመሳሳይ ነበር፤ ይህም አዲስ ነገር ይይ እንጂ መልኩ ተመሳሳይ እንደነበር ይጠቁማል፤ በኋላ ግን የተለያዩ ቀለማትን መመልከት ይችላል፡፡ ይህም ምክንያታዊ ሆኖ ያገኘውን አዲስ ዕውቀት ሲመረምር የተለያዩ ነገሮችን መመልከት መቻሉን ነው፡፡

በዋናነት አትሌት መሆን እየፈለገች ባል እንድታገባ የምትገደደው ማርታ፣ መሆን እሚፈልገውን እንዳይሆን የሚደረገው ብርሃኑ፣ በፍዝ እነሱ የሆኑትን ስለሆነ የሚሰደበውና የሚታመመው ቴንሳ፣ አልሰጥም ስላለች ያላትን የምትቀማው አስካለ ባህል የሕይወት መምሪያ መንገድ ሊሆንላቸው አልቻለም፤ ምክንያቱም የማኅበረሰቡ እሴት ለእነሱ ተፈጥሯዊ ተሰጧቸውን፤ ፍላጎታቸውን እንዲያወጡ ነጻነትን አይሰጣቸውም፡፡ ስለዚህ በእርሱ ላለመመራትና የራሳቸውን እሴት ለማበጀት ይጥራሉ፡፡ ቤተሰቦቻቸውም እናስተምራቸዋለን ብለው የሚጥሉባቸው ቅጣትም የተሳሳተ ትርጉምን እያበጀ እንዲነጠሉ ወይም የአእምሮ እክል እንዲገጥማቸው ያደርጋል፡፡ መነጠላቸውና ለአእምሮ ህመም መዳረጋቸው ከቅጣቱ መባስና ከፍራቻቸው ጋር ተዳምሮ በማስመሰል የሚኖሩትን ስርዓት በማበጀት ዕርቅ ቢፈጥሩም የቤተሰባቸውን እሴት የሚወርሱና ባህሉን የሚያስቀጥሉ ሳይሆኑ "የአርቴፊሻል" ባህል ባለቤት ይኾናሉ፡፡

## 3.6 “የምስራች! ልጅ እንደ እናቷ ኾነች”

### 3.6.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

ኤልያስ በተደጋጋሚ በትምህርት የሚወድቅና “አርቤሸት” የተሰኘውን ጨዋታ የሚወድ ልጅ ነው። ይህን ጨዋታ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዳይጫወቱ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ወደ ስድስተኛ ክፍል ለመግባት ሁለት ጊዜ ወድቋል። ጎበዝ ታናሽ ወንድም አለው። ወደ ስድስተኛ ክፍል ለመግባት ለሶስተኛ ጊዜ መፈተን እንዳለበት ሲነግሩት ለወንድሙ ሦስት ብር ሰጥቶት እንዲፈተንለት አደረገ፤ እና አለፈ።

ሰናይትና ምንውየለት የተባሉ ተማሪዎችም አብረው ለመፈተን ስማቸው ተለጥፎ ነበር። የምንውየለት አባት ርዕሰ መምህሩን ስላናገረው እና ሰናይት ደግሞ ከርዕሰ መምህሩ ጋር ስለወሰለተች አልፈዋል። ኤልያስ የምንውየለትን ነገር ምንም አይልም። የሰናይት ነገር ግን ሁል ጊዜ ያናድደዋል። እርሱ በትክክል ተፈትኖ ያለፈ ይመስል ሰናይት ከርዕሰ መምህሩ ጋር ያደረገችውን ነገር ለሁሉም ለመናገር ይፈልጋል።

የኤልያስ አባት የክፍለ ሃገር ባስ ሹፌር ነበር። ገና ተረግዞ እያለ ነው በመኪና አደጋ የሞተው። ለእናትየው ኤልያስ የባሏ ማስታወሻ ነው። በጣም ትወደዋለች፤ ምንም ቢያጠፋ አትቆጣውም፤ ትመክረዋለች እንጂ። ግን ትመክረው፣ ትመክረውና ማጥናት ሲጀምር “አልለመድከውም ይደክምሃል ና ተኛ ኤርሚያስ ያጥና” (65) ትለዋለች፤ ለመግደርደር ትንሽ ቁጭ ሲል በቁጣ ወደ መኝታ ትጋብዘዋለች። አስተማሪዎቹም “አርቤሸት” እንዳይጫወት ያስፈራሩታል፤ እነርሱ ግን ካርታ ሲቆምሩ ያያቸዋል። ስለዚህ እነሱ እርሱን ሲያስፈራሩት፣ እሱ ያንን ማድረግ እንደማይችሉ ውስጡ ያምናል፤ ተደብቆም ይጫወታል።

በኤልያስ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ይመክሩታል፤ ይቆጡታል፤ ያስጠነቅቁታል፤ ይመክሩታል ነገር ግን ለሱ የሚነግሩትን እነርሱ አይፈጽሙትም። ፊት ለፊት የሚነግሩትና ተደብቀው የሚያደርጉት የሚጣረሱ ናቸው። የኤልያስም ባህሪ የተቀዳው ከነሱ ነው። እናትየው እንዲያጠና ብትመክረውም ማጥናት ሲጀምር ተኛ ትለዋለች። እንደሚደክመው አስባ ቢሆንም ኤልያስ ግን የሚሰማው ይህ አይደለም። እነርሱ ሲተኙ ቁጭ ብሎ የሚያጠናው ወንድሙ ጎብዞ እያለ አንተ አልለመድከውም ተኛ ስትለው። ወንድምህ ካንተ የተሻለ ነው፤ ጎበዝ ነው፤ እሱ ጠንካራ ስለሆነ ማጥናት ይችላል፤ አንተ ግን ይህንን ማድረግ አትችልም የሚለውን ነገር ነው የሚያሳስበው። ከዚህም በተጨማሪ እናትየው ኤልያስ አምሽቶ እንዲያጠና አትፈልግም። ለምን? ቢባል ጠረኑን

እያሸተተች፣ ጸጉሩን እየዳበሰች፣ አቅፋው ከባሏ ጋር ያሳለፈችውን ፍቅር ማስታወስ ትፈልጋለች፡፡

የኤልያስ እናት፡- የኤልያስ እናት የትዝታዋ እስረኛ ናት፡፡ ከባልዋ ጋር ያሳለፈችውን እያንዷንዷን ቅጽበት የምትመለከተው በኤልያስ ውስጥ ነው፡፡ በልጇ ውስጥ የምትፈልገውም የምታየውም ባሏን ነው፡፡ ይህ ነገር ደግሞ ኤልያስ እንደ ልጅነቱ ትኩረት እንዳያገኝና እና እንዳታግዘው አድርጓታል፡፡ እንደፈለገ ቢሆን አትናገረውም፤ አትቆጣውም፡፡ ስራ እንኳ እንዲሰራ የምታደርገው ትንሹን ወንድሙን ነው፡፡ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክል ይመስለዋል፤ እናም የእናቱ ምንም አለማለት ደግሞ ይህን ትክክል የመሰለውን ስሜት ያረጋግጥለታል፡፡ ማንበብ ሲጀምር እንኳ እንዳያነብ ታደርገዋለች፡፡ በዚህ እኔ ላንተ ብዬ ነው ከሰካርም ጋር የምጣላው፣ የሆነነገር ብሆን ምን ትሆናለህ? ቢያንስ ዕውቀት ይኑርህ! ትለዋለች፣ በዚህ ይከብድሃል፤ ተወው አታጥና፤ ተኛ፤ እያለች በቁጣም ጭምር ታዘዋለች፡፡ ታዲያ ልጅ የቱን ይስማ? እናት አንዷ የእሴት አስተማሪ ናት፡፡ ይህች እናት ግን የልጆቿን ግብረገብ መቅረጽ አልቻለችም፡፡ እንዲያውም መጥፎያቸው ስትሆን ይታያል፡፡

በተጨማሪም እናት ኤርሚያስን ከማን እንደወለደችው ባይገለጸም እንኳ ከልጆቿ ጋር ካላት ተራክቦ መረዳት እንደሚቻለው እናታዊ ባህሪ የላትም፡፡ የደመነፍሳዊ ስሜቷ ተገዢ ናት፡፡ ሁለቱ ልጆቿ ከተለያዩ ወንድ የተገኙ እንደመሆናቸው ለእነሱ ያላትን ስሜት ነው ለልጆቿ የምታሳየው፡፡ ኤርሚያስ ያግዛታል፤ ይደክማል፤ ጎበዝ ነው፤ ግን ፍቅርና እንክብካቤዋን አያገኝም፡፡ ይህም ለአባትየው ካላት ስሜት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ኤልያስ እያጠፋ እየሰነፈ እንኳ እንዲሻሻል ትመክረዋለች እንጂ አትቆጣውም ይህም ለመጀመሪያ ፍቅረኛዋ ያላትን ጥልቅ ስሜት የምታሳይበት መንገድ ነው፡፡ ከሱ ጋር የነበራትን ፍትወታዊ ስሜትም በልጇ ለማግኘት ትጥራለች፡፡ ከባሏ ጋር የነበራት ስሜት ታምቆ እንዳለ ነው እሱን በተለያዩ መንገዶች ለማርካት ትሻለች፡፡ እሱን ብቻ ነው አቅፋው የምትተኛው፡፡ አቅፋው ስትተኛ፣ ጸጉሩን ስትደባብስ የምታስታውሰው ባሏን ነው፡፡ ሌላኛው ልጇ ለብቻው ነው የሚተኛው፡፡

ወንድምየው ኤርሚያስ፡- ፈተና ተፈተንልኝ ሲለው ወደፊት እንደምታጠና ቃል ግባልኝ ይለዋል፤ ኤልያስ ቃል ይገባል፤ ግን እንደማያደርገው ያውቀዋል፤ በርግጥ ታናሹ ነው፤ ታናሽየው ሲፈተንለት ትክክል አለመሆኑን ኤርሚያስ ያውቃል፡፡ ከማን ተማረው? ትክክል አይደለም እያሉ ማድረግን? ከእናትየው፡፡ እናትየው አጥና፣ እሱ ነው ትክክለኛው ነገር

ትለዋለች ግን ደሞ ተኛ ትለዋለች፤ ከተኛ ደሞ አያጠናም፡፡ ስለዚህ ወንድምዬው የሚሰራው ስራ ትክክል እንዳልሆነ እያወቀ ይፈተንለታል፡፡

ኤርሚያስ ወንድሙን መበቀል ይፈልጋል፡፡ እናትየው ለኤልያስ በጣም ስለምታደላ ፍቅሯን ማግኘት አይችልም፡፡ ስለዚህ በተቻለው አቅም እሱን በልጦ ለመገኘት ይጥራል፤ በትምህርቱ ጎበዝ ነው፣ ታዛዥም ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን የእናትየውን ትኩረት እንዲያገኝ አልረዱትም፡፡ ወንድምየው መጥቶ እንዲፈተንለት ሲጠይቀው በቃል ሽፍኖ ይፈተንለታል፡፡ አንድም ወንድምየው የእርሱን ርዳታ ፈላጊ በመሆኑ የበላይነቱን ያሳይበታል፤ አንድም ኤልያስ በራሱ ጥረት እንዲሳካለት ከመርዳት ይልቅ በስንፍናው ሁሌ ጥገኛው ሆኖ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ ይህም በአካባቢው የሚደርስበትን ትችትና የስሜት ህመምን እንደሚያስከትል ስለሚያደርገው በቀሉ የተሳካ ነበር፡፡

ኤልያስ፡- እርሱ እውነተኛ ነበር፤ አይኮርጅም፡፡ እውነት ነው ብሎ ላመነበት ነገር ለመገዛት ይጥር ነበር፡፡ በዙሪያው የሚያየው ነገር ግን በማስመሰልና በጥቅም ላይ የተገነባ ነው፡፡ ሰናይት ምንም እንዳልተፈጠረና ፈተናውን ተፈትና እንዳለፈች ሁሉ አዳዲስ ደብተር ይዛና አዲስ ጆሮ ጌጥ አድርጋ ሲያያት፣ አስተማሪዎቹ የዱርዬ ጨዋታ ነው ብለው እነርሱን እየቀጧቸው እነሱ ግን ሲቆምሩ ሲያይ፣ የእናትየው የውሸት ምክር፣ የወንድምየውም የውሸት ምክርና ቃል፣ እንዲሁም ርዳታ ሁሉ ውሸት ይሆኑበታል፡፡ የእርሱ እውነተኛነት ምንም ጥቅም አይኖረውም፡፡ ማንም አለመኮረጁንና ፈተናውን ለመስራት መጣሩን አያዩለትም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከሌሎች ጋር እያወዳደሩ እንደሌሎቹ እንዲሆን ይጎተጉቱታል እንጂ ማንም በእሱ ማንነት የሚያየው የለም፡፡ ምናልባት ትምህርቱን ሊቀበል (ሊረዳው) ያልቻለበት አንዳች ምክንያት ይኖረዋል፤ ምናልባት በሆነ መስክ ስኬታማ የመሆን እድል ሊኖረው ይችላል፡፡

በዙሪያ ያሉ ሰዎች ትጋትን አላስተማሩትም፡፡ እናትየው አስተማሪዎቹና ወንድምየው እሱን ያገዙት የረዱት ይመስላቸዋል፤ ግን የሚያደርጉት ነገር ተቃራኒውን ነው፡፡ ነገር ግን ትጉህና ሰናይ ምግባር ያለው ሊያደርጉት ይጥራሉ፡፡ ግጭቱ በራሱ ላይ ይፈጠራል፡፡ ሁሉን ነገር ተጠራጣሪና ጠያቂ ይሆናል፡፡ የእናቱን ፍቅር እውነትነት፣ የወንድሙ እሱን ሊረዳው (ሊፈተንለት) ለምን እንዳሰበ፣ አስተማሪዎቹ የሚሏቸውን የሚጠይቁትን ሁሉ እያነሳ፣ የሚመለከተውን ሁሉ እያመሳከረ ዙሪያውን በጥርጣሬ ያያል፡፡ ተራኪው "…አብራርቶ ሊያስረዳው የማይችል መጠራጠር ልቡን ሞላው…" (73) ብሎ ከገለጸ በኋላ የሚያስበውን ነገር እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡

*"ወንድሜ ማነው? ከየት መጣ?*

*በአባት አንመሳሰል በመልክ አንመሳሰል……*

*እናቴስ የምታቅፈኝ እውነቷን ነው?*

*ወንድሜስ የተፈተነልኝ ለሶስት ብሩ ነው?*

*አዎ! ሠናይት ያለፈችው ባለፄ ነገር ሠርታ ነው……እስከ ዛሬ ፈተና ብኮርጅ ኖሮ አልወድቅም ነበር……ደ'ሞ አርቤሽት መጫወት የዱርዬ ስራ ነው ይሉናል……ያስፈራሩናል……እነሱን ማንው የሚያስፈራራቸው?" (73)*

ይህ የሚያሳየው ኤልያስ በዙሪያው ያሉ ሰዎች የፈጠሩበትን የአእምሮ እክል ነው፡፡ ትክክል የሆነውና ያልሆነው፤ መሆን ያለበትና የሌለበት ይዘበራረቅበታል፡፡

ትምህርት እሴቶቹን የሚማርበት መንገድ ነው፡፡ እሱነቱን የሚገነባበትም ጭምር፡፡ ኤልያስ ትምህርቱን ለመማር አለመፍቀዱ የሚያሳየው ባህሉን ላለመውረስና ላለማወቅ የሚያደርገውን ግፊት ነው፡፡ ይህን ግፊት ደግሞ በአካባቢው ያሉ ሰዎች መከላከል ስለሚፈልጉ እንዲማር ይጫኑታል፡፡ እሱ ግን ትምህርቱን ገፍቶ ቁማር ይጫወታል፡፡ በተጨማሪም እናትየው እንዲሆንላት የምትፈልገውን አይነት ሰው ሊሆንላት አልቻለም፤ ለመሆንም ፍላጎት የለውም፡፡

### 3.6.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

የሚቀጥለው ትዕይንት "ከእለታት አንድ ቀን" ብሎ ነው የሚጀምረው፡፡ ከዚያ የሚከሰተው ኤልያስ አልጋ ላይ መተኛት አስጠላኝ ብሎ መሬት ላይ ሲተኛ ነው፡፡ መሬት ላይ የመተኛት ወይም ለመተኛት የመፈለጉ ጉዳይ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡ አንደኛ አልጋው ላይ ሲተኛ እናቱ አቅፋው ነበር የምትተኛው፡፡ ይህን መታቀፉንና ከእናቱ ጋር መተኛቱን አልፈለገውም፡፡ ስለዚህ አልጋው ላይ መተኛትም የእናቱን ጠረን ማሽተትም፣ ከወንድሙ ጋር መተኛትም ጠልቶ መሬት ላይ ይተኛል፡፡ የጥላቻው መንስኤ ፍትወታዊ ስሜቶችን መረዳት መቻሉ ነው፡፡ እናትየው ለምን እንደምታቅፈው፣ ለምን እንደምታሻሸው ሲገባው ጥላቻ ያድርበታል፤ ስለዚህ ከሷ መራቅ ይሻል፡፡

እሱ ተኝቶ ወንድምየው ቁጭ ብሎ ሲያጠና ይስቅበታል፡፡ ኤልያስ በዙሪያው ያሉ ሰዎች ግድ አይሰጡትም፡፡ እያንዳንዱን ነገር እያብሰለሰለ ምላሽ ለማበጀት ይጥራል፤ እሱም ግድ የለሽ

መሆን ነው። እዚያው ቤት ውስጥ በመሆኑ ግን በማስመሰል እንደ ልጅም እንደ ወንድምም ሆኖ ይኖራል። ባህል አንድ አካል ግን አይደለም፤ ባለቤትነት ስሜትም አይሰማውም፤ የተነጠለ ነው።

## 3.7 "መንገዶች ሁሉ ወደ ዘሴ ይወስዳሉ"

### 3.7.1 የተፈጥሮና የባህል ግጭት

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሳባ፣ አዳነና ዘሴ ይቃኛሉ። አዳነና ሳባ ፍቅረኛሞች ናቸው። ሁለት አመት ያህል አብረው ቆይተዋል፤ ሁልጊዜ ተቃጥረው ሲገናኙ "ደሴ ሆቴል" አልቤርጎ ውስጥ ያሳልፋሉ። በስተመጨረሻ ግን ሳባ ሁሌ አልቤርጎ ውስጥ መተኛት እንዳስጠላትና የራሱን ቤት እንዲያገኝ፣ አለበለዚያ እንደሚለያዩ ትነግረዋለች። ዘሴ የአዳነ ጓደኛ ቢሆንም በእድሜው ትልቅ ነው። አዳነም እንደ ታላቅ ወንድሙ የሚቀርበውና የሚወደው ጓደኛው ነው። ሳባም ዘሴ ምንም እንደማይረዳውና በእድሜ ከሚበልጡትና ስለሱ ከማያስቡ ሰዎች ጋራ ጓደኛ እንደሆነ እያነሳች ታብጠለጥላቸዋለች። በዚህ ጭቅጭቅ ተለያይተው እርሷን ወደ ቤቷ ታክሲ አስይዞ እርሱ ወደ ዘሴ ቤት ይሄዳል። ቤት እንዲፈልግለትና እንዲረዳው ሊያማክረው። ዘሴ ቤት ደርሶ ውይይት እንደጀመሩ ከውጪ የሴት ድምጽ ይሰማል። ዘሴ ስለዘገየባት ወይም ከውጭ ዝናብ ስለሆነም በሩን ከፍታ ሳባ የዘሴን ስም በቁልምጫ እየጠራች ትገባለች።

ሳባ አዳነ ፊት ዘሴ ስለእርሱ እንደማያስብ ማለትም የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስከበር የሚጥር ሰው እንደሆነ፣ በእድሜ የገፋ ሰው እንደሆነ ወዘተ እያነሳች ስታብጠለጥለው ነበር። የራሳቸውን ነገር እያመቻቹ ስለሱ ግድ የሌላቸው ጓደኞች እንዳሉት ስትገልጽ ነበር። ዘሴም አዳነ ሳባን እንዲተዋትና ሌላ ጓደኛ እንዲፈልግ ይመክረዋል፤ "እንደምትደብረውም" ጭምር ይገልጻል።

ሳባ በማስመሰል የተሞላች ናት። ከአዳነ ጋር እስከተጨቃጨቁና ዘሴ ቤት እስከተገናኙበት ቀን ድረስ እንደምታፈቅረው እድለኛ እንደሆነ እንዲሰማው ስታደርግ ነበረ። ከዘሴ ጋርም እንደዚያው የድብቅ ወዳጅነት አላት። ልክ እንደሌሎቹ ታሪኮች ሁሉ በግልጽ ተገቢ ነው ተብሎ የሚደረግና በድብቅ አይገባም ተብሎ የሚታሰብ ነገር ሲደረግ ይታያል።

በመጀመሪያ ዘሴ ለአዳነ ስለፍቅራቸው ጥሩነት "ከአንድዋ ጋር እንዲህ መሆንህ የመልካም ፍቅርና የፀባይ ጥራት ምልክት ነው" (106) እያለ ይገልጽለት ነበር። ይህን ሀቲት በሁለት መንግድ ማየት ይቻላል። አንድ ትክክልና ስህተት ነው ብሎ ለአዳነ የሚነግረው ዘሴ፣ ትክክል

ነው ያለውን ነገር እርሱ አይኖረውም፤ አንድ ለአንድ መወሰን ተገቢ ነገር ነው ብሎ የደነገገው ዘሴ በድብቅ ከሳባ ጋር ግንኙነት በመፍጠር የራሱን ሕግ ይጥሳል፡፡

ሁለተኛ የማያምንበትን ነገር ነው ለማስተማር የሚጥረው፡፡ ለዛ ነው ግብረገባዊ ታናሾችን መፍጠር ያልቻው፡፡ ሳባ ከአዳነ ጋር መቆየት አልፈቀደችም፤ በድብቅ ትደርብበታለች፤ ምክንያቱም ግብረገባዊ ድንጋጌዎቹ በአስተምህሮ እንጂ በተግባር እንደማይሰሩ ትረዳለች፡፡

አዳነና ሳባ የሚጣሉት ወይም ሳባ የመለያያ ምክንያታችን ይሆናል የምትለው "ቤት"ን ነው፡፡ ሳባ የሄደችውና እምነቱ የሚናደው ዘሴ ቤት ውስጥ ነው፡፡ የተገናኙት ካፌ ውስጥ በድብቅም እንኳ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ ሌላ ይሆን ነበር፡፡ ምናልባትም ቤት እንዲፈልግላቸው ልትነግረው ይሆናል ብሎ ማሰብ ይቻላል፤ ግን አይደለም፡፡ ቤቱ ብቻ መሆኑ አይደለም በዚያ ቤት ውስጥ ድርሻ አላት በራሷ ቁልፍ ከፍታ ነው የገባችው፡፡

ቤት ከለላ ነው፡፡ አንድም ከአውሬ፣ ከጸሃይ ከዝናብ የምንሸሸግበት፤ አንድም ድርጊታችንን ከመሰሎቻችን (ሰዎች) የምንደብቅበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ያሰለቻት፣ እንድትማረርና እንዲጣሉ ያደረጋቸው ምክንያትም ቤት ነው፡፡ "አልቤርጎ" ብዙ ሰዎች የሚያርፉበት፣ የብዙዎች ላብና ጠረን ያጎደፈው ነው፡፡ ሳባ የራሳችን ቤት ይኑረን ስትል ጨምራ የምትገልጸው ነገር አለ፡፡ "ምን ይነካኛል? የራሳችን የሆነች ቤት ካገኘን……ይበቃናል፡፡ ቢያንስ ብርድ ልብሱና አንሶላው የእኛ ነው፡፡" (110) ይህ ጥያቄዋ የአንድ ቀን ብቻ አይደለም፡፡ ሌላም ጊዜ አንስታዋለች፡፡ ሌላ ቀን ግን "ይሁን፤ ይሁን" ብለው ነበር የሚያልፉት፡፡ ለጥያቄዋ መልስ መስጠት አልቻለም፡፡ እሷ የምትፈልገው የምትሸሸግበትን ነው፡፡ አዳነ ደግሞ በግላጭ የሚታይ ፍቅር እንጂ በነጻነት እንደፈለገች የምትሆንበት የራሷን አሻራ ማሳረፍ የምትችልበት ቤት የለውም፡፡ ምንም እንኳን ባይሳካለትም ቤት ፍለጋ በዝናብና በጭቃ መኳተኑ እረፍት ሲሰጠው ይታያል፡፡ በፊት "ልክ ነሽ፤ ልክ ነሽ፡፡" ሲላት ቆይቶ ከተጣሉ በኋላ አጥብቆ ሊፈልግ ብርታቱን ሁሉ የሚሰበስበው ለቤት ነው፡፡ ብዙ ጊዜያቸውን (የሚወሃዱበት "መርፌና ክር" የሚሆኑት) የሚያሳልፉት የራሳቸው ባልሆነ፣ የሌላውን ጠረን በያዘ፣ ባረጀ አልቤርጎ ውስጥ ነው፡፡ ያስጠላትና ያማረራት ነገር ቤት ብቻ አይደለም፤ ለውበቷ መጠበቅ የምትወደው ኬክና ለስላሳም ጭምር ነው እንጂ፡፡

አልቤርጎ ማህበረሰቡ የሰራላቸው ጎጆ ነው ባህል፣ ልማድ፣ እሴት፤ ይህን ኖሩበት ግን የራሳቸው ነገር የላቸውም፡፡ ሌሎች በኖሩበት ታዛ ስር መኖር እንጂ የራሳቸውን መቀለስ አልቻሉም፡፡ ሳባ ሊኖረን ይገባል የምትለው ጎጆም የራሳቸውን እሴት ለመገንባት በማለሟ ነው፡፡

የሷ ሆነ ጥበቧን የምታሳርፍበት ነገር ትፈልጋለች፡፡ ልክ ብርሃኑ ወንድነቱ ሚናውን እንዲወጣ ማኅበረሰቡ ሲገፋው እንደነበረው ሁሉ ሳባም በሴትነቷ ሚና መወጣት ትፈልጋለች፡፡

ከአልቤርጎው ሲወጡ በጣም ከባድ ዝናብና ውርጭ ነበር፡፡ መሸሸጊያ አላገኙም በረንዳ ላይ ቢቆሙም ሊጠልላቸው አልቻለም፡፡ ሃይለኛና ፈጣኑ ዝናብ ሲያባራ ካፌያ ተተካ፡፡ ሳባ ካፌያውን ታግሳ ማሳለፍ አልቻለችም፡፡ ደሳለኝ "ታገሽ" ሲላት እንቢ "ይመሽብኛል" አለችው፡፡ "‹ትንሽ ቆዩ……እንበሰብሳለን፡፡ ይኼም ያልፋል› ‹አይሆንም ይመሽብኛል›" (112) ቤት መሸሸጊያ ነው ብያለሁ፡፡ ይህ መሸሸጊያ ቢኖር ኖሮ የዝናብ ዶፍና የውርጭ ውሽንፍር አይወርድባቸውም ነበር፡፡ በመቀጠል ዝናቡ አዲስ የተሰራችውን ጸጉሯንና የምትወደውን ቀሚሷን አበላሽቶባታል፡፡ ዘሴ ቤት ብትሆን ይህ እንደማይደርስባት ልብ ይሏል፡፡

ከባዱ ዝናብ ግጭታቸው የከረረበትን ወቅትና ሁኔታ መስሏል፡፡ ለዚህ ግጭት እልባት ለመስጠት ሁለቱም ይጥራሉ፡፡ እርሱ በቸልተኝነት ያከረመውን ቤት ለመፈለግ፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አልቆረጠም ነበር፡፡ ለዚያ ነው መጀመሪያ ዝናቡ ይለፍ፤ ቀጥሎ ካፊያው ይለፍ፤ እያለ በአሮጌ ታዛ ስር ለመሸሸግ የፈለገው፡፡ ሳባ ግን ከባዱን ዝናብ ተጠለለች፤ ታገሰች፣ ከዚያ ለመሄድ ወሰነች፡፡ እንድትቆይ ሲጠይቃት የሰጠችው ምክንያት "ይመሽብኛል" የሚል ነበር፡፡ አዳነ ታገሽ ይላታል፤ እስከመቼ? ይህ ጥያቄ ያሳሰባት ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ይመሻል እድሜዋ ሁሉን ማድረግ የሚችለው አቅሟ እየደከመ እየመሸ ነው የሚሄደው፡፡ በሌሎች ቤት ኖራ የራሷን ቤት ሳትቀይስ መሞት ያሳስባታል፡፡ የሳባ ሃሳብ ለሕይወት ዘመኗ ብቻ አይደለም፤ ስለዘላለማዊነትም ታስባለች፡፡ አሻራዋን ጥላ ስሟ ሲታወስ የምትኖርበትን ነገር ትሻለች፡፡

ጥንዶቹ ሁለት አመት አብረው ነበሩ፤ ለውጥ የለም፡፡ እርሷ መለወጥ ትፈልጋለች፤ ታምጻለች፡፡ እርሱ እንዳለ መቆየት ይፈልጋል፤ ከሌሎች ጋር መጋፈጡን ይፈራዋል፡፡ ሳባ ግን አትፈራም፡፡ ይህንንም ካፊያውን መድፈሯ ይጠቁማል፡፡ የዘሴን ቤት መዝጊያ አጥብቆ ይመለከታል፡፡ ቀለሙን አቅሙን ሁሉ ይገልጻል፡፡ እንዲያውም መቀርቀሪያውን "የሰከረ ዝሆን የሚያስቀር ነው" ብሎ ይገልጸዋል፡፡ ይህን ጠንካራ መዝጊያ ከፍታ የምትገባው ሳባ በራሷ ቁልፍ ነው፡፡ መዝጊያው ያን ያህል ጠንካራ ከሆነ "የብረት መዝጊያ" የሚሆን ባል መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አዳነ ግን ጭራሹን ቤት የለውም ስለዚህ የባልነት ብቃት ስለሌለው እሱን ትታ ወደ ዘሴ ትሄዳለች፡፡ እሴቷን ለማስጠበቅ ስትልም ተፈጥሯዊ ከሆነው ፍቅር ጋር ግጭት ትፈጥራለች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ፍቅር ብቻ ትዳርን ሊያስመሰርትና

የአብሮነት ቆይታ ዋስትና መሆን እንደማይችል ነው። እንዲያውም ቁሳቁስ ወይም ገንዘብ ፍቅርን ሲያሸንፈውና ጥንዶችን ሲለያይ ነው።

መቼቶቹ ካፌ - አልቤርጎ - በረንዳ - ዘሴ ቤት ነው። ካፌው ብዙ ሰው የሚጠቀምበት፣ ግን ዙሪያውን የተከለለ ነው፤ ማለትም ጣራ ግርግዳና ወለል አለው፤ ነገር ግን ወደዚህ የሚገቡት ሰዎች "ዘመናዊ" የሚባሉት ናቸው። ጥንዶቹ እዚህ ቤት ሲተዋወቁ ተመሳሳይ እሳቤ ነበራቸው። ስለዚህ በአንድነት ለመኖር ፍቅር ጀመሩ። አብረው አልቤርጎ ይገባሉ። ብዙ ሰው ጊዜውን ወዳሳለፈበት፣ ወዳሮጌው፣ ወደዛገው አልቤርጎ ገብተው ረጅም ጊዜያቸውን በዚያ ያጠፋሉ። ሳባ ከዚህ መውጣትና የራሳቸው የሆነ ቤት እንዲኖራት ስትሻ አዳነ ቸልተኛ ይሆናል። በስተመጨረሻ ለመፈለግ እንኳ ሲወስን እሷን ለማስደሰት እንጂ የራስ ቤት መኖር የግድ አስፈላጊ ነው ብሎ ስላመነ አይደለም። በግጭት ወደ በረንዳ ይሄዳሉ። በረንዳው እንደ ሌሎቹ ቤት የተከለለ አይደለም፤ ግርግዳዎች ይቀሩታል። በዚህ መጠለል አይችሉም። ዝናብ ይቀጠቅጣቸዋል። በመብረቅ፣ በውሽንፍር የታጀበ ከባድ ዝናብ ነበር። ሃይል ይጠቀም የነበረው ተፈጥሮ ነው። (ዝናብ፣ መብረቅ፣ ነፋስ) ሲበላሽ፣ ቅርጹንና ውበቱን ሲያጣ የነበሩት ነገሮች ልብስ፣ የተተኮሰችው ጸጉር፣ ጫማ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ሰው ሰራሽ ስለሆኑ ግብረገብን ይወክላሉ።

ተፈጥሮ በይበልጥ ሃይሉን የሚያሳርፍባትና ሰው ሰራሽ ነገሯን የሚያበላሽባት ሳባ በካፊያው እየበሰበሰች ትሄዳለች። ይህ ማለት ሳባ በደመነፍሳዊ ፍላጎቷ ማየል ምክንያት ግብረገባዊ እሴቶቿ እንደተበላሹባትና ተፈጥሯዊ ስሜቷ እንደተቆጣጠራት ያሳያል። በአንድ ተወስና መቆየት፣ ታማኝነት፣ ጽናት እና ሌሎችም እሴቶቿ እኩይ ሆነው ይገኛሉ።

ካፌ ውስጥ ሲገናኙ በስልጣኔ መንገድ እየተጓዙ ነበር፤ ማለትም በምዕራባዊያኑ የኑሮ መስመር ለመኖር እየሞከሩ። እሴቶቻቸውን ጥለው ነበር። አልቤርጎ ሲገቡ አንድም ወሲባዊ ፍላጎታቸውን ሲያረኩ የተሰማቸውን የሰብዕና ዝቅጠት በዝገት፣ በቀፋፊነት ሲገልጽ የሌሎችን ስርዓት ተከትለው እንደሚጓዙ ለማሳየት ደግሞ የሌሎች ጠረን በቀረበት አንሶላ ላይ መተኛታቸውን ገልጿል፤ አንድም ግብረገባዊ መርሖቻቸውን ጥሰው ደመነፍሳዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት ወደ አልቤርጎ መግባታቸውን ያስረዳል። ከገቡበት ዝቅጠት ወይም "ቅንዝረኝነት" ለመውጣት የምትፈልገው ሳባ ናት። ፍርሀቷ አብራው እስከመጨረሻ ከሱ ጋር እንድትሆን ስለሚይዛት ብትታገሰውም ሁሉም ነገር እየሰለቻት ይመጣል። ከዚህ ህይወት መውጣት ግን ቀላል አይደለም።

አንድም ስትገዛለት የነበረው ደመነፍሳዊነት፣ አንድም ከኅሊናዋ የሚፈጠረው የጥፋተኝነት ስሜት ሊቆጣጠሯት ስለሚታገሉ ነውጥ ውስጥ እንድትገባ ያደርጋታል፡፡ የቀሚሷ፣ የጸጉሯ መበላሸት ሁሉ ለእነዚህ ጉዳዮች ማስረጃ ይሆናሉ፡፡ እሱ ከዚያ መውጣት ስላልፈለገም ትታው ትሄዳለች፡፡ ዘሴ የራሱ ቤት አለው፤ ማለት የራሱን እሴት አስጠብቆ የሚሄድ ነው ማለት ነው፡፡

### 3.7.2 የተፈጥሮና የባህል ዕርቅ

የሳባ መነጫነጭና ያልነበራትን ባህሪ ማሳየት የገባችበትን ሥነ ልቡናዊ ቀውስ አመላካች ነው፡፡ ከውዥንብሩ ለመውጣትና ለመሸሸ ትፈልጋለች፤ ሆኖም ዘሴ እሴቱን ጠብቆ የሚኖር ቤት ያለው ነበር፤ ጥሩ መሸሸጊያ አድርጋውም ወደ ቤቱ ስትሄድ በራሷ ቁልፍ ከፍታ ነበር የምትገባው፡፡ የባህሉ አንድ አካል ስለነበረች የባለቤትነት መብት አላት፤ ከቅጣት በኋላም በፈቃዷ ወደዚህ በመምጣቷ እርቅ ትፈጥራለች፤ ለእሴቶቿ ዋጋ በመስጠትም ጠንካራውን የማኅበረሰብ በር ከፍታ ትገባለች፡፡

አዳነም ወደ ዘሴ ቤት ነው የሚሄደው፡፡ እሱም ልክ እንደ ሳባ ሁሉ የመረጠው ወደ ነባሩ ባህል መመለስ ነው፡፡ ሁለቱም ግብረገብን ባስተማራቸው ሰው ቤት ተገናኝተዋል፡፡ የዘሴ ቤት በር ጠንካራ መሆን የሚያሳየን ምንም ያህል ጠንካራ ቢሆንም ይህንን በር ከፍታ መግባት የቻለችው ሳባ እና ተከፍቶለት የገባው አዳነ ሁለቱም በሩን “የሰከረ ዝሆን የሚመልሰውን” በር መዝለቅ ችለዋል፡፡ እንዲሁም የሚሰብከውን ግብረገብ መኖር ያልቻለው ዘሴ ሁሉም ከበሩ ውስጥ ሆኖ ከመግባት ሲከላከል አይታይም፡፡ በውስጣዊ ፈቃድና ፍላጎት ላይ ያልተገነባ ባህልን ይዘውም ሳይዙም በአንድ ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በሩ ሁሉንም ማስገባት መቻሉ የሚያሳየው ጠንካራ ቢመስልም እንኳ እንዳይገባ የሚያግደው ነገር ስለማይኖር ባህሉ በተለያዩ አመለካከቶች በሚመጡ እሴቶች ጥንካሬ እንደሌለው ይገልጻል፡፡ በዚህ አይነት ባህል ደግሞ ጽኑ የግብረገብ መሰረት እንደማይኖረውና አባላቱም አፈንግጠው በመውጣት የሚደርስባቸውን ቅጣት መቋቋም ባለመቻላቸው ግን ወደ ማኅበረሰቡ በማስመሰል ተሞልተው ሲመለሱና የሚያስተምሩት ሌላ የሚተገብሩት ሌላ፣ በመሆኑ እራሱን ችሎ መቆም ሲያቅተው ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

*ሕማማትና በገና* ከተሰኘው የአዳም ረታ መጽሐፍ ውስጥ ሰባት ታሪኮችን በአላማ ተኮር ናሙና በመምረጥ የተፈጥሮና የባህል ጉዳይ እንዴት እንደተቀነቀነ ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) የንባብን ዘዴ በመጠቀም ለማሳየት ጥረት አድርጓል፡፡ ግብረገብ ደመነፍሳዊ ስሜት ማለሳለስ አቅቶት፣ ወዲህ ተፈጥሯዊ ስሜትን ለማርካት ሽፋን ሆኖ ሲያገለግል፣ ወዲህ ደግሞ በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር ሲወድቅ ይታያል፡፡

በታሪኮቹ ውስጥ መካካድ፣ መናናቅ፣ ቃል ኪዳንን አለመጠበቅ፣ ለመልካም ድርጊት መጥፎ ምላሽ መስጠት፣ ውሸት፣ ማስመሰል፣ የበላይነትን ለማስፈን መጣር፣ ራስ ወዳድነት፣ በሌሎች ልፋት ራስን ማክበር እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ተለምዷዊ በሆኑ ተራክቦዎች ቢቀርቡም ይህ ገጽ ሲገፈፍ የሚያተኩሩት የተፈጥሮና የባህል ግጭት፣ በግጭቱ የሚፈጠር ምስቅልቅል እና ከዚህ ምስቅልቅል ለመሸሽ የሚፈጠር ዕርቅ፣ እንዲሁም ዕርቁ የሚፈጠርበት አዳዲስ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ተፈጥሮና ባህል ግጭት የሚፈጥሩት፣ አንድም ባህሉ የተፈጠረው ተፈጥሯዊ ባህሪን ተመርኩዞና ጥያቄውን በተገቢው መንገድ ለማስተናገድ በሚያመች መልኩ ሳይሆን በማመቅ እና በመጫን በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ልውጣ ልውጣ በሚለው ተፈጥሮና አይሆንም ብሎ ሊቆልፍበት በሚጥረው ባህል አንዱ አካል በሆነው ግብረገብ መካከል አለመጣጣም ይፈጠራል፡፡

ይህን አለመጣጣም ለማስወገድ ወይ ተፈጥሮ ወይ ባህል ማሸነፍ አለበት፤ ይህንንም ለመምረጥ ይቸገራሉ፡፡ ከባህሉ መጣስ በሚመጣ ቅጣት በተፈጥሮ ማየል በሚደርስ ማፈንገጥ ውስጥ ወድቀው ይማቅቃሉ፤ ወይም ሁለቱንም የሚያስማማ በመሰላቸው መንገድ በድብቅ ፍላጎታቸውን ያሟላሉ፡፡ መጋለጥን መፍራታቸውም ተጨማሪ ስጋት ይሆንባቸዋል፡፡ በሌላኛው ምዕራፍ የተገለጹት የተለያዩ የአእምሮ መቃወስ ምልክቶችም ይፈጠራሉ፡፡

አንድም የቀውሱ ሰበብ በነጻ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ ግብረገብ መኖሩ ነው፡፡ በተለያየ መንገድ በሚገኝ ዕውቀት ወይም "የስልጣኔ ባህል" በአደጉበት ማኅበረሰብ ባህል ጋር አጣጥመው ማስኬድ ባለመቻላቸው በነጻ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ፣ አብሮ ለመኖር ሲባል በሰው ፊት ተገቢ ነው ብለው የሚያምኑባቸውን በድብቅ የማይደግሟቸውና ግብረገባዊ ጽናት የሌላቸው ሲሆኑ ተስተውሏል፡፡

በእኩልነትና ነጻነት ፍላጎታቸውን የሚያሟላ አዲስ ጎዳና በመቀየስ ከተፈጥሮ ጋር እርቅ ለመፍጠር ሲጥሩ፣ የማይሆንላቸው ሲሆን ደግሞ ወደ መነጠሉ ሲሄዱ፣ ኅሊናቸው መጀመሪያ ያካበተው ዕውቀት ስህተት ሲሆንበትና አዲሱን ተቀብሎ አረጋግጦ ሳይጨርስ ከአካባቢው በሚደርስበት ግፊት ምክንያት ቀውስ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ማኅበረሰቡ የሚጥልባቸው ቅጣትም እነርሱን ከማስተማር ይልቅ ከውስጥ ከሚፈጠርባቸው ቀውስ ጋር ተዳምሮ "የአእምሮ መዛባት" እና ተያያዥ ችግሮች እንዲገጥሟቸው ያደርጋል፡፡ አንዳንዴም ቀውሱ ወደከፋ ደረጃ በማደግ ራስን እስከማስጠፋት ያደርሳል፡፡

ስለዚህ በ*ሕማማትና በገና* ውስጥ የሚገኙ አጫጭር ታሪኮች በጋራ የሚያነሱት ስለ ግብረገብ ነው፡፡ ግብረገብ ደግሞ የሰው ልጅ ተፈጥሮን በማለሳለስ ሰላማዊና እኩልነት የሰፈነበት ሕይወት እንዲኖራቸው ታልመው የተፈጠሩ እሴቶች መመሪያ ነው፡፡ እነዚህ እሴቶች ግን ሁሉንም በእኩል መንገድ ሊያስተናግዱ ባለመቻላቸው እራሱን ሽፋን እያደረጉ ኢ ግብረገባዊ ድርጊቶች ሲፈጽሙ ያሳያል፡፡ ግብረገብን ለሌላው ሊያስተምሩ የሚሞክሩትም በቃል እንጂ በተግባር አይደለም፡፡ ይህም ከሌላውም ከራሳቸውም ጋር ግጭት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ከግለሰቦች የሚጀምረው ይህ ግጭትና መነጠል በማኅበረሰብ ደረጃ ግብረገብን ጽኑ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶች እየተበራከቱ ይሄዳሉ፡፡ ተተኪውም ያለፈው ትውልድ እንዳደረገው (የሚማረውን) በአስተምህሮ ግብረገባዊ፣ በተግባሩ ግን ኢ-ግብረገባዊ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ለይሉኝታ እንጂ በውስጣዊ ፍላጎት ላይ ለተገነባ ግብረገብ ትኩረት አይኖረውም፡፡ በጋራ ሲሆን አባል የሆነ፣ በተናጠል ግን የአብሮነት መንፈስ የሌለው ማኅበረሰብ ይፈጠራል፡፡

በሌላ አንጻር እንዲሁ ሁለት አይነት የግብረገብ መሰረቶች አሉ፡፡ በእግዚአብሔር ህላዌ የሚያምኑና የማያምኑ፡፡ በአምላክ ህላዌ የሚያምኑት የሰው ልጅ በተፈጥሮ ሁሉን ዕውቀት ይዞ የተፈጠረ ስለሆነ ይህን ዕውቀት ማዳበር እንጂ መፍጠር አያስፈልገውም የሚል አቋም አላቸው፡፡ ስለዚህ በነዚኛዎቹ የግብረገብ መሰረቱ ዘላለማዊነት ነው፡፡ ዘላለማዊትን ስለሚሹ ግብረገባዊ ይሆናሉ፡፡ ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘት የሆነ ነገር ማጣት አለባቸው፡፡ ምድርን እንደ አጭር የሕይወት ክፍል ወይም የመሸጋገሪያ ድልድይ ወይም የመፈተኛ ቦታ ወዘተ. አድርገው ለሚያምኑት ምድራዊ ሕይወት አንድና ብቸኛ አይደለችም፡፡ ይልቁን ከምድራዊው ሕይወት በኋላ የሚመጣው ሕይወት ረዥም፣ ምቹ እና ዘላለማዊ ነው፡፡ ለዚህ ሕይወት መገኘት ደግሞ ምድር ላይ የተለያዩ ፈተናዎችን ወይም ስቃዮችን ወይም ክስተቶችን አልፈው ለቀጣዩ ህይወት ብቁ ለመሆን መስዋዕትነትን መክፈል የውዴታ ግዴታቸው ይሆናል፡፡ ይህንን

ግዴታም በማድረግ ግብረገባቸውን ይገነባሉ። ስለዚህ በዚህ ስር የሚገነቡት ግብረገቦች የሆነ ነገር ማጣትን ይጨምራሉ። ይህም ተፈጥሯዊ ፍላጎትን አርቆ በመጣል ቀጣዩን ሕይወት ያስገኝልኛል ብሎ ያመነውን ሕይወት መላበስ ነው። ስለዚህ ፍላጎት ይታሰራል፤ የታሰረው ደግሞ በታመቀ ቁጥር ሃይል እያበጀ ይሄዳል። እናም የፈነዳ ቀን ያጥለቀልቃቸዋል።

በእግዚአብሔር ህላዌ የማያምኑት የሰውን ልጅ ከእንስሳነት ወደ ማኅበራዊ እንስሳነት ለማሻገር የግብረገብ የግድ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ ሰዎች የሰው ልጅ በአዝግሞተ ለውጣዊው እድገታቸው ውስጥ ግብረገብ የመጨረሻ (አሁን ላለው መጨረሻ) ምርጡ ደረጃ ነው ብለው ያምናሉ። የግብረገባቸው መሰረት ሰላማዊ ሕይወት ነው። በተቻለ መጠን ደስተኛ ሕይወትን ለማግኘት ነው። ደስታን የሚፈልጉት ደግሞ ህይወት አጭርና ብቸኛ ስለሆነች በእሷ ለመጠቀም ነው። በርግጥ በእነዚህ ውስጥ ዘላለማዊነት አይታሰብም እያልኩ አይደለም። በእነዚህም ውስጥ ዘላለማዊነት ተፈላጊ ነው። ግን ይህንን ዘላለማዊነት የሚተገብሩት ወይም ይኖራል ብለው የሚያምኑት እዚሁ በተከሰቱበት ምድር ላይ ነው። ለዚህም ነው ዝነኛ የሚያደርጋቸውን ስራ "ስም ከመቃብር በላይ ይውላል" በሚለው ፈሊጥ እየታጀቡ የሚሰሩት።

ሁለቱም አመለካከቶች ደመነፍሳዊ ስሜት ከአእምሯቸው በላይ እንደሆነ ያምናሉ። ፈጣሪ አለ ብለው የሚያምኑቱ መጥፎ ስራዎች የሚሰሩትና አልባሌ ጠባይ ሊከሰት የሚችለው በልዕለ ሃይል አማካኝነት ነው ሲሉ ፈጣሪ የለም የሚሉት ደግሞ የሰው ልጅ እኩይ ባህሪ የሚፈጠረው የእንስሳነት ባህሪውን ስለወረሰ ነው ብለው ያምናሉ። የእምነታቸው መለያየትም ለምርጫ ጥንቁቅ መሆንና ከድርጊት በኋላ የሚመጣን ሃላፊነት መቀበል ላይ ልዩነትን ይፈጥራል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ሌላ ጉዳይ ለሕይወት ክብር መስጠት እና ለሞት ክብር መስጠት ናቸው። ለሞት ክብር የሚሰጡት በፈጣሪ የሚያምኑትና ሞትን ድልድይ አድርገው የሚቆጥሩት ናቸው። ለቀጣዩ ማለትም ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት እየታሰበም የተለያዩ መታሰቢያዎች (ተዝካሮች) ይደረጉለታል። ለሞት ክብር የሌላቸው ደግሞ ለሕይወት ከፍተኛ ዋጋ አላቸው። በህይወታቸው ደስታን ሊፈጥሩላቸው የሚችሉ ነገሮችንም ያደርጋሉ። ይህም ግብረገባቸው ላይ ለውጥ ያመጣል።

አንዳንድ በአብዮት የሚመጡ የባህል ለውጦች ማኅበረሰቡ ውስጥ ሰርጸው ሳይገቡ "አርቴፊሻል" ሕይወትን በሰዎች ላይ ይፈጥራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ባህሎች ተፈጥሮን ለማመቅ

ሲጥሩ የታመቀው ተፈጥሯዊ ስሜት ደግሞ ልክ እንደ "እስፕሪንግ" በሃይል በተጫነው ቁጥር ይበልጥ በመንጠር አይሎ ይወጣል፡፡

ባህሉ አንድም "በአርቴፊሻል" እሴቶች የተሞላ ከሆነ፣ አንድም ተፈጥሮን የሚያምቅ ከሆነ ደግሞ እሴቶቹ ድድርናቸውን ያጣሉ፡፡ ስለዚህም ማኅበረሰቡ ሁለት አይነት ሰብዕናዎችን ያበጃል፤ ወይም ወደ ሁለቱም ጽንፎች ይበታተናል፡፡ ከላይ በጠቀስኩት ምክንያት በዚህ መንገድ መቀጠል አይችሉም፡፡ ስለዚህ የአእምሮ እክሎች ይገጥሚቸዋል፡፡ ትርምስና ሁከት ውስጥ ይገባሉ፡፡ እነዚህ ነገሮችም ሲደጋገሙ ትክክለኛ ነገሮች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ ሁሉም የሚቃወመውን ሊያሻሽለው የሚፈልገው ነገር አለ:: ግን ሌሎች የሚሰጡት ምላሽ ደግሞ እነዚህ ሁሉ ተሳስተው እኔ ብቻ ትክክል አልሆንም የሚል አመለካከትን እንዲያበጅ ስለሚያደርጉት ከራሱ ጋር መሆን ይጀምራል፡፡ ግለሰቡ እንደ ማኅበረሰብ የባህሉ ተሳታፊና አባል ሆኖ ልክ አይደለም፣ ያሉትን ልክ አይደለም ይላል፤ ልክ ነው ያሉትን ልክ ነው ብሎ ያረጋግጣል፤ እንደ ግለሰብ ግን የራሱን እሴት ይፈጥራል፡፡ የሚፈጥረው ሰብዕና የሚያደርስበት ጫና እና የሚገጥመውን የአእምሮ እክሎች ተቋቁሞ ማለፍ የቻለ የሚያምንበትን ነገር በኑሮው ያሳያል፡፡ ይህንን ማድረግ ያልቻለ ተግባሩ ሌላ፣ እምነቱ ሌላ ሆኖ ይኖራል፡፡ የማስመሰል ሕይወቱን መቋቋም ካቃተውና እራሱን መውቀስ ከጀመረም ህመሙ በርትቶበት የከፋ ደረጃ ላይ ይወድቃል፡፡

"ሕማማትና በገና" የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡ የማኅበረሰቡን ዝብርቅርቅ የባህል እሴቶች፣ ይሁን የሚለውን ማድረግ የተሳነው፣ እራሱን እያስታመመ አብሯቸው ሆኖ የተነጠለ ግለሰብ፣ (የግለሰቦች መነጠል ደግሞ የማኅበረሰብን ህልውና ይፈታተናል፡፡) በስልጣኔና፣ በዕውቀት፣ በዘመናዊነት ላይ የሚፈጠሩ የጽንሰ ሃሳብ መዛባቶች የተፈጠሩበት ማኅበረሰብ፣ አንዱ ሌላውን ሕይወት አሰመርኩለት፤ አበጀሁለት ብሎ ሲያጠፋው የሚታይን ኅብረተሰብ፣ ተስፋ መቁረጦች የሞሉበት፣ ማንነትን አለማወቅ፣ ሰብዕናን መጠራጠር፣ ራስን መጥላትና ማጥፋት የሚያመጣ ባህል ባለቤት የሆኑ ገጸ ባህሪያትን ይዟል፡፡ በድንጋጌዎቹ ለሰው ለሚታይ የማስመሰል ድርጊቶች ይጠቀምበታል፣ እንጂ ለውስጣዊ ማንነቱ ወይም ለአብኣዊ ድርጊቶቹ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ከእንዲህ አይነቱ ማኅበረሰብ የሚፈጠሩ ትውልዶች ደግሞ ወደ ከፋ ዝቅጠት ውስጥ ሲገቡ፣ ራሳቸውን ችለው መቆም ሲያቅጣቸው፣ እርግጠኛ የሚሆኑበትን ነገር ሲያጡ፣ እንዲህ ነኝ የሚሉት ባህላዊ ማንነት ሲያጡና በአእምሮ መታወክ የተሞሉ ሆነው ይገኛሉ፤ ቴንሳና ጓደኞች፣ እንዲሁም ኤልያስ ምስክር ይሆናሉ፡፡ ጠና (2008) እንደሚሉት ለዘመናችን

እጅግ አስፈላጊው ነገር ግብረገብ ነው፡፡ የ"ቴክኖሎጂ" ዕውቀቶችና ምርቶች የመጠቁትን ያህል ግብረገባዊነት እየዘቀጠ እንጂ እያደገ አይደለም፡፡ ለልማትና ለሰላማዊ ህይወት ግን ግብረገብም ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ ነው፡፡ አዳምም በስራዎቹ ከጠና ሃሳብ ጋር የሚጋራ ጭብጥ ያቀነቅናል፡፡ ይህንን ጭብጥም ዲኮንስትራክሽናዊ (ነገረ አፍርሶታዊ) የማንበቢያ ዘዴን በመጠቀም ለማግኘት በሚቻልበት መንገድ አቅርቦታል፡፡ ቴክስቶቹ (ገጸንባቦቹ) ግብረገብ ተፈጥሮን ከማሰር ወደ ማለሳለሱ እንዲቀየር የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ የግብረገብ መሰረታቸውም ሊቀየር እንደሚገባ የሚጠቁሙም፡፡

በሌላ በኩል በሕዝባዊ ባህልና ሃገራዊ ባህል መካከል የሚፈጠር ግጭትን መመልከት ይቻላል፡፡ ሕዝባዊው ባህል በትምህርትም፤ በመገናኛ ብዙሃንም እየተስፋፋ ይሄድና ሃገራዊውን ባህል ይሸፍነዋል፡፡ ከዚህ ውጤቶች ውስጥ አንዱ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ዘመናዊ ወይም ዘመናዊነት በሚለው እሳቤ እየተመራ የሃገራዊውን ባህል እሴት ዋጋ ያሳጣዋል፡፡ አንዳንዴ ሊመጣጠኑና ሊስማሙ የማይችሉ ባህርያት ከሁለቱ ባህሎች ይፈልቃሉ፡፡ በተለይ በወሲባዊ ጉዳዮች የተቀነቀነው ጉዳይም ይህ ነው፡፡

"የስንዝሮዎቹ" ጥንቅሽና አቢይ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናሉ፡፡ ሀገራዊው ባህል ወሲብን ከትዳር በፊት ሲከለክል፣ ሕዝባዊው ባህል ወሲብን በፈለጉ ጊዜ እንዲያደርጉ ሲፈቅድ፣ ገጸባህርያቱ ደግሞ ከስልጡንነታቸው ጋር ተያይዞ የሚመጣው የሕዝባዊ ባህል ግፊት እና ከማኅበረሰባቸው ግብረገቦች በሚወጡ ፍርሃቶች መሃል አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ፡፡

## የጥቁምታ ሃሳቦች

መጽሐፉ በብዙ ጽንሰ ሃሳቦች ተዋቅሮ ስለሚገኝ ከርእሶቹ፣ ከተራኪ አንጻሩና ከሌሎችም ጽንፎች ቢጠና ውጤታማ ያደርጋል፡፡

በተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች እየታገዙ የሚመረመሩ ጉዳዮችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናት ባለበት ውስንነት ምክንያት ያልተረጎማቸውና ያልዳሰሳቸው በርካታ ጉዳዮችና ተምሳሌቶች ስላሉ በተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችና ንድፈ ሃሳቦች እየታገዙ ቢመረመሩ አንዳች መፍትሄን ያስገኛል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

በእሸቱ አጋ። "*ሥነ ምግባር* ከ1940-1953 የወጡ የአማርኛ ግጥሞች።" አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። *የሰው፡ ጠባይና፡ አብሮ፡ የመኖር፡ ዘዴ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1943 ዓ.ም።

ቴዎድሮስ አለበል። "ልጅነት" በ*ማሕሌትና አለንጋና ምስር*፤ *ሥነ* ልቡናዊ ንባብ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2006 ዓ.ም።

ቴዎድሮስ ገብሬ። *በይነዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001።

አዳም ረታ። *ሕማማትና በገና እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች።* አዲስ አበባ፤ ርሖቦት አሳታሚዎች፣ 2006 ዓ.ም (2ኛ *ዕትም*)።

ከተማ አድማሱ። *ስሜትና አእምሮ።* ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኀበር፣ 2009 ዓ.ም (ከተማ አልተገለጸም)።

የማነ ገብረ ማርያም። *የፍልስፍና ትምህርት።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1954 ዓ.ም።

ጠና ደዎ። *ሰው፣ ብግረገብ ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች።* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2008 ዓ.ም።

——— *The SAGE Dictionary of Cultural Studies*. London: SAGE Publications Ltd, 2004.

Abrhams, M.H. *A Glossary of Literary Terms.* 7th ed. Heinle & Heinle: Cornell University, 1999.

Adriano, Moraes, Migliavacca. "Morality in Poetry the New Critical A pproach." Cadernos do IL. Porto Alegre, n.º 43, dezembro de 2011. p. 295-304.

Asim, Karim. "Literature and Morality. International" J. Soc. Sci. & Education, Vol. 2, 2012. 186-193.

Baldick, Chris. *Oxford Concise Dictionary of Literary Terms.* Oxford: Oxford University Press, 2001.

Charles, W. Elito. *English Philosophers*. (Ed.) Vo. 2: New York: P.F. Collier & son, 1910.

Christopher, Norris. *Deconstruction Theory and Practice*. (3rd ed). London and New York: Taylor & Francis e-Library, 2004.

Dani, Cavallaro. *Critical And Cultural Theory Thematic Variations*. In 2001 The Athlone Press. Park Drive, London NW11 7SG And New Brunswick, New Jersey Reprinted 2006, 2007

Edwar, Quinn. *A Dictionary of Literary and Thematic Terms.* 2nd ed. United States of America, An imprint of Infobase Publishing, 2006.

Eileen, John. "Literature and the Idea of Morality." Garry L. Hagberg &Walter Jost (eds.). In A Companion to the Philosophy of Literature. West Sussex: Blackwell Publishing Ltd. 2010. Pp. 285-299.

Ferber, Michael. *A Dictionary of Literary Symbols.* (2nd ed). Cambridge: Cambridge University, 2007.

Georg, Lind. *Cultural Fairness and the Measurement of Morality*. University of Konstanz. 1995.

John, Fiske. (General Editor) *KEY CONCEPTS IN COMMUNICATION AND CULTURAL STUDIES.* 2nd ed. published in the Taylor & Francis e-Library, 2006.

Jove Jim S. Aguas. "Ethics and Moral Philosophy of Karol Wojtyla." Kritike vol. 7-1. 2013. 115-137.

Killen. and el. "Morality, development, and culture." M. Gelfand, C.Y.Chiu, & Y.Y. Hong (Ed.). Advances in culture and psychology New York: Oxford University Press. 2015. pp. 161-220.

L. Miller. *Questions that matter.* (E.d.). United states of America cominercial, printing enterprise, 1984.

Lee, Archie. And John, G. Archie. "Introduction to Ethical Studies: An Open Source Reader." Version 0.11 Edition. 2003.

Michael, C. LaBossiere. *Moral Methods Tools for Ethical Argumentation*. 1st ed. US and the UK. 2012.

Mola Feleke."Deconstructive Discourse of content as Refilected in Haddis Alemayehu's Fikir Eske Mekabir."MA Thesis, Departmenet of Foreign Language & Lieterature, Addis Ababa University, 2008.

Nataša, Pantić. MORAL EDUCATION THROUGH LITERATURE . University of Edinburgh, Edinburgh. 2006, 401-414. DOI: 10.2298/ZIPI0602401P.

Pojman, Louis, P. *How should we live? An introduction to Ethics.* Thompson Wadswoeth: 2005.

R.Gnanasekaran. "An Introduction to Derrida, Deconstruction and Post Structuralism." Vol. 3-7, pp. 2015. 211-214,

Roland, Theuas, S. Pada. "The Paradox of Ipseity and Difference: Derrida's Deconstruction and Logocentrism." Kritike: Vol.1-1, 2007. 32-51.

Stefan, Gammel. Ethics and Morality. The Ethics Portfolio- Technical University Darmstadt for Nano Cap, Routledge, 2006.

Thomas, Hobbes. *Leviathan or the Matter, Forme, & Power of a Common-wealth Ecclesiasticall and Civill.* London, printed for Andrew Crooke, at the Green Dragon in St. Pauls Church-yard: 1651.

Ttena Shale. "Moral Vision on the Continuumia Tody of selected Amharic Novels" PHD Thesis, Departmenet of Foreign Language & Lieterature, Addis Ababa University, 2008.

Wendmu Geda. "Deconstruction and Pluralist Discourse: An Analysis of Nawal, El Saadawi's novels: Woman at Point Zero and God Dies by the Nile."MA Thesis, Departmenet of Foreign Language & Lieterature, Addis Ababa University,2007.

http://www.kritike.org/journal/issue_1/pada_june2007.pdf ISSN 1908-7330

http://www.kritike.org/journal/issue_12/aguas_june2013.pdf ISSN 1908-7330 Article Jove Jim S. AguasUniversity, 2007.

ISSN: 2360-7831 http://www.academicresearchjournals.org/IJELC/Index.htm

DOI: 10.14662/IJELC2015.057

file:///C:/Users/user/Downloads/ethicsbook.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/Lind-1995_Cultural%20Fairness%20MU-95.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/Leviathan.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/Moralmethods%20of%20moral.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/aguas_june2013.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/morality%20and%20cultur.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/moral....pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/pasnau.mindandnature.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/ethics_morality%20stephen%20gammel.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/PojmanText_11781.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/BeauchampChapter1.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/Gnanasekaran.pdf

file:///C:/Users/user/Documents/Download/Download/Smith-DefinitionMoral-1999.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/Deconstruction%20(1).pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/ethics_morality%20stephen%20gammel.pdf

file:///C:/Users/user/Downloads/morality%20and%20cultur.pdf

# ማረጋገጫ

“የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በአዳም ረታ ሕማማትና በገና ውስጥ” በሚል ርስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ (ኤም.ኤ ዲግሪ) ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናት የግሌና አዲስ፤ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊ ዲሲፕሊን መሰረት የተሰራ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ስም፡- ሰላማዊት በየነ ደጀኔ

ፊርማ፡- ___________

የጥናቱ ማሟያ መርሐ ግብር፡- የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር

ቦታ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ

የቀረበበት ጊዜ፡- ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም